# ፒራሚድ ገንቢዎቹ ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን!




ድሩሲላ ዱንጂ ሒውስተን

1926 እ.ኤ.አ.

ትርጉም፡- በጌታቸው ተስፋዬ ጎጂ

መጋቢት ፲፫·፳፻፬ ዓ.ም.

# ፒራሚድ ገንቢዎቹ ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን

ደራሲ፡- ድሩሲላ ዱንጅን ሒውስተን

(1926 እ.ኤ.አ)

ትርጉም ፡-በጌታቸው ተስፋዬ ጎጂ

(2002 ዓ.ም)

Scanned by CamScanner

**የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው!።**

ተርጓሚው ከዚህ ቀደም ያሳተመው ትርጉም
"ታቦተ ፅዮንን ፍለጋ"
**The Sign and the Seal By Graham Hancok(1995)**

ጌታቸው ተስፋዬ ጎጂ

## ማስታወሻነቱ

ለባለቤቴ ለላንቺስል ተስፋዬ ለልጆ ለጽዮን፣
ለእስጢፋኖስና ለሃና ጌታቸው፡ ይሁንልኝ፡

## ምሥጋና

ይህንን መጽሐፍ እንዳነበውና እንድተረጉመው ላበረታቱኝ ሁሉ ምስጋናየን አቀርባለሁ።

## ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| መግቢያ | | 9 |
| ምዕራፍ አንድ | የኢምፖየሩ ዘመንና እድማስ | 16 |
| ምዕራፍ ሁለት | ጥንታዊቱ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ | 29 |
| ምዕራፍ ሦስት | ጥንታዊት ኢትዮጵያና ምድሯ | 43 |
| ምዕራፍ አራት | የኢትዮጵያ አስደናቂ ሥልጣኔ | 59 |
| ምዕራፍ አምስት | ቅድመ ታሪክ ግብጽ የአስደናቂ ነገሮች ምድር | 75 |
| ምዕራፍ ስድስት | ግብጽና ወርቃማው ዘመን | 91 |
| ምዕራፍ ሰባት | ግብጽና ኃያላን ፈርኦኖቿ | 107 |




Scanned by CamScanner

# ድሩሲላ ዱንጅን በተመለከተ

## (1876-1941 እ.ኤ.አ)



ድሩሲላ ከጆን ዊሊያም እና ከሊዲያ ቴሰረ ዱንጅ የተወለደች ስትሆን በመምህርነትና በጋዜጠኝነት እንዲሁም በራሷ ጥረት የታሪክ ተመራማሪነት ደረጃ የደረሰች አስደናቂ ሴት ነበረች። በ1876 እ.ኤ.አ በቨርጂንያ ግዛት ዊንቸስተር ከተማ የተወለደችውና ረጅሙን የሕይወቷን ዘመን በደቡብ ምዕራብ የኖረችው ይህች ሴት በመጀመሪያ በኦክላሆማ ቀጥሎም በፊኒክስ አሪዞና ግዛት ኖራለች። ከቤተሰቧ ጋር ከሚኒሶታ ግዛት ወደ ኦክላሆማ በመጣችበት ዘመን አባቷ በአሜሪካን ባብቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሽነሪነትና በሰባኪነት ያገለግል ነበር። አባቷ ጆን ዱንጅ በልጁ ላይ "የዘር ማንነቷን ክብር" ያሠረጸባት በመሆን ይታወቃል። ወደ አባቷ ዘንድ ይመጡ ከነበሩት ሰዎች መካከል እንደ ፍሬደሪክ ዳግላስና ብላንሽ ኬ ብሩሽ እንዲሁም ሌሎች የጥቁር ዘር ሰዎች፤በድሩሲላ አስተሳሰብ ላይ በተጨማሪ ስለ ጥቁር ዘር ምንነትና ክብር እንዲሠርጽ አድርገዋል። በሃያ ሁለት ዓመት ዕድሜዋ ያገባችው ባሏ ፐራይስ



Scanned by CamScanner

ሂውስተን፣የግምጃ ቤት ጠባቂና፣የአስራ አንድ ዓመት ታላቋም ነበር። የአንዷ ሴት ልጅ እናት የነበረችው ድሩሲላ ለአስራ ሁለት ዓመታት የሕጻናት መምህር ሆና ሠርታለች።

በ1915 እ.ኤ.አ የድሩሲላ ታናሽ ወንድም ሮስኮ፣የማተሚያ መሳሪያ በመግዛት በደቡብ የአሜሪካ ግዛት ታዋቂ የሆነ "The Black Dispatch" በመባል ይታወቅ የነበረ ሣምንታዊ ጋዜጣ ባለቤት ሆነ። ጋዜጣው የጥቁሮችን ችግር በመተንተን ይታወቃል። ድሩሲላ፣ ወንድሟን ሮስኮን በገንዘብም ሆነ በጽሑፍ አቅራቢነት ደግፈዋለች። በደብሊው ኢ.ቢ.ዱ ቡዋ (W.E.B. Du Bois) ተጽፎ "The NEGRO" በሚል ርዕስ ለሕትመት የበቃው መጽሐፍ በዚሁ በ1915 እ.ኤ.አ ነበር። ድሩሲላ፣ይህንን መጽሐፍ ካነበበች በኋላ ስሜትዋ በእጅጉ በመነካቱ ለቀጣዩ የምርምር ሥራዎቿ በር ከፋች ሆኖላታል። " The NEGRO" የተባለው የዱቡዋ መጽሐፍ ያተኮረው አውሮፓውያን አፍሪቃን በቅኝ ግዛትነት ከመያዛቸው በፊት ጥቁርን ሕዝብ ታሪክ አልባ አድርገው የጻፉትን የዘረኛ አስተሳሰብ በጥብቅ በመንቀፍ ነበር። እኚሁ ጸሓፊ፣ ከአፍሪቃዊ አመለካከት አንጻር በመነሳት የአፍሪቃን ሕዝብ ታሪክ ጽፈዋል። ይህንን በማድረጋቸው፣ከአፍሪቃ በባርነት ተነድቶና በአሜሪካ ይኖር የነበረውን ጥቁር ሕዝብ ስለምንነቱና ስለማንነቱ የጋራ አመለካከት ለማስያዝ አስችለውታል።

ይህ የዱቡዋ መጽሐፍ ለድሩሲላ ስለጥቁር ዘር ታሪክ በጥልቅ ለማጥናት ምክንያት ስለሆናት በርካታ የተዋጣላቸው የታሪክ ቅጾች (volumes) የያዙ የታሪክ መጻሕፍትን ለመጻፍ በቅታለች። የዚህ ሥራዋ ውጤት የሆነውና በ1926 ዓ.ም እ.ኤ.አ ለሕትመት የበቃው **"Wonderful Ethiopians of the Ancient Cushite Empire."** (ቅፅ 1) በመባል የሚታወቀው መጽሐፏ የጥንታዊ



ዘመን ሥልጣኔ ምንጭ ባለቤቶች የሆኑትን ጥንታዊት ግብጽንና ኢትዮጵያን ይዳስሳል። ለጥቆም በአረቢያ፣በፋርስ፣በባቢሎንና በሕንድ የነበሩትን የጥቁር ሕዝቦችን ግንኙነት በማሳየት ለአካባቢው የሥልጣኔ ባለቤቶች የጥቁር ዘር እንደሆነ ያሳያል። የድሩሲላ መጽሐፍ ታትሞ ሲወጣ፣በዋና ዋና የጥቁር ጋዜጦችና ጆርናሎች በበጎ ዓይን ቢታይም በወቅቱ ይታተም በነበረው የነጮች ጋዜጣ "ዘ ሺካጎ ዲፌንደር" ወ/ሮ ሁዋይት ኦቨንግተን፣መጽሐፉን "የግርጌ ማስታወሻ(footnote)፣ዋቢ (bibliography) እና ማውጫ (index) የሌለው በማለት ለማጣጣል ከሞከረች በኋላ "የቀረቡት ማስረጃዎች ተአማኒነት ያላቸው ከመሆኑ ባሻገር የምንረዳው ጉዳይ ስለጥቁር ሕዝቦችና ስለኩሽ ሥርወ መንግሥታት ታላቅነት ከመደነቅ በቀር ሌላ ማለት አይቻልም።" በማለት አስተያየት ሰጥታበታለች።

ለኒው ዮርክ ታይምስና ለአምስተርዳም ጋዜጣ ጽሑፍ በማቅረብ ይታወቅ የነበረው የታሪክ ሰው ጄ.ኤ.ሮጀርስ(J. A. Rogers) የድሩሲላን መጽሐፍ "በብዙ ቅጽል የታጀበና ሙገሳ የበዛበት፣ለተራ ሰው የሚሆን ግን ምሁራዊ ይዘቱን የሳተ ቢለውም ዞሮ ዞሮ "በፀሐፊዋ የቀረበው ማስረጃና የተደረገው ምርምር እጅግ ሰፊ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ገምጋሚ ጭምር(ለሮጀር) ከዚህ በፊት የማይታወቅና ፈጽሞ አዲስ የሆነ" በማለት የመጽሐፉን ማስረጃዎች እውነተኛነት ለመቀበል ተገዷል።

የድሩሲላን መጽሐፍ በተመለከተ በበጎ ዓይን የገመገመው የታሪክ ሰው አርተር ኤ ሾምበርግ (Arthur A. Schomberg) ሲጽፍ " በርግጠኝነት ለመግለጽ የምፈልገው ደራሲዋ ይህንን የመሰለ ሰፊና ጥልቅ ጥናታዊ ምርምር በማድረግ በፊታችን ያቀረበችው የታሪክ ሥራ ውጤት በእጅጉ የሚያስደንቅ ነው።"



Scanned by CamScanner

በማለት ያምድሚል። ከተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚመስለው፣ወ/ሮ ድሩሲላ በቀጣይ የጻፈቻቸው ቅጽ ሁለትና ሦስት ፈጽመው አለመታተማቸውን ሲሆን እንደሚገመተው እነዚህ ተጨማሪ መጽሐፍቶች ለሕትመት በዝግጅት ላይ እንዳሉ አንዳንድ ማሻሻያዎችና፣ ክለሳዎች እንዲሁም ተጨማሪ መረጃዎች እንደታከሉበትና የርዕስ ለውጦችም እንደተደረገበት ይታመናል። በ1927 እ.ኤ.አ ለሚ/ር ሾምበርግ በጻፈችው ደብዳቤ"ድንቅ ኢትዮጵያውያን" ስለተባለው መጽሐፏ ስትገልጽ "ያነበብከው መጽሐፍ ከሦስቱ ቅጾች አንዱን ብቻ ነው፣የተቀሩት ሁለት ቅጾች መቼ እንደሚታተሙ አላውቅም። ቅጽ ሁለት የሚገልጸው ጥንታዊ ኩሾች በምዕራብ አውሮፓ.....ቀጥሎ ከሁሉም ውብ የሆነው መጽሐፍ ሦስተኛው ቅጽ ነው " ብላለች።



# ከተርጓሚው

በጥቁሯ የታሪክ ፀሐፊ፣ ወ/ሮ ዱሩሲላ ደንጅ ሂውስተን በ1926 ዓ.ም እ.ኤ.አ ለሕትመት የበቃው ይህ የታሪክ መጽሐፍ ታትሞ በወጣበት ዘመን፣ የዓለማችንን የታሪክ ጸሓፍት በእጅጉ ያስደነገጠና ዝምታን ያሰፈነ ነበረ። መጽሐፉ በአራት ዋና ዋና ርዕሶች የተከፋፈለና አሳማኝ መረጃዎችን ያዘለ ሲሆን፣የመጀመሪያው ክፍል የኢትዮጵያንና የግብጽን ሥልጣኔ ይተርካል፣ ከክፍል ሁለት እስከ አራት ደግሞ ኩሻዊ ኢትዮጵያውያን ለአረብ፣ለባቢሎንና፣ለሕንድ ያስተላለፉትን ሥልጣኔ ይዳስሳል። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ትኩረቱን ያደረገው ግን በኢትዮጵያና ግብጽ ሥልጣኔና ግንኙነት ብቻ ላይ በመሆኑ ይህንኑ ክፍል ብቻ ለትርጉም አብቅቶታል። አንባብያን ከዚህ ትርጉም ከፍተኛ ግንዛቤ ለመጨበጥ እንደሚችሉ እምነቴ ነው። ከሦስቱ የኖህ ልጆች መካከል የጥቁሩ ካም ልጅ፣ ኩሽ በተለየ መልኩ ለዓለም ሕዝቦች የሥልጣኔ ምንጭ እንደነበር ከግብጽ እስከ ሕንድ፣ከሶኡዳን እስከ አቢሲኒያ ከታናሹ እስያ እስከ ስፖኝ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ አሜሪካ፣ ከኖርዌይ እስከ ሩሲያ፣በቁፋሮ የተገኙት አርኪኦሎጂካዊ መረጃዎች ሕያው ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።

የኩሽ ዘር የሆኑት ኢትዮጵያውያን ለሰው ዘር የሥልጣኔ፣የባህል፣የሥነ ጥበብ፣የሃይማኖት፣የመንግሥትና፣የሕግ መሠረቶችን በመጣል ያበረከቱትን አስተዋጽዖ ከጥንታውያኑና ከእውነተኞቹ ታሪካዊ ቅርሶች የታሪካዊ መዛግብቶችና ማህደራት ለመመልከት ያስችለናል። ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ ዛሬ በአሉታዊ መልኩ የምናየውና የምንሰማው ሁሉ ታሪካችንን ከሥረ መሠረቱ ካለማጥናት፣ካለመመርመር፣ካለመረዳትና ካለማወቅ የመነጨ ነው።



Scanned by CamScanner

ከዚህም በላይ ስለምንነታችንና ማንነታችን አውቀን የጥንቱን ታሪካችንን እንዳናድስ በረቀቀ ዘዴ የዓለም አቀፉ ሴራ ተጠቂዎች ሆነናል:: ዛሬ በዓለማችን በድህነት፣በራብተኝነትና፣በኋላቀርነት የቀደምትነቱን ስፍራ ይዘናል:: ቢሆንም "ከጥንቱ ዘር" በደማችንና በአጥንታችን ውስጥ የወረስናቸውን ጥበብና ዕውቀት በኃያሉ ፈጣሪ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ተጠቃሚ እንድንሆን ወደ ፈጣሪያችን በንጽሕና መመለስ ይገባናል:: "ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ሊለውጥ ይችላልን?" ተብሎ በእግዚአብሐር ነብይ በኤርምያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 13 ቁ. 23 የተነገረው ቃል እስከ ዘመኑ ፍጻሜ የፀና በመሆኑ፣ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በቅድስና እጆቻችንን ወደ እግዚአብሔር ከዘረጋን (መዝ፣67 (68):31) ያለምንም ጥርጥር ወደቀደመው ክብራችን እንደምንመለስ ተርጓሚው ባለሙሉ ተስፋ ነው::

በየትኛውም የሕዝብ ቤተ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች ለሰው ዘር ሥልጣኔ ምንጭ ስለሆኑት ስለኢትዮጵያውያን አንዳችም ፋይዳ አይሰጡም:: ሆኖም ግን፣ጥንታውያኑ ያረጁና ያፈጁ መጻሕፍት በተመረመሩ ጊዜያት ለዘመናችን ከፍተኛ ሥልጣኔ ምንጮች እነማን እንደነበሩ እውነቱን ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ:: ለሦስት ሺህ ዘመናት ያለ ምንም ማቋረጥ በሦስት አህጉራት የዘለቀው የጥንታዊ ኩሽ ኢትዮጵያውያን ኤምፓየር ታሪክ የማቆራኝ ሰንሰለት እነሆ! "አማልክት አብረዋቸው በግብዣ ለመቀመጥ የሚወዷቸው ሃይማኖታዊ ሰዎች በማለት ሄሮዶተስ የተናገረላትን የጥንታዊቱን ኢትዮጵያ ምድርና "የጥንት ዘር" እንመልከት::

* <u>መፍቻ</u> ቅ.ል.ክ ማለት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ



## **መግቢያ** (ከደራሲዋ)

የሥልጣኔ ምንጭ ከየት እንደሆነ ከጥንት አንስቶ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ መልስ ለማግኘት እየተሞከረ ነው:: ከግብጽ፣ከጥንታዊቷ ባቢሎን፣ከደቡብ አሜሪካ፣አርኪዎሎጅስቶች በቁፋሮ ያገኟቸው መረጃዎች እንደሚገልጹት የሣይንስና የሥነ ጥበብ ውጤቶች ጥንት ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው እንደነበረ ቢሆንም፣ ታሪክ ግን ስለእነዚህ ጉዳዮች ግልጽ ማድረግ አልቻለም:: የጥንቱን የሰው ዘር አኗኗር በተመለከተ የተጻፉትን መጻሕፍት ማግኘት እጅግ ከባድ ቢሆንም፣ ሳይንቲስቶች፣ ስለአሁኑና ስለጥንቱ ሥልጣኔ በማነጻጸር እያጠኑ ናቸው:: የጥናቱ አስቸጋሪነትና የሚጠይቀው ቴክኒካዊ ክህሎት ከፍተኛ፣ በእውነት ላይ የተመረከዙ መጻሕፍቶች በጣም ጥቂቶች ቢሆኑም፣ ሥልጣኔ ከየት እንደመነጨ ለመግለጽ ሙከራው አላበቃም:: በዘመናችን፣የትኛው የሰው ዘር፣በተለይ ለዓለም ሥልጣኔ ምንጭ እንደነበር ያለ አድልዎ ለመናገር ዝግጁ አእምሮን ይጠይቃል::

ኬልቶችና ቲውቶኖች፣የዘመናችን ኢትዮጵያውያንን አጉቶቻችንና አክስቶቻችን በማለት መጥራታቸው ሣይንሳዊ እውነታን ያዘለ ከመሆኑም ባሻገር ሌላው የሚደንቀው ጉዳይ ዛሬ በስፖኝ ግዛት ባስክ በተባለው ክልል የሚኖሩት አይቤራውያን(Iberians) ሥረ መሠረታቸውን ከጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ኩሽ ኤምፖየር አድርገው የመናገራቸው ጉዳይ ነው:: አንዳንድ ተመራማሪዎች "የአትላንቲስ ሕዝቦች" ይሏቸዋል:: ሌላው የሚገርመው፣በድሮዋ ኢጣሊያ ይኖሩ የነበሩት ኢትሩስካኖች(Etruscans) የተባሉት ሕዝቦች ጉዳይ ሲሆን፣ ምንጫቸው ስውር የሆነ፣ነገር ግን ሮማውያንን ያስተማሩ በመሆናቸው ይታወቃሉ:: በተጨማሪ ፈላስጂያኖች(Pelasgians) ለግሪክ ባህል መዳበር፣ መነሳትና መውደቅ በተቆራኘ መልኩ፣በግሪክ አፈ-ታሪክ ሲጠቀሱ ኖረዋል፣ነገር ግን፣በታሪክ



Scanned by CamScanner

ጽሑፎች ውስጥ ስለእነዚህ ሕዝቦች በተበታተነ ሁኔታ ተጠቅሶ ይገኛል:: ይህ ሥራ እነዚህን የተበታተኑ መረጃዎች አሰባስቦ አንድ ወጥ ምዕራፎች አድርጓቸዋል:: እዚህ ላይ ለአንድ አፍታ ቆም ብለን ጠፍቶ ስለቀረው ኤጂያዊ (Aegean) ሥልጣኔ፣ስለግሪካዊ ሆሜርና ስለ አፈታሪኮቻቸው፣ታሪካዊቷን ግሪክ ከነሙሉ ክብሯ ስናጠናት የሚታሰበን ጉዳይ ሥልጣኔን የተቀዳጀችው ከታናሽቱ እሲያ ስለመሆኑ የዘመናችን መጻሕፍት ሳይጠቅሱት ማለፋቸውን ነው::

ፊንቃውያን(Phoencians) ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን ብለው ይጠሩ ነበር:: ዕብራውያንም ደግሞ ይህንኑ ተቀብለው ኢትዮጵያውያን ብለዋቸዋል:: በኢንዶ አውሮፓውያንና በኩሽ ልሣን መካከል ያለውን ዝምድና ያጤነ ተመራማሪ ደግሞ የተለየ ሲያደርጋቸው እናያለን:: የዛሬዎቹን ኢትዮጵያውያን አንፀባራቂ ሃይማኖት ስንመለከት፤ እንዲሁም በእነርሱ ላይ ስለምናያቸው መረዳትን ስለሚያዳግቱ ባህርያትና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ስናጠና፣ለብዙ ጥያቄዎቻችን መልሶችን ያስገኝልናል:: የጥንቶቹ ድንቅ ኢትዮጵያውያን የቀለም ሥራዎች ለዘመናት ፈጽሞ የማይደበዝዙ፣ጠንካራ አለትን ሰርስሮ የመቆፈር ችሎታ የነበራቸው፣ እንደብዙ ሣይንቲስቶች አባባል ዛሬ ለጠፋት በርካታ የሥነ ጥበብ ውጤቶች ባለቤቶች የነበሩ፣በዘመናቸው የኤሌክትሪክ ባህርያትን በማወቃቸው ከሜታል ሮቦቶችን የሰሩ፣ "ፔጋሰስ" (በራሪ ፈረስ) የፈበረኩ ቢሆንም፤ዛሬ ግን እነዚህ ሁሉ ድንቅ የስራ ውጤቶቻቸው እንደ አፈታሪክ ሲነገሩ ይታያል::

የጥንታዊቷን ኩሽ ኢትዮጵያ የንግድ እንቅስቃሴን በተመለከተ፣በተራቀቀ ክህሎት የተሞሉት ደፋር ባህረተኞቿ መርከቦቻቸው የዓለማችንን ውቅያኖሶች ሰንጥቀው ስለማለፋቸው ፈጽሞ የማያጠራጥር መረጃዎችን እናገኛለን:: ለዚህም ማስረጃ የሆኑ የኢትዮጵያውያን የባህልና የሃይማኖታዊ ቅርሶች ዛሬም



በአሜሪካን ኢንስቲውቲሽኖች ውስጥ ይገኛሉ:: በደብዛዛው ከሚታወቀው የጥንት ታሪክ ውስጥ ስለሰው ዘር ሥልጣኔ ምንጭ "የጥንቱ አትላንቲስ" ይታወቃል:: እነዚህ የአትላንቲስ ሰዎች እንስሳትን በማላመድ፣ዕፅዋትን በማዳቀል ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ግሪኮችና ሮማውያን እንደአማልክቶቻቸው ይጠሯቸው የነበሩት እነዚህ የኩሽ ኢምፖየር ነገሥታትና ንግሥቲቶች ከአትላንቲስ የዘር ግንድ አንዱ ነበር ተብሎ ይታመናል:: ስለእነዚህ ነገሥታት፤ የጥንት ዘመናትን የታሪክ ጽሑፎች፣ ትረካዎችንና አፈታሪኮችን ለሚያጠናና ለሚመራመር በቀላሉ መረዳት ይቻለዋል::

እነዚህ ነገሥታት በሕንድ፣በከላውዴዎን፣በግብጽ፣በግሪክና በሮማ እስከ መመለክ ደረጃም ደርሰው ነበር፣ከልደተ ክርስቶስ በኋላም እስከ እረማውያን ውድቀት ድረስ የአትላንቲስ ዘር በሕዝቦች ሥነ ጥበብና ሥነ ጽሑፍ ውስጥ በሰፊው ሲጠቀሱ የመኖራቸው ጉዳይ የታሪኩን ተጨባጭነት ያረጋግጣል:: የአትላንቲስ አንዱ ቅርንጫፍ ትራንስ አትላንቲክ አሜሪካ ሲሆን፤ሰማይ ጠቀስ ሕንጻዎችን ገንቢ የነበሩት ኩሾች ስለመሆናቸው መጻሕፍት ይገልጻሉ:: አስፈሪ የነበሩትን የአዝቴክ ሕዝቦች ባህል ስናጠና ለሥልጣኔያቸው እርሾ የኩሽ ሰዎች እንደነበሩ፤እንዲሁም በደቡብ አሜሪካ ለማያ (Maya) ሥልጣኔ ምንጭ በርግጠኝነት የኩሽ ተጽእኖ እንደነበረበት ለማወቅ ይቻላል:: የኢንካ (Incas) ሥልጣኔ ማረጋገጫ የሆኑና በ1492 እ.ኤ.አ በምእራብ አውሮፖ የተገኙት የነሐስ መገልገያዎች የሚያረጋግጡት፣በዚያን ዘመን በአውሮፖ ይኖሩ በነበሩ ሰዎች ያልተሰሩ ስለመሆናቸው ሲሆን፣በሦስት አህጉራት ላይ የበላይነትን ተቀዳጅተው በነበሩ ኩሽ ኢትዮጵያውያን ድንቅ የብየዳ ዕውቀትና ጥበብ መሠራታቸውን አረጋግጧል:: ይህንን መረጃ ለማቅረብ የተፈለገበት ምክንያት ለዛሬው ዘመናዊ ባህል መዳበር ሥረ መሠረት የነበሩትን ጥንታውያን ሕዝቦችን



Scanned by CamScanner

ማንነት ለመግለጽ የቆሙ ጥቂት ሰዎች በመገኘታቸው ነው። የዘመናችን ጥናትና ምርመር ሥራዎች የተባሉት በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ብስለትና ጥልቀት በሌላቸውና በወገንተኝነትም በተሞሉ ሰዎች የተበረዙ ናቸው። ዛሬ የሚነበቡት የታሪክ መጽሐፍት ከእነርሱ በፊት ስለነበሩ ጥንታዊ ሰዎች ቀደምት ጸሐፍት የተናገሩትን ፈጽሞ የሚቃረኑ ሆነው ተገኝተዋል። እውነተኛው የባህላችን ምንጭ ከየት እንደነበረ፣መሠረታዊ መርሆቹስ ምን እንደነበሩ፣ማስተዋልና ጥበብን ስናገኝ ብቻ ነው የዛሬውን የሰው ልጅ አኗኗር ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የምንችለው።

ባሳለፍናቸው ዘመናት በገዥነት ቦታ ተቀምጠው የነበሩ ሰዎች እጅግ ብዙ ስህተቶችን ሲፈጽሙ የታዩበት ምክንያት መረጃ አልባ በመሆናው ሲሆን፣ በዚህም የተነሳ ሚዛናዊ መሪዎች ሊሆኑ አልቻሉም። በመሪነት የሚቀመጡ ሰዎች መረጃ አልባ ከሆኑ ደግሞ ከመንግሥት መሪ የማይጠበቅና ተራ የሆነ የፖለቲካ ፍላጐታቸው ብቻ ያንጸባርቃሉ። በዚህም የተነሳ ከእነርሱ የፈለቀ በጐ ነገር ለዓለማችን ሲታይ አልቻለም፣ትርፉ መከራ ማምጣታቸው ብቻ ነበር። ዘረኝነትና አብሮት የተቆራኘው አድልዎ ለዓለማችን ግስጋሴ ታላቁ ችግር ሆኗል። ለሕብረተሰብ ክፍሎች መጋጨት ዋናው ምክንያት የዓለማችን ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ በጥቂቶች እጅ እየተከማቸ የመሄዱ ጉዳይ ሲሆን፣ለሰው ልጅ አሳዛኝ ገጽታና መከራ መጨመር ዋናው ምክንያት ነው። በዚህም የተነሳ በዘመናችን የሚታየው አርቲፊሳላዊነት ራሳችንን እንደገና እንድንመረምር ያስገድደናል።

የዘመናችንን መጻሕፍት ስንመለከት በተቀናበረ መልኩ የኢትዮጵያውያንን ገጽታ በማጉደፍ የጎስቋላዋን ኢትዮጵያ ስዕል በሚያሳፍር መልኩ ሲያስተላልፉ ይታያሉ። ይህም በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደ ዓለም አቀፍ ሴራ እንዳለ ያሳያል።



ምክንያቱም ይህ መጽሐፍ ሊገልጻቸው ያለውን እውነታ በመደበቅ ወንጀል ተሳትፈዋልና። ዛሬ በዓለማችን የተመረጡ ዘሮች የተባሉት የሥልጣኔው ቁንጮ ሆነው ቢታዩም፣ቀድሞ ግን የሰው ልጅ ዕድል ፈንታን ጨብጠው የነበሩት አሁን በከፍተኛ ተሰፋ አስቆራጭና ዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙት የኩሽ ኢትዮጵያዊ ዘር ነው።

የሰለጠነ የሰው ዘር ዓላማ ሌላውን ለመጉዳት መሆን የለበትም። ከእኛ ስለተለዩ ሕዝቦች መረጃ እንዳናገኝ ተደርጓል። በአመለካከታችን ጠባብና ከልላዊ ሆነናል። በሰው ዘሮች መካከል ለሚከሰተው ጥላቻ ምንጩ አንዱ ስለሌላው ባለመረዳቱ የተነሣ ሲሆን፣በዓለም በተጓዥነታቸው የሚታወቁና ስለሰው ዘር አመጣጥ ያነበቡ፣ በአእምሮ የተመራመሩና ስለችግሮቹ የተረዱ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚሁ ሰዎች ናቸው ለሰው ልጆች መቀራረብና ወንድማማችነት ሲሰሩ የሚታዩት። በደካማ ሕዝቦች ላይ ለደረሰው አስከፊ የፍትህ መጓደልና ግፍ የእንግሊዝ፣የፈረንሣይ፣የጀርመንና የአሜሪካ ሕዝቦች ስለታሪክ መረጃዎች አለማወቃቸው ሲሆን፣በዚህም የተነሳ ንጹሑ ወገን ከበደለኛው ጋር ሲቀጣ ታይቷል፣ነገር ግን እኛ እውነቱን ብንገልጽ የራስ ወዳዶች ኃይል ይወገዳል።

በዚህ ረገድ አንድ ጥያቄ በአእምሮአችን ውስጥ ይብሰለሰላል፤ይኸውም ኢትዮጵያውያን ከሌላው ሕዝብ ጋር እኩል እድል ለምን ተነፈጋቸው? ከታሪክ ማህደር ከተገኙት መረጃዎች ተነስተን ይህንን ጉዳይ ለአንዴና ለሁልጊዜ የሚሆን እልባት መስጠት ይገባናል። ርግጠኞች ነን እኛ ኢትዮጵያውያንን የተዋረዱ ሕዝቦች አድርገን እንደቆጠርናቸው ሁሉ እነርሱ ደግሞ ዕድሉን ቢያገኙ እኛ እንዳደረግንባቸው እንደማያደርጉብን የታመነ ነው። ይህ ደግሞ ግምት አይደለም ስለማንነታቸው ባህርይ በጥንታውያኑ መዛግብት ውስጥ የተገኙት መረጃዎች ያረጋግጣሉና። የኩሽ ኢትዮጵያውያን ዘር ሲወርድ



Scanned by CamScanner

ሲዋረድ የመጣው ታሪክ እጅግ አስደሳች አልነበረም ነበር። የሚገርመው ግን፣የእነርሱን ማንነት ለመረዳት የሚያስችሉን የተትረፈረፉ መዛግብትና ማስረጃዎች ለብዙ ዘመናት ተሸፍነው የመቆየታቸው ጉዳይ ነው።

ኩሽ ኢትዮጵያዊው ታላቅ ዘር ነው። ምናልባት በምድር የሸመገለ የሰው ዘር፣በማናቸውም መከራ ውስጥ የማይሸነፍና የማይሞት። ሌሎች የሰው ዘሮች ድምጻቸውን ሲያጠፉ ወይም ተስፋ ቆርጠው ራሳቸውን ወደ ማጥፋት ሲመለሱ፣ኢትዮጵያውያን ግን ችግሮችን በፀጋ ተቀብለው በደስተኝነት ጉዟቸውን የሚቀጥሉ ናቸው። መንገዶች ሁሉ የተዘጉ ሲሆኑባቸው ጊዜንና ቅዝምዝምን ጉንበስ ብሎ ማሳለፍ ነው በሚለው ዘይቤአቸው ክፉን በትዕግስት በማሳለፍ ወደ ቀደመው ጉዟቸው በመቀጠል የታወቁ ናቸው። ዛሬ የናቅናቸው ኢትዮጵያውያን ዘመናት ያሳለፉትን የግብጽ ፒራሚዶች የገነቡ፣የሥልጣኔን መሠረት ያስቀመጡ ሕዝቦች ለመሆናቸው ዓይነ ልቦናችንን ከፍተን መቀበል ያለብን ጉዳይ ነው። ያለፉት ዘመናት ካሳደረባቸው ጫና የተነሳ ዛሬ ራሳቸውን ደፍተው በመካከላችን ያሉት እነዚህ ሕዝቦች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስላለው ስለራሳቸው ታሪክ አያውቁም። እናንተ፣የተዋረዳችሁና የተገሣቆላችሁ ኢትዮጵያውያን፣ራሳችሁን ከፍ አድርጉ! የጥንት ቅድመ አያቶቻችሁ የሠሯቸውን የድንቅ ሥራዎች ታሪክ አድምጡ! እናንተ የአርያን ዘሮች ከእንቅልፋችሁ ንቁ! በውስጣችሁ ታምቆ ያለውን ኃይልና ችሎታ ላለንበት የዓለማችን ዘመን አበርክቱ! ለዘመናችን የሥልጣኔ ውድቀት ምክንያቱ፣ይህ በእናንተ ውስጥ ያለው ኃይል በጥቅም ላይ ባለመዋሉ ነው። እኛው እራሳችን በተቀበልነው ሣይንስ የተረጋገጠው፣**የኩሽ ዘር የሥልጣኔ ፏፏቴ መሆኑን ነው።** ከሆነ፣ እውነቱን ከፈለጋችሁና ሚዛናዊ ፍርድ ለመስጠት የምትሹ በመግለጽ እስኪ የአርኪኦሎጂ፣የኤትኖሎጂ፣የጂኦሎጅና፣የፊሎሶፊ መዛግብቶችን



ይህን የጥንታውያንን እጅግ አስደናቂ አስገራሚና አኩሪ የታሪክ ድራማ እንመልከት።

ዛሬ በዓለማችን ያሉን ተቋማት፣ሕጎቻችን፣ጾታዊ ሃሣቦቻችን ባህሎቻችን መሠረታቸው ከኩሽ ዘር ውርስ የሆኑ ናቸው። ይህንን ስንል የዛሬዎቹን ኩሾች እንዲያው በከንቱ ውዳሴ እንዲኩራሩ ለማድረግ ሳይሆን፣ከጥንት አባቶቻቸው የወረሱትን፣ነገር ግን ተዳፍኖ የቀረውን በጎውን ነገር ሁሉ ወደተቀደሰና ከፍተኛ የልዕልና ደረጃ እንዲያሸጋግሩት ለመቀስቀስ ነው። በዓለማችን ስለሚገኙ የሕዝብ ክፍሎች ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን እንደሆኑ ተለይተው የመታወቃቸው ጉዳይ ለዘመናችን የዓለም መሪዎች ጠቀሜታው ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዳይስቱ ስለሚያደርጋቸው ነው። ያለእንደዚህ አይነት ዕውቀት መመራት፣ሕዝቦች ከፈጣሪ አምላክ የተሰጣቸውን ጸጋና ሊያበረክቱት የሚገባቸውን ድርሻ የሚያስተጓጉል ሊሆን ይችላል። ይህንን እውነታ ሕዝቦች ካልተገነዘቡት ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ ካለፉት የዓለም ጦርነቶች መገንዘብ ይቻላል። ዓለም አቀፋዊው መረጋጋት ሊከሰት አይችልም። የሰው ልጅን እውነተኛ የታሪክ ዕውቀት እንደአላስፈላጊ ዕውቀት በመቁጠራችን የዓለም ሰላም ሚዛን ሊጠበቅ አልተቻለም። ለሥልጣኔያችን መቀጠል ከሚደረጉት አስተዋጽኦዎች መካከል ለባህላችን መንስኤ ስለሆኑት እውነተኛና ጥንታ መረጃዎች ከጥንታዊውና ከዘመኑ መዛግብት መረጃ ማሰባሰብን ይጠይቃል።



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ አንድ

## የኤምፖየሩ ዘመንና አድማስ

በግብጽ ምድር የተለየ፤ ብቸኛ፤የተራቀቀ ባህልና ሥልጣኔ በመጀመሪያው ሥርወ መንግሥት እንደነበር ፔትሪ (Petrie) አረጋግጧል። "አረባዊ የተባለው ጥንታዊ ባህል ተከትሎም የታየው ወደር የለሽ የሥነ ጽሑፍ እመርታ፤እንዲሁም የከላውዴውያኑ ጥንታዊ ባህል ከጥንታዊው ኩሽ የኢትዮጵያ ኤምፖየር የተገኙ ናቸው። በብዙ ሚስጢራዊ መሽፈኛዎች የተሸፈኑችው፤ በበርካታ አዝናኝ አፈታሪኮቿና አስማታዊ ትረካዎቿና በፍልስፍናዋ የምትታወቀው ሕንድ፤እንዲሁም የጥንቶቹ ሜዶናውያና የፋርስ አኗኗር ስርዓት ብሎም የድል ገድሎቻቸውን ስናጠና ተጽእኖአቸው እስከ ምዕራብ አውሮፖ የመዝለቁ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ለመንስኤው በርካታ ጥያቄዎችንም ይጭራሉ። ኬልቶች(Celts) እነማን ናቸው? ቲውቶኖችስ? (Teutons) "የአርያን ዘር" የተባለው ምንጩ ከየት ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶች አንባብያንን ብቻ ሳይሆን ደራሲዋንም ጭምር ለማመን የሚያስቸግር ነው። አርኪኦሎጅስቶች መረጃ ለማግኘት ይቆፍራሉ፤ኢትኖሎጅስቶች የመረጃ ምንጫቸውን ያሳውቃሉ፤ ሆኖም ግን ታሪክ ጸሓፍት ያንኑ ያረጀ ያፈጀ ግትር ንድፈ ሃሣብ ያራምዳሉ። ፔትሪ፤በተባለ አርኪኦሎጅስት አማካኝነት በግብጽ ምድር የተገኘው የቁፋሮ መረጃ ግን በምድራችን የሰለጠነ የሰው ዘር ይኖር እንደነበር ያረጋግጥልናል።



ከግብጽ ከተገኙት መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ይህ የሰው ዘር ሥልጣኔ ቀደምት የነበረና በላቀም ደረጃ ላይ ይገኝ እንደነበር ከመረጋገጡም ባሻገር፤ሥልጣኔው በቅድመ ታሪክ ዘመናት ከነበሩት ሁሉ ልዩና የጥንታዊው ዘር መገለጫም እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ የጥንት ሰው ዘር፤የጥንቱ ዓለም ሥልጣኔ ጮራ ፈንጣቂና አቅኝ ነበረ። ይህም አቅኝ የሰው ዘር እንደጥንቶቹ አነጋገር የማይንስና የሥነ ጥበብ መገኛ ከሆነው ከኩሽ ኢትዮጵያውያን ዘር ስለመሆኑ ተመራማሪዎቹ ያምናሉ። በኰሎምበስ ዘመን ወደ ሕንድ ፍልሰት የነበረበት ምክንያት አስደናቂ ጥበቦቿ አውሮፖውያንን ስለሳቡ ነበር። እንዲሁም ውድና የተደነቁ ቁሣቁሶች ባለቤት የነበረችው ባቢሎንና የትንሿ እስያ አስገራሚ ሥልጣኔ ተገኘ ተብሎ የሚታመነው እምብዛም ከማይታወቀው ኩሽ ኢትዮጵያውያን ዘር ስለመሆኑ ታሪክ ይጠቅሳል።

የኩሽ ዘር የሥራ ውጤቶች በሕብረት ሥራ ላይ የተመረኮዙና የእውነተኛ ዲሞክራሲ መገለጫ ነበሩ፤ሌላው ደግሞ ኩሾች በክህሎታቸው የተራቀቁ ስለነበሩ ታላላቅ ሕንጻዎችን ገንብተዋል፤ግዙፍ ሐይቆችን ቆፍረዋል፤ዘመናትን ያሳለፉ የማይፈራርሱ መንገዶችን ሰርተዋል። የጥንቶቹ መዛግብትና ዜና መዋዕሎች በአንድነት ያረጋገጡት ይህንኑ ነው። የዘመናችን ተመራማሪዎችና ጸሓፍት ግን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እነዚህን እውነታዎች ችላ ብለዋቸዋል።



Scanned by CamScanner

የግብጽ ሥልጣኔ ባንዴ ቦግ ብሎ የመጣ ሳይሆን፣የብዙ ሺህ ዘመናት ዕድገትን ስለማስቆጠሩና ረጅም ዘመናትን ስለመቆየቱ ታሪክ ይገልጻል:: የዓለማችን የታሪክ ሰዎችና ተመራማሪዎች ግን ከግብጽ ሥልጣኔ በፊት የነበረውን ቅድመ ታሪክ ከመግለጽ ዝምታን መርጠዋል:: ለምን ይሆን? የግብጽ ሥልጣኔ ሲጠሳ ግን ጉዳዩ ጥንታዊውን ዓለም ሲያስደንቀው መኖሩ የታወቀ ነው:: ከዚህ ሥልጣኔ በስተጀርባ ማን ነበር? የግብጽ ሥልጣኔ ምንጩ ከታችኛው አባይ እንዳልሆነ ቢታወቅም፣የሥልጣኔ መምህሯ ማን እንደነበር እውነቱን ለመግለጽ ለምን ፍራቻ ነገሰ? ለዚህ ምክንያቱ፣የዚህ ሥልጣኔ ምንጩ ኩሽ ኢትዮጵያውያን ስለመሆናቸው የታወቁና ስለታሪክ ጉዳይ በሥልጣን የሚናገሩ ምሁራን በማረጋገጣቸው ነው:: በሰው ልጅ ታሪክ "አቴና" ብቻ ነበረች በቅጽበት የዕውቀትና የሥነ ጥበብ ባለቤት ለመሆን የበቃችው::

እነዚህን እውነታዎች ለመመስከር ዓለም እስከመቼ ዝምታን ይመርጣል? የታላቁ እስክንድር፣የጁሊየስ ቄሣርና የናፖሊዎን ቦናፖርት ድሎች ከኢትዮጵያኖቹ ገድል አኳያ እንደኢምንት የሚቆጠሩ ቢሆኑም፣ስለእነዚህ ጥንታውያን ሕዝቦች ለመናገር ፍራቻ ነግሶአል:: በሜዴተራንያን ባህር ዳርቻ እንደሰንሰለት ተቆራኝተው የነበሩትና ዛሬ ፍርስራሾቻቸው በምስክርነት የሚታዩት ከተሞች፣የኩሽ ኢትዮጵያውያን የሥነ ጥበብ ሥራዎች አይደሉምን? የኩሽ ኢትዮጵያውያን ኤምፖየር በነበሩባቸው አህጉራት ውስጥ ተሰርተው በለነበሩት ድንቅ ሥራዎችስ ሳይንቲስቶች መረጃ በእጃቸው ስለመኖሩ የታወቀ አይደለምን? ዓለም ከግብጽ በቁፋሮ



ስለተገኙት ድንቅ ቅርሶች ሁሉ ይደነቃል፣ግብጽ የነበራትን ጥበብ ለግሪክና ለሮማ እንደአስተላለፈች ታሪክ ይመሰክራል::

እስኪ ለአንድ አፍታ በዚያች ምድር ስለተከናወኑት ሥራዎች በሣይንሳዊ መነጽር እንመልከት፣ስለ አቅኚው "የጥንቱ ዘር" ጥቂት እንበል:: ኢትዮጵያ ስንል በአፍሪቃ አህጉር በተወሰነ ስፍራ ስለምትገኝ ሃገር ማሰባችን የተለመደ ነው፣ጥንት ግን እውነታው ይህ አልነበረም:: የጥንት ካርታዎችንና ሥነ ምድራዊ አቀማመጥን የሚገልጹ መረጃዎችን ስናጠና፣የጥንቶቹ ኩሽ ምድር እጅግ ሰፊና ኃያል ኤምፖየር እንደነበር መገንዘብ ይቻላል:: እንደ ሮዘንሙለር አባባል፣የዕብራውያን ምሁራን የኩሽ ምድር የሚሉት በረሃማውን ክፍል ነው:: እንደ ሀክስሌይ አገላለጽ፣ድራቭዲያን ሕንዶች ካሉበት ሕንድ አንስቶ እስከ እስፖኝ ምድር ያለውን የኩሽ ምድር ይጠቀልላል ይላል:: ግሪኮች፣የኢትዮጵያ ሃገር በኢንዱስና በጋንጅስ ወንዞች መካከል ያለውን ምድር ነው በማለት ይገልጹታል:: (Rosenmuller's Biblical Geography, BK III P. 154) እንደ ኤች ጂ ዌልስ(H.G.Wells) አባባል፣ በጥንት ዘመን ከሴም ወይም ከአርያን ቋንቋዎች ይልቅ የካም ቋንቋ በስፋትና በብዛት ይነገር እንደነበር ጠቅሷል(Outline of History, Vol. 1,P. 158) ::

ይህ ቋንቋ፣የኒሎቲክ ሕዝቦች ቋንቋ ሲሆን፣በዘመኑ የእስያን ምዕራብና ደቡብ ክፍል ያጠቃልል እንደነበረ ምናልባትም ድራቪዲያን ተብለው ከሚጠሩት የሕንድ ሕዝቦች ጋር ዝምድና ሳይኖራቸው እንደማይቀር



Scanned by CamScanner

የሄልዩሊቲክ ባህል ሕዝቦች ብሎ ከሚጠራቸው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ጆርጅ ኡልዩት ይናገራል::

እንደ ሰር ኤች ኤች ጆንሰን (Sir.H.H.Johnson) አባባል ዛሬ የማይነገረውና ጠፋ የሚባለው የካም ቋንቋ ተበታትነው ይገኙ በነበሩት በክሬት፤በሊዲያ፤በባስክ፤በከፍካዝ፤በድራቪዲያን፤በሱሜራያውያንና በኤላውያን ዘንድ ይነገር ነበር:: የባዛንታይኑ እስጢፋኖስ (Stephanus of Byzantium) እንደገለጸው፤ኢትዮጵያ በምድር የመጀመሪያዋ ሃገር ስትሆን የአምልኮተ ሥርዓትንና የመንግሥትን ሕግ የመሠረተች ናት:: በቀጣይ ዘመናት የተፈጠሩት መንግሥታት የሬፑብሊካዊ መንግሥት መሠረታዊ መርሆችን የወሰዱት ከኢትዮጵያ ነው:: መርሆዎቹም፤እኩልነት፤ መቻቻል፤ ሥራ፤ ዕውቀትና ፍትሕ ናቸው በማለት ገልጸታል::

የዘመናችን የታሪክ መጻሕፍት ግን በግብጽና በከለዳውያን የታሪክ ማህደራት ተመዝግበው ያለውን ምስክርነት ወደጐን በመተው ሌላ ንድፈ ሃሣብ በማቅረብ ግሪኮችና ዕብራውያን በመዛግብቶቻቸው ካሰፈሩት ሀቅ በተቃራኒ ሁኔታ የሰው ዘሮችን ሲመድቡ ይታያሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ስለጥንታውያኑ የሰው ዘር ግንኙነቶች ከግብጽ፤ከከለዳውያን፤ከግሪክ ስዎችና ምሁራን በተሻለ ሁኔታ ማን ሊመሰክር ይችላል? ምርምራቸው ጥልቀት የሌለው የዘመናችን ጸሐፍት ያልተገነዘቡት ጉዳይ ግሪክና ሮማ ከመነሳታቸው በፊት መላው የሜዲተራንያን ባህር የጠረፍ ከተሞችና ደሴቶቻቸው ሁሉ ኩሽ ኢትዮጵያውያን በመሠረቷቸው ድንቅ ከተሞች የተሞሉ እንደነበሩ ያለማወቃቸው ነው:: ግሪካውያንና ሮማውያን



አማልክቶቻችን ብለው እስከ ማምለክ ደርሰው የነበሩት የኩሽ ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ንግሥቲቶችን ነበር:: የተጎናፀፉት ድንቅ የሥራ ውጤቶች ልዩ ስለነበሩ በቀጣዩ ዘመናት በሕንድ፤በግብጽ፤በታናሽቱ እስያ በሜዴተራንያን ሃገሮችና በኢትዮጵያ ጭምር እንደ አምላክ ተቆጥረው ተመልከዋል::

ሁሉን አቀፍ የሆነ ጥናትና ምርምርን ያካሄደው ራውሊንሰን (Rawlinson) እንደተናገረው፤ዓለም ላለፉት ሦስት ሺህ ዘመናት ለተጐናጸፈችው ዕድገት፤የሴማውያንና የኢንዶ አውሮፓውያን ዘሮች ባለውለታ ሲያደርግ ይታያል፤ቀድሞ ግን እንደዚህ አልነበረም:: ግብጽና ባቢሎን እንዲሁም ምጽራይምና ናምሩድ ሁሉም የካም ዘር ግንድ ሲሆኑ፤የሰው ልጅ በሣይንስ፤በሥነ ጥበብ፤በሌሎችም መስኮች ላደረጋቸው ግስጋሴዎች ፈር ቀዳጆች ነበሩ:: በፊደላት መጻፍ፤በሥነ ከዋክብት ጥናት፤በታሪክ፤በዘመን አቆጣጠር፤በሥነ ሕንፃ፤በፕላስቲክ ጥበብ፤በቅርፃ ቅርጽ፤በባህር ጉዞ፤በእርሻና በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ረገድ ለተደረገው ዕድገት ምንጬ ከእነዚህ ሃገሮች በአንዱ አሊያም በሌላው ነበር::(Rawlinson's, Ancient Monarchies, Vol.I) እንስሳትን ለማዳ የማድረግ ጥበብ የነዚህ የቅድመ ታሪክ ሰዎች ውጤት ሲሆን፤በነበራቸው ክህሎትና ያላሰለሰ ጥረት ከወፍ ዘራሽ አዝዕርትና እፅዋት እንደ ስንዴ፤አጃ የመሳሰሉትንና ለዛሬው የእርሻ መሠረቶቻችን ግብአት የሆኑትን አስገኝተዋል:: ይህ ሥራ የተሠራበት ዘመን እጅግ

የራቀ ከመሆኑም የተነሳ እውነተኞቹ የአዝዕርትና የእጽዋት ዘሮች ዛሬ ስለመጥፋታቸው ይነገራል።

የጥንቱ ዘመን ፊሎሶፊ (Philosophy of Ancient History) በተባለው መጽሐፍ፤በንሰን(Bunsen) እንደጻፈውና ራውሊንሰን እንዳረጋገጠው፤የካም ዘር የሥልጣኔ መሠረት ነው ተብሎ ዋጋ ሊሰጠው ይገባል። ይህ ቤተሰብ ያካተተው፤ጥንታዊቷን ኢትዮጵያንና ግብጽን ቀደምት ከነዓናውያንንና የጥንት ከለዳውያንን ነበር። በከለዳውያን ሃውልቶች ላይ ተቀርፀው የተገኙት ጽሑፎች ያረጋገጡትም የነዚህን ሕዝቦች የዘር መቀራረብ ሲሆን፤መጽሐፍ ቅዱስም ይህንኑ ያረጋግጣል። የካምን ልጆች ኩሽ፤ምጽራይም፤ፉጥና ከነዓን ይላቸዋል፤ምጽራይም በግብጽ ኖረ፤ ከነዓን ደግሞ በአፍሪቃ፤ኩሽ ግን ግዛቱን በብዙ ሃገሮች አስፋፍቶ ነበር። (Philosphy of Ancient History. Bunsen P.52)

በንሰን እንደ ደመደመው፤የኩሽ ቅኝ ግዛቶች ይገኙ የነበሩት በእስያ ሃገራት ደቡባዊ ጠረፍና በአፍሪቃ፤እንዲሁም ከአርኪኦሎጂካል ቅሪቶች እንደተረጋገጠው በደቡባዊና ምስራቃዊ የአረብ ጠረፎች ሲሆን፤ኩሽ የሚለው ስም ለአራት ታላላቅ ግዛቶች ተሰጥቶ ነበር። እነዚህም፤ምድያ፤ፋርስ፤ ሱስንያና፤አሪያ ወይም በኢንዱስና በጤግሮስ ወንዞች መካከል ይገኝ ለነበረው ምድር ነበር። በአፍሪቃ ደግሞ ኢትዮጵያ፤ግብጽ፤ሊቢያ ሲሆኑ፤በተጨማሪ ከነዓናውያንና ፊንቃውያን በዚሁ የካም ዘር ግንድ ይካተታሉ። እነዚህ ጠይም ወይም ጥቁር ቆዳ ያላቸው ሕዝቦች የሥልጣኔያችን መገኛዎች ናቸው። በሰናዖር ሜዳ



ሰማይ ጠቀስ ሕንፃ የገነቡ፤በአባይ ተፋሰስ ከሜሮይ እስከ ሜምፊስ ከተማ ድረስ በታላላቅ የግንባታ ሥራ የታወቁ ነበሩ። በደቡባዊ አረብ ምድርም ድንቅ ሕንፃዎች የሠሩ፤በደቡብ ሳይቤሪያ ለሚታዩት ሃውልቶችና በአሜሪካም ምድር ከሚሲሲፒ ወንዝ እስከ ሜክሲኮ ብሎም እስከ ፔሩ ድረስ ተተክለው ለሚታዩት ትክል ድንጋዮች ባለቤቶች ናቸው። ይህ የኩሽ ኢትዮጵያውያን ኤምፓየር ሦስት ክፍለ አህጉራትን ያጠቃለለ ስለመሆኑ እንዲሁም የኢትዮጵያውያን ሥልጣኔ በጥንቱ ዘመን ባህል ላይ ያለጥርጥር ተጽዕኖ እንዳሳደረ በቅርብ ዘመናት ከተጻፉት ጥቂት የታሪክ መጻሕፍት መካከል ተገልጾ ይገኛል። ስለኢትዮጵያውያኑ ሲናገሩ፤ ጠይምና ቡናማ የቆዳ ቀለም ያላቸው ማሲጠራዊ የሆኑ የሄልዮሊቲክን ባህል የወከሉ ሰዎች ይሏቸዋል።

የኤሊዮት ስሚዝን(Eliot Smith) ጥናትና ምርምር ተመርኩዞ ዌልስ እንደመሰከረው፤ይህ የኩሽ ኢትዮጵያውያን ባህል ወደ መላው ዓለም ቀስ በቀስ መሠራጨት የጀመረው ከ1500 እስከ 1000 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ (ቅ.ል.ክ) ነበር። እንደርሱ አባባል በጥንት ዘመን በዓለም የታወቀና የላቀ ባህል ነበረው፤በዙሪያውም በርካታ የሰለጠነ ማህበረሰብን ያቀፈ ነበር። ባልድዊን በግልጽ እንዳረጋገጠው፤ዕብራውያን ጸሐፍት እነዚህን የመጀመሪያ የከተማ ነዋሪዎች ሥልጡን ኩሻውያን ይሏቸዋል። የጥንቱ የሃይማኖት ባህልና አፈታሪክ እንዲሁም ተቋማት ሁሉ ከዚሁ ከአንድ ምንጭ የተገኙ ነበሩ። ዓለም የግብጽንና የከለዳውያንን ሥልጣኔ ጥንታዊነት ቢቀበለውም፤ ችላ ያለው ግን ከሁሉም በፊት የነበረውንና ጥንታዊውን የኢትዮጵያን የላቀ ባህልና ፖለቲካዊ አደረጃጀት



Scanned by CamScanner

ነው::የኢትዮጵያን ጥንታዊነት በማረጋገጥ ረገድ ግብጻውያንና ከለዳውያን ጭምር በግልጽ የተቀበሉት ጉዳይ ሲሆን፣ መታወቅ ያለበት ጉዳይ በዛሬ የታሪክ መጽሐፍት ተጠቅሰው ያሉት ሃገራት የሥልጣኔ ምንጮች አለመሆናቸውን ነው። በተጨማሪ፤ መገንዘብ ያለብን የእስያ ሥልጣኔ ምንጩ ከቀይ ባህር አካባቢ ካለ የጥቁር ምድር መሆኑን ነው:: ይህንንም የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ከከለዳውያን ፍርስራሾች ውስጥ ተገኝተዋል::(Prehistoric Nations, Baldwin) ስለ ሕንድ ሥነ ጽሑፍ ጥናት በማድረግ የሚታወቀው ዊልፎርድ፣ኢትዮጵያን በተመለከተ ሳንስክሪት ተብለው በሚታወቁት የሕንዶች መጽሐፍት መጻፉን አረጋግጧል::

እንደጥንታዊው መጽሐፍ ጥሩና መሠረት፣ዓለም በሰባት ክፍል የተከፋፈለች ስትሆን፣ኢትዮጵያ፤ ኩሽ ዲዊፓ በመባል ስትጠራ በውስጧ አረቢያና ታናሽቱ እስያ፣ሶርያ፣ኑብያ፣አርመን፣ሜሶፖታሚያ፤በአፍሪቃ አህጉር ደግሞ ሰፋ ያሉ ቦታዎችን ያካተተች ነበረች:: እንደ ሳንስክሪት፣ ጽሑፎች ከተገኙት መረጃዎች ማረጋገጫነት በመነሳት ጥልቅ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ የታሪክ ሰዎች፣እነዚህ ሃገሮች እጅግ ጥንት በሆነው ዘመን ኃያል ሃብታምና የሰለጠኑ ስፍራዎች እንደ ነበሩ ጽፈዋል:: የቅርብ ዘመናት ታሪክ ጸሐፍት እንዳጣመሙት ሳይሆን፣በሴላ ዘር ስም የተካተቱት ሕዝቦች ሁሉ ኢትዮጵያውያን ተብለው ይጠሩ ነበር:: ብስለት የሌላቸው የዘመኑ የታሪክ ተማሪዎች ግን በመሰላቸው መንገድ ርዕስንና መደብ እየፈጠሩ ብሔሮችን ቢያካትቱም፣የኩሽ ሕዝቦች ማንነታቸውን



ለውጠው የማያውቁ ናቸው:: ፊንቂያውያን ተብለው ይጠሩ የነበሩ ሕዝቦች፣በክርስቶስ ልደት አካባቢ ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን ብለው ጠርተዋል፤ጥንታዊ ሪከርዶችና ጽሑፎች ሰማራውያንን ኩሾች ይሏቸው እንደነበር ይታወቃል::

ይህች ኢትዮጵያ የተባለች አስደናቂ ሃገር ኃይሏ ከመሰበሩ በፊት ለብዙ ሺህ ዘመናት የኖረች በመሆኗ የዘመናችን አጭር የታሪክ አቆጣጠር ታሪኳን አይወስነውም:: መጽሐፍ ቅዱስ ዘመናቶችን በአሃዝ ባያስቀምጥም ከዘፍጥረት አንስቶ ከቶ እኛ ልንረዳው የማንችለውን የእግዚአብሔርን የዘመን አቆጣጠር ይገልጻል:: የቅድመ ታሪክ ብሔሮች(Prehistoric Nations- Baldwin) በተባለው መጽሐፍና እንዲሁም በጥንታዊ መዛግብትና ማህደራት ውስጥ የኩሽ ቅኝ ግዛት በአባይ ሸለቆ መመሥረቱ ተዘግቧል:: ይህ የተባለው ዘመን ከ7 እስከ 8 ሺህ ቅ.ል.ክ አሊያም ከዚህ ቀደም ብሎ እንደነበረ፣በእነዚያ ዘመናት ኩሽ ኢትዮጵያውያን ሰፊ የኮሚኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋት የዓለምን ዳርቻዎች ለማገናኘት ስለመብቃታቸው ተገልጿል:: ሆሜር ከመወለዱ በፊት ይህ የኩሽ የበላይነት ቢያበቃም፣የተበታተኑት ማህበረሰቦች በግብጽ፣በደቡብ አረቢያ፣በፊንቂያና በሌሎችም ሀገሮች እንደነበሩ ታሪክ ያረጋግጣል:: (Prehistoric Nations, PP. 95-96)

ባልድዊን ሲገልጽ፤ ግብጽና ከለዳውያን እስኪተለያዩበት እስከ 5ሺህ ዓመት ቅ.ል.ክ ድረስ ኩሾች ተወዳዳሪ አልነበራቸውም:: ከ3500 እስከ



Scanned by CamScanner

3ሺህ ዓመት ቅ.ል.ክ መካከል ባለው ጊዜ የነበረው የንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥታዊ ሥርዓት ለመከፋፈል በቃ:: ለሺህዎች ዘመናት ፀንቶ የቆየው ይህ ታላቅ የኩሽ ኢምፓየር በምን ምክንያት እንደተከፋፈለ ባናውቅም፣ከጥፋት ውሃ በኋላ ለብዙ ሺህ ዘመናት ጸንቶ የቆየው ይህ ሥልጣኔ ይሆናል ተብሎ ይገመታል:: ግባውያን፣ሂምራውያንና ኢትዮጵያውያን የበላይነታቸውን ለብዙ ሺህ ዘመናት ጠብቀው ከቆዩ በኋላ በ1300 ቅ.ል.ክ ይህ ጥንታዊ ክብራቸው ወደቀ፤ይህም አሦራውያን ከመነሳታቸው በፊት ሲሆን፣ይኸውም የሴማውያን ነገዶች የሆኑ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ አርብቶ አደሮች የአረብን ባህረገብ ምድር ወረው ከመያዛቸው በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ነበር:: እንደ ዘመናችን የታሪክ ጸሐፍት አባባል ሳይሆን፣ ዛሬ መካከለኛው ምስራቅ ተብሎ የሚጠራውን ስፍራ፤ በድል አድራጊነት ይዘው የነበሩት የጥንት ኩሻዊ አረቦች እንጂ ሴማዊ አረቦች አልነበሩም:: የአሦር መንግሥትም ከተነሣ በኋላ የግብጽ የበላይ በመሆን በዓለም ኤምፓየር ደረጃ ኃያልና ዓለም አቀፍ ውክልና ይዘው ለሺህዎች ዘመናት የቆዩት ኩሽ ኢትዮጲያውያን ብቻ ነበሩ:: ይህን የመሰለ ግዙፍ ጥላ ለማጥላት የቻለ ዘር ማን ይሆን?

«የአረቢያ ምሽቶች» በመባል የሚታወቁት ትረካዎችን ስናነብ፣ልብን የሚሰቅሉና ደስ የሚያሰኙን እውነትም መስለውን የምናነባቸው ናቸው። እነዚህ ስዕላዊ ትረካዎች፣በዘመኑ የኩሽ ሥልጣኔ ዓለም አቀፋዊ የንግድ እንቅስቃሴ ይዘትን የሚያስቃኙ ሲሆኑ፣ወቅቱ የኢትዮጵያ ዝና ቀስ በቀስ እየተዳከመ የሄደበትን ዘመን የሚያመላክቱ ነበር:: በትረካዎቹ የሚጠቀሱት እንደ ሕንድ፣ፋርስ፣ አረቢያና ከለዳውያን ተብለው የሚጠሩት ሕዝቦች በዋነኛነት ኩሻዊ ሲሆኑ፣ዘመኑ የወርቅና የብር ዘመናት የተባለበት ማብቂያ ላይ ነበር:: አርኪኦሎጂካዊ ምርምሮችም ይህ የተባለው ዘመን እንደነበረ አረጋግጠዋል:: በአረቢያ ምሽቶች የተነገሩት ትረካዎች ድንቅና ስሜትን የሚማርኩ ናቸው:: ትረካዎቹም እንዲያው ለማዝናናት የተፈጠሩ አልነበሩም:: በትረካዎቹ ውስጥ ያሉትን እንደ ጂንና እስመህበ አልቦ ነገር የሚከሰቱ ፍጡራንን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው ይዘቱን ብናጤን የሚገልጽልን ጉዳይ አንድ እጅግ ኃያል ስለነበረ አንድ ጥንታዊ ሥልጣኔ የመኖሩን ጉዳይ ነው:: የዚህ ማረጋገጫ፣ዛሬ በጥንታዊቷ ከለዳውያን ምድር፣በግብጽ በአረቢያና በሜዲተራንያን ጠረፎች እየተገኙ ያሉት ማስረጃዎች ናቸው::

ሂረን(Heeren)በምርምር ውጤቱ እንደገለጸውና የዘመናችን ታሪክ ጸሐፍት እንዳቀረቡት መረጃ መሠረት፣ከጥንት ዘመናት አንስቶ እስከ ዘመናችን ድረስ ኢትዮጵያውያን እጅግ የተከበሩና በዚያው መጠን በምስጢር የተሞሉ ሕዝቦችም ናቸው ብሏል:: ኢትዮጵያውያን በሥልጣኔያቸው ከሚጠሩት የጥንት ሕዝቦች ባህልና ወግ ውስጥ ስማቸው የታወቀ ነው:: የግብጽ ካህናት መዛግብት ስለኢትዮጵያውያን ጉዳይ የተሞሉ ናቸው:: በታናሽቱ እስያ፣በኤፍራጥስና በጤግሮስ ወንዞች መካከል ያሉት ሕዝቦች፣የኢትዮጵያን ልብ ወለድ ትረካዎች ከራሳቸው ወግ ጋር በማስተሳሰር፣ውጊያዎቻቸውንና የጦር ድሎቻቸውን እንደራሳቸው ጀግኖች ገድል አድርገው ገልጸውበታል፤ግሪኮችም እንደዚሁ::



Scanned by CamScanner

ዳዩንሰስ(Dionysus)፣ሄርኩለስ(Hercules)፣ሳተርንና(Saturn)ኦሲሪስ(Osiris) ዚየስና(Zeus) አፖሎ(Apollo) የተባሉት የቅድመ ታሪክ የኩሽ ዘር ነገሥታት ስሞች ነበሩ። በእነዚህ በተከበሩ ኢትዮጵያውያንና በሌሎቹም ስም ዙሪያ የሜዲተራኒያንና የምስራቅ ሕዝቦች አፈታሪኮቻቸውን አዋህደውበታል። ስለሆነም፣ የጥንቱን ዓለም አኗኗር ስርዓት፣ሥነ ጽሑፍና ኪነት በእጅጉ የደመቀ በማድረጋቸው ሲታወሱ ኖረዋል።

ጥንታውያኑ ቅርጻ ቅርጾች፤ስዕላትና ድራማዎች የቅድመ ታሪክ ኩሾች ድንቅ የሥራ ውጤቶች ሲሆኑ፣የግሪክና የሮማውያን ሥነ ጽሑፍና ሙዚቃ የኢትዮጵያውያን ተጽእኖ ቀስ በቀስ እንዳረሰረሰው ይታያል። በሃሣብም ሆነ በቅርጽ ይህ የኩሽ ኢትዮጵያውያን ሥራ በዘመናችን ኪነት ውስጥ የበላይነቱን እንደያዘ ይገኛል። ግሪኮች፣ ኢጣልያንና ሲሲሊን ሳያውቁ በየግጥሞቻቸውና በየዘፈኖቻቸው በየጫወታቸው ኢትዮጵያውያንን «እጅግ ሩቅ በሆነ ምድር የሚኖሩ፣ፍትሐዊ ሕዝቦች፣ በአማልክቶች የተወደዱና የተመረጡ፤ ከእነርሱ ጋር ለመገናኘትና በዓላቶቻቸውን ለማክበር የኦሎምፒያ ሰዎች ወደ እነርሱ ይጓዙ የነበር፤ያቀርቧቸው የነበረው መስዋእት ከሰው ልጆች ሁሉ በአምላክ የተወደደላቸው።» በማለት ያሞግሷቸው እንደነበር ሂረን ጽፎአል ። አሁንስ ቢሆን ኢትዮጵያውያንን በመደነቅና በመገረም የማይመለከታቸው ማነው? ግልጽና ጥንቁቅ የሆኑ የታሪክ ሰዎች ኢትዮጵያውያን በሥልጣኔና በዕውቀት እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው እንደነበር አስረግጠው ይመሰክሩላቸዋል።



# ምዕራፍ ሁለት
## ጥንታዊቱ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ

ዘመኑ እጅግ በመራቁ የተነሣ የጥንታዊቱ ኢትዮጵያ ኢምፖየር መዲና የት እንደነበር በርግጥ ለማወቅ አዳጋች ነው። እንደ ቦካርት አባባል፣አረብ ምድር ሆኖ ከዚህ ማዕከል የኩሽ ዘር ወደ ምስራቅና ምዕራብ ተዛመተ ይላል። እንደ ጌሴኒየስ አባባል፣መዲናዋ በአፍሪቃ ነበር። ግሪኮች ደግሞ፣የጥንታዊት ኢትዮጵያ ቦታ በላይኛው አባይ ሲሆን፣የሰው ዘር መገኛ በዚሁ ሥፍራ ነው ይላሉ። የገነትም የአትክልት ሥፍራ በዚህ አካባቢ ይሆናል በሚል እምነት ፍለጋም አካሂደው ነበር። ሥነ ጥበብ፣ ወግና ሥርዓት በላይኛው አባይ ሸለቆ ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች መንጭቶ ወደ ቅኝ ግዛቶች እንደተስፋፋ ይነገራል። ግብጻውያን ሥልጣኔንና ሃይማኖትን ከኢትዮጵያውያን ስለተቀበሉት ከራሳቸው የሆነ ኦርጅናሌ ነገር የላቸውም፤እንዲያማ ባይሆን ኖሮ ላለፉት 3ሺህ ዘመናት የግብጽ ካህናቶች ስለተከተሉት ሃይማኖት ምንነትና እውነተኛ ትርጉም ባውቁ ነበር ይላሉ ግሪኮች። (Budge, Osiris and the Egyptian Resurrection - Preface) በጅ እንደሚገልጸው የግብጻውያን አምልኮተ ሥርዓት በኑብያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታወቅና በተግባርም የዋለ ሲሆን፣የግብጽ ተራው ሕዝብ ግን የሃይማኖቱንና የእምነቱን ሚስጢር በትክክል ተረድቶት ባለማወቁ የተነሳ የእምነቱን ስርኣት ቀስ በቀስ እየተወው ሄዷዋል።



Scanned by CamScanner

እንደ የፐቶሎማይክ(Ptolemaic) ጸሐፍት አገላለጽ ግብጽ፤ከኢትዮጵያው አባይ ወንዝ በተወሰደ አፈርና ጭቃ የተመሠረተች ሃገር ናት። በምድሯ የኖሩት የመጀመሪያዋ አቅኝዎችዋ ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ሥርዓተ መስዋዕትንና አምልኮን በማስተማር ረገድ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ናቸው። ግብጽ፤በኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ስር በነበረችበት ወቅት በሁለቱም ምድሮች የነበረው ሕግና ጽሑፍ አንድ ዓይነት የነበረ ለመሆኑና ሃይሮግሊፊክ ተብሎ የሚታወቀውን ፊደል ከግብጻውያኑ ይልቅ ተራው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያውቀውና የሚያነበውም እንደነበር ይታወቃል(Diodorus Siculus, bk. IIII,ch.3)። በዚህም የተነሳ የጽሑፍ ዕውቀትን ኢትዮጵያውያን ሲጠቀሙበት፣በግብጻውያን ዘንድ ከካህናቶቿ በስተቀር ሌላው ሕዝብ የሚያውቀው አልነበረም። ይህ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኝ የነበረው የሜሮዲያዊ ጽሑፍ በግብጽ ግዛት ከመጀመሪያው ፏፏቴ በስተሰሜን ባለው ምድርና በኑብያ ውስጥ ደግሞ ከሶባ በስተደቡብ አይታወቅም። ለዚህ ምክንያቱ በቅኝ ገዥው ና በተገዥው መካከል ልዩነትን ለማሳየት ይሆናል።ሄሮዶተስ እንደዘገበው (bk.II,P.29) ሜሮይ፣ታላቅና ዘመናዊ ከተማ የነበረች፣ሁሉም ሕንጻዎቿ ከቀይ ሸክላ ጡብ የተገነቡ ነበሩ።(Meroe - Crowfoot, PP. 6,30).

እንደ ሣይክሎፒዲያ ኦፍ ቢብሊካል ሊትሬቸር(Cyclopedia of Biblical Literature) አባባል፣የቅኝ ገዥው ቡድን በካህናቱ አማካኝነት ወደ ግብጽ የገባው ከሜሮይ ነበር። በጥንታዊት ኢትዮጵያ ግዛቶች የሚገኙት



ጥንታዊ ሃውልቶች በአጽንኦት የሚያረጋግጡት ይህንኑ ሲሆን፣ዳዩደረስ ሲኩለስ እንደ ዘገበው ደግሞ፣ዚየስ፣አሞንና ኦሲሪስ እንደ አማልክት ተቆጥረው በሜሮይ ከተማ ይከበሩ ነበር። በሌላ በኩል ንግድ፣ሣይንስና ሥነ ጥበባት ከላይኛው አባይ ወደ ግብጽ ስለመዛመታቸው ማረጋገጫዎች አሉ። ሄሮደተስ፤ኢትዮጵያውያንን ሲገልጽ፣ «የላይኛውን አባይ የሚቆጣጠሩ ብልህ ሰዎች፣ ዕድሜያቸው የረዘመ፣ ባህላቸው ሥርዓታቸውና ሥነ ምግባራቸው በወርቃማው ዘመን ሰዎች የተመሰለ፣በዓላቶቻቸውና ግብዣዎቻቸው በራሱ በጁፒተር የተከበሩ» ብሏል። በዘመነ ግሪክ፤ ግብጽ፣ኢትዮጵያን እንደ ፍጹማዊ መንግሥት አድርጋ ትመለከታት የነበረች ሲሆን፣ፑራና የተባሉት የሕንድ ጥንታዊ የታሪክ መጽሐፍት ደግሞ ኢትዮጵያን ከግብጽ በፊት የነበረችና ሥልጣኔዋም ከግብጽ የቀደመ በማለት ይጠቅሷታል። በሣንስክሪት መጽሐፍት ውስጥ በሕንድ ሕዝቦች እስከ«መመለክ» ደረጃ ደርሰው ስለነበሩት የኩሽ ነገሥታት ስም ዝርዝር ከመጠቀሱም ባሻገር፣ግሪኮችና ሮማውያን እነዚህን ስሞች በመውረስና በሚያመቻቸው መንገድ በመለወጥ የሕዝባቸውን ስሜት ለማርካት ሲጠቀሙበት ኖረዋል።

የሕንድ ፑራና መጽሓፍት የሚገልጹት፣ኩሾቹ ወደ ግብጽ ከመዝለቃቸው በፊት ወደ ሕንድ በመጀመሪያ የመግባታቸው ጉዳይ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ሥልጣኔያቸው ከከለዳውያንና ከአባይ ምድር ሕዝቦች ጋር እኩል ዕድሜ እንዳለው ይናገራሉ። እንደ መጽሐፍቱ አባባል፤ግብጽ፣ከኩሽ ድዊፖ አጠቃላይ ግዛት አንዷ ስትሆን ፖሊ የተባለችው ቅኝ ግዛት ደግሞ



Scanned by CamScanner

ፊንቃያውያን የተባሉ ሕዝቦች የተገኙባት የኩሽ ምድር ነበረች። የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ መዲና በዘመናችን ሜሮይ ተብላ ትጠራ የነበረችው ስትሆን፣ከእርሷ በፊት የነበረችው ሜሩ ትባል ነበር። ሊኖርማንት ጥንታውያኑን ሰዎች የሜሩ ሰዎች ይላቸዋል። የሳንስክሪት ጸሐፍት ደግሞ፣የሜሩን ንጉሥ የሕንድ ዋናው አምላክ ነበር የሚሉት። ይህም የሚገልጸው፣የሕንድ የመጀመሪያዋ ቅኝ ገዥ ኢትዮጵያ መሆናኗ ሲሆን፣የቀደምት ታሪክ ጸሐፍት እንደሚሉት፣በሁለቱ ሃገሮችና ሕዝቦች መካከል የሚታየው የፊት ገጽታና የቆዳ ቀለም የመመሳሰል ጉዳይ ይህንኑ ሃሣብ ያጠናክራል።

በጥንታውያኑ መጽሐፍት መሰረት ግዛቱን በሦስት አህጉራት አስፋፍቶ ስለነበረውና ዴቫ ናሁሻ ስለተባለው ሌላው የሜሩ ንጉሥ ሥራዎች ተገልፆአል። በታናሽቱ እስያ የነበሩና ዛሬ የጠፉ ሥነ ጽሑፎች፣ የኢትዮጵያ የበላይነት በክልሉ መስፋፋቱን አስመልክተው ያሉት ብዙ ነገር አለ። እጅግ ጥንታዊ በሆነ ፊደልና ቋንቋ ተጽፎ የተገኘው "ፍርጊያ" የተባለው የጥንት ዘመን ግጥም፣ዳዩኒሰስ ተብሎ ይጠራ ስለነበረ ስለ አንድ የተከበረ ኢትዮጵያዊ የተገጠመ ሲሆን፣ባልድዊን እንደሚለው፣ስለዚህ ሰው የሚገልጹ መጻሕፍት ንጉሥ ሜኑስ ከመነሳቱና ሄለናውያን ከመምጣታቸው በፊት ጠፍተዋል።ጥንታውያኑ ግሪኮች፣የዳዩኒሰስን ታሪክ በማዛባት ለካራሙ የ«ወይን ጠጅ አምላክ» በማድረግ አቅርበውታል። የሚገርመው፣የኩሾቹን ትውፊት መረዳት በተሳናቸው ቁጥር ታሪክን በመሰላቸው መንገድ እያጣመሙና እያዛቡ

ለራሳቸው ፍላጐት ማርኪያ የመጠቀማቸው ጉዳይ ነው። "ኢትዮጲስ" በሚል ስያሜ የሚታወቀው ግጥም፣በታናሽቱ እስያ ጠረፍ የነበረችውን የትሮይን ከተማ ለማስመለስ ስለተደረገው ውጊያ ሲሆን፣በዚህ ጦርነት ኩሽ ኢትዮጵያውያን በታላቅ ጀግንነት ስለመዋጋታቸው የሚዘክር ነበር። ጦርነቱ ግን የግብጻውያን ጦርነት ተደርጐ ቀርቧል።

በዚያ የጥንት ዘመን፣ግብጽ፣በኢትዮጵያ አገዛዝ ሥር እንደነበረች የሚያስረዱ መረጃዎቹ አሉ። ይህንን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ነቢዩ ኢሣይያስ ኢትዮጵያና ግብጽ የተቀራረበ ግንኙነት እንደነበራቸው ጠቅሷል። የግብጽ ብሔራዊና ንጉሣዊ ቤተሰብ ይባል የነበረው በዋነኛነት የኢትዮጵያውያን ስም የነበረው ከመሆኑም ባሻገር፣ ከኢትዮጵያ መዲና የግብጽ አስተዳደር ይመራ እንደነበር አሳማኝ መረጃዎች አሉ። ኢትዮጵያ፣ከግብጽ ጋር ባደረገቻቸው ጦርነቶች የተዳከመችበትም ጊዜ እንደነበር ሁሉ አንዴ ስታስገብር አንዳንዴም ስትገብር ኖራለች። የዘመናችን መጽሐፍት ስለነዚህ ጉዳዮች በጣም ጥቂት መረጃዎች አሏቸው፣በተለይ የላይኛው አባይ ምድርን አስመልክቶ። ሆኖም ግን፣ ያረጁና ያፈጁ መጽሐፍት ሲገለጡ፣ስለድንቅ ኩሽ ኢትዮጵያውያን የተሞሉ ታሪኮችን ያካተቱ ናቸው። ጥንታውያኑ በመጽሐፍቶቻቸው ውስጥ በግብጽ ሰፍረው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ስለመሆናቸው አስረግጠው እየተናገሩ፣እኛ ከእነርሱ ምስክርነት ሌላ መስጠት እንደምን እንችላለን?። ፊክሉስ፣ "የደጋው ክፍል የጥቁር አባይ ነዋሪዎች ስለአለፈው አንፀባራቂ ገድላቸው ይገነዘባሉ፣ራሳቸውንም

በኩራት ኢትዮጵያዊ በማለት ይጠራሉ በማለት ጽፏል። ሬክለስ፣በአባይ ወንዝና በባህረ ኤርትራ መካከል የሚገኘውን የባለ ሃብት ማዕዘንማ ስፍራን የኢትዮጵያ ዋና ምድር ብሎታል። ይህ ተራራማ ምድር ከዓለም ለየት ያለ ቀስታሽ ብርሃን የፈለቀበት፣ጮራው ለመጭዎቹ ብሔሮች የፈነጠቀበት ስፍራ ነው ይላል። ለጥቆም ሲጠይቅ፣በዙሪያዋ የከበቧትን አስፈሪና እንደ እሳት የሚፋጁ በረሃዎችን አልፎ ዝናዋ እንዴት በዓለም ሊናኝ ቻለ? ወደእርሷስ ለመቅረብ የከጀሉትን እንዳይችሉ አድርጎ ያገዳቸው የማይታየው አጥር ምንድን ነው? እንደ ሂረን ግምት ደግሞ፣ከቶም የማይመሳሰሉና የተራራቁ እጅግ በርካታ ብሔሮችና ሕዝቦች ኢትዮጵያውያን ተብለው ተጠርተዋል፣ቢሆንም ግን በአፍሪቃ ምድር ከታሪክ አኳያ እንደ ኢትዮጵያና ግብጽ ትኩረትን የሚስብ የለም።

ሂረን እንደሚለው፣ኢትዮጵያውያን ጥቁር ቆዳ ያለውን የሰው ዘር በመወከል ይታወቃሉ።(Heeren's Historical Research - Ethiopian Nations, ch. 1, P. 46) የኩሽ የማይናቀው በርካታው ቁጥር በአፍሪቃ እንደሚኖር ሁሉ የዚህ ዘር ተቀጥላ በእስያ ለመኖሩ ማስረጃዎች አሉ ይላል። በፋርስ ዘመነ መንግሥት፣ኢትዮጵያ ራሷን የቻለችና ተሰሚነት የነበራት ሃገርና መንግሥት የነበረች ስለ መሆንዋና፣ካምቢሰስ የተባለው የፋርስ ንጉሥ ኢትዮጵያን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ብዙ ጊዜ ሙከራ አድርጎ ሙከራዎቹ ሁሉም ከንቱ ሆነው ስለመቅረታቸው ታሪክ ዘግቧል። ሮዜሊኒ(Rosellini)እንደሚለው፣ግብጽን በንጉሥነት ያስተዳድሯት ከነበሩት ኢትዮጵያውያን ነገሥታት መካከል ንጉሥ ሳባኮና ንጉሥ



ቲርሃቅ፣ በግብጽ ዙፋን ላይ የተቀመጡት በወራሴ መንግሥት የዘር ግንድ ውስጥ በመቆጠራቸው እንጂ በሴራ ወይም በጦር መሣሪያ አመጽ ያገኙት ሥልጣን እንዳልነበረ ገልጿል። ከእነርሱ መነሳት በፊት ተቀርጸው በነበሩት ሀውልቶች ላይ ተስለው የተገኙት ስዕላት የሚገልጹት ነገር ቢኖር ስለ ኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ነው።

ኢትዮጵያውያን፣በዚያ ጥንት ዘመን በሕንጻ ጥበብ የተካኑ እንደነበሩ፣ ፒራሚዶቹንም ለመስራት የዋለው የመሠረት ድንጋይ የተወሰደው ከኢትዮጵያ ስለመሆኑ፣የፒራሚዶቹን አቀማመጥና ቅርጽ ለተመለከተ ሃይማኖታዊና ሥነ ከዋክብታዊ ሚስጢርን ያዘሉ ስለመሆናቸው ብዙ ይባላል። ዱብዋ እንደጠቀሰውና ከላይኛው አባይ እንደተገኘው መረጃ መሠረት፣ጥቁር ቀለም ያላቸው ካህናት ቀይማ መልክ ለነበራቸው ስዎች ስለመሣሪያዎችና ስለምልክቶች ሲገልጹላቸው ያሳያል ብሏል። እነዚህ ጠበብት ኩሾች፣የተቀደሰ የካህናት ዘር ተብለው ተጠርተዋል።የኩሽ ኢትዮጵያውያን ሃይማኖት፣ጥንትም ቢሆን ለየት ያለና አስገራሚም ነበር። ሰውንም ጭምር በመስዋዕትነት ያቀርቡ ነበር ተብሎ ይነገራል። ይህ ሥርዓት እስከ ግሪክና ሮማውያን ዘመነ መንግሥት ድረስ ለመዝለቁ ዶውድ ሲገልጽ፣አፍሪቃዊው ውድና ቅርብ የሆነውን ዘመዱን ለመስዋዕትነት ያቀርብ የነበረው ከጥላቻ በመነጨ ድርጊት ሳይሆን ለፈጣሪው ካለው ፍቅር የተነሣ ነበር ብሏል። ብዙ የተነገረለት ይህ የካህናት ወገን፣ከግብጽ ይልቅ በላይኛው አባይ ተሰሚነቱ ከፍተኛ በነበረበት ወቅት፣ከግብጽ በመውጣት ወደ ናፓታ በተመለሰ ጊዜ የታችኛ



Scanned by CamScanner

ው ግብጽ ሕዝብ ሃይማኖቱ ትርጉም አልባ ሆነ፤ከኢትዮጵያ በመለየቱ የተነሳ ቋንቋውም ጭምር እየተዳከመ ሄደ::

የኑብያን ግዛት ለሚጎበኝ ሰው የሚገነዘበው ጉዳይ፣ነዋሪዎቹ ከግብጻውያን ተራ ሰዎች ይልቅ በብዙ መንገድ የሚለዩ ስለመሆናቸው ሲሆን፤ባራብራዎች አለያም ደግሞ የአባይ ኑብያኖች የሚባሉት በዘመናቸው እስከ ግብጽ የተንሰራፉ እንደነበሩ ይነገራል:: እንደ ባኤዴከር(Baedecker) አባባል ኑብያኖቹ ጠንካራና ጡንቻማ አርሶ አደሮች ናቸው:: ከግብጻውያኑ ይልቅ ጉልበተኞችና ጠረኞች ይላቸዋል:: እንደ ኬን (Keane) አገላለጽ ደግሞ፣ኑብያኖቹ በሞራል ደረጃም ቢሆን የላቁ፤ባለ ወፍራም ከንፈር፣ፊካ ያሉ ዓይኖች ያሏቸውና የራስ ቅሎቻቸው ቅርጽ ጠባብ የሆኑ ኒግሮይድ ይላቸዋል:: አንድን የሰው ዘር ከሌላው ዘር ለመለየት በቆዳ ቀለም ላይ ከመመርኮዝ ይልቅ በራስ ቅል ቅርጽ አቀማመጥ ላይ ተንተርሶ መግለጽ ይቻላል ይባላል:: የታርታር ዘር የራስ ቅል ፍጹም ክብ ሲሆን፣የኢትዮጵያውያን ራስ ቅል አቀማመጥ ደግሞ ሞላላ ነው:: የአውሮፖውያኑ ግን በሁለቱ መካከል አማካይ ነው:: አንድ ዘር ከሌላው ካልተደባለቀ በቀር የመጀመሪያ ፍጥረቱን አይቀይርም ተብሎ ይታመናል:: እንደ ኬን ድምደማ፤ባራብራ የተባሉት የኑብያ ሰዎች፤ችምችም ያለ የራስ ፀጉር የነበራቸው፣እምብዛም ጢም የማይታይባቸው፤ በግብጽ ቤተ መቅደስ ግድግዳዎች ላይ ምስሎቻቸው ተስለው የተገኙት ናቸው:: የጥንታዊ ኩሽ ኤምፖየር ሰዎች ገጽታ ይሄን ይመስል ነበር ይባላል::



እንደ ስትራቦ (Strabo) አጠራር ኑብያዊ በአባይ በስተምዕራብ በኩል የነበረ ታላቅ ዘር ሲሆን፣ የፈለሰውም ከ2 ሺህ ዓመታት በፊት ኮርዶፋን ከተባለ ስፍራ ነው የሚል እምነት አለ:: ነዋሪዎቹ ኑባ የተባለውን ስም አይቀበሉትም፣ምክንያቱም ባሪያ ከሚለው ቃል ጋር የተዛመደ በመሆኑ፤ኑባ ተብለው ከመጠራት ይልቅ ባራብራ ተብለው ጥንት በሚጠሩበት ስም ራሳቸውን ይጠራሉ:: ባራብራዎች በመልካቸውና በገጽታቸው ላይ በዘመናት ብዛት ለውጥ ቢያሳዩም ኒግሮይድ ናቸው:: በግብጻውያን ሃውልቶች ላይ ተስለው ከሚታዮትና «ዋዋ» ከሚባሉት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ናቸው:: የቀደምት ግብጻውያን መልክ «ረቱ» በሚል አጠራር ይታወቃል ደኀራዊኑ ግብጻውያን ግን ከኢትዮጵያውያን ጋር በመደባለቃቸው የተነሣ መልካቸው እንደክልስ ይመስል ነበር:: የዋዋዎቹን(Wawa) ኩሻዊ መሆን የሚገልጹ መረጃዎች በግብጽ ሃውልቶች ላይ ከ5ሺህ ዓመታት በፊት ተጽፈው መገኘታቸው ይታወቃል:: ይህም የሚያመለክተው ግብጻውያን ዋዋዎች ከ6 ሺህ ዓመታት በፊት ከሌላ የሰው ዘር ጋር የመደባለቃቸውን ጉዳይ የሚያመለክት ነው:: የጥንት ግብጽ ነገሥታት የፊት ገጽታ ሉተመለከተ ከኢትዮጵያዊ መልክ ጋር መመሳሰሉን ያሳያል ሆኖም ግን ቀስ በቀስ በጋብቻ ትስስር የተነሣ የእስያውያን ገጽታ ወደማሳየት ተቀይሯል:: በተጨማሪ ሊዘነጋ የማይገባ ጉዳይ ቢኖር፣ለቆዳ ቀለም መጥቆር ዐብይኛው አባይ አካባቢ ያለው የፀሐይ ንዳድ አስተዋጽኦ እንደነበረው ነው::



Scanned by CamScanner

የፒፒ 1ኛን ዘመቻዎች በተመለከተ ተቀርጸው የተገኙት ጽሑፎች በግብጽ ደብባዊ ድንበር የነበሩትን ሕዝቦች ኔግሮይድ ማለቱ አንዳንድ ፀሐፊዎችን ግራ አጋብቷል:: ምክንያቱም እነዚህ ሕዝቦች መንግሥት ከመመስረቱ በፊት የነበሩ፣የጥንቱ ዘር ሰዎች የሆኑና ከመጀመሪያዎቹ የኩሽ ዝርያዎችም የሚመደቡ የመጀመሪያው የአሲቢኒያ አቦርጅናሌ ዘር ስለመሆናቸው የሚታወቅ ጉዳይ በመሆኑ ነው:: በግብጽ ታላቁ ስፊንክስ ሃውልት ላይ ተቀርጾ የሚታየው የኬኦፕስ (Cheops) የፊት ገጽታ ለዚሁ ማረጋገጫ ነው:: የግብጻውያንን የታሪክ መጽሐፍት ወስዳችሁ የነገሥታቶቻቸው ምስል ያሉበትን ገጾች ብትመለከቱ ያለአንዳች ጥርጥር ኢትዮጵያዊ ገጽታን ትመለከታላችሁ:: ይህ የቀደምት ዘር በግብጽ ሃውልቶች ላይ አጉ ተብሎ ይጠራል:: ይህም የኑብያኖቹ ቅድመ አያቶች በግብጽ ምድር የገዥው ዘርና መደብ እንደነበሩ አመላካች ነው:: በ1892 ዓ.ም ፔትሪ፣ለብሪቲሽ አሶሲየሽን ከ3ኛውና ከ4ኛው የግብጽ ሥርወ መንግሥታት ዘመን የሆኑና ለእይታ ያቀረባቸው የራስ ቅሎችን ያለጥርጥር የኔግሮይድ መልክ ይታይባቸዋል በማለት ይገልጻል:: ስለ ራስ ቅሎቹ ዶልቶሴፋሊክ ወይም ሞላላ መሆናቸውንም ይናገራል:: ሆኖም ግን የአርኪኦሎጂ ግኝቶች በየጊዜው እየገለጹልን ያሉት መረጃዎች፣ግብጽ በቅድመ ታሪኳ ሙሉ በሙሉ ኩሻዊ ስለመሆኗ እንጂ ዛሬ ታሪክ ጸሐፍት እንደሚመድቡት ከያፌት ዘር ቅርንጫፍ እንዳልመጡ ያረጋግጣል::



እንደ አንዳንድ ግብጻውያን አባባል እነርሱም ሆኑ የቀድሞ ሃይማኖታቸው የተገኘው ከፑንት ላንድ ነው:: ፑንትላንድ፣ዛሬ ሁሉም እንደሚያውቀው ከኑብያ ደቡብ የምትገኝ የሶማሌ ምድር ናት፡ የፑንትላንድ ንግሥሥ ሚስት ከመቀመጫዋ ሰፋ ያለች ባለዳሌ ነበረች፣ንጉሡ ደግሞ የኩሽ ዘር ገጽታ ነበረው:: በፑንትላንድ፣የወርቅ አንባሮች፣የዝሆን ጥርሶች፣ ኤቦኒና ሌሎች ምርቶች እንደልብ ከመገኘታቸውም ባሻገር ሌላ የምትታወቅበት ለአምልኮትና ለቀብር ሥርዓት በብዛት ይውል በነበረው በዕጣን ምርቷ ነው:: በዕጣን ንግድ ታዋቂ እንደነበረች የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በአፍሪቃ አህጉር በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በሐማት ሸለቆ ካሉ ፍርስራሾችና አለቶች ላይ ተቀርፀው ተገኝተዋል:: መረጃዎቹ የሚገልጹት 2ሺህ ዓመት ቅ.ል.ክ. በቴባድ ከተማ የተሰበሰበ ግብረ ኃይል፣ከፑንትላንድ ዕጣን ለማምጣት ስለአደረገው ጉዞ ይገልጻል:: በቴብስ ቤተ መቅደስ ውስጥ በውብ ሁኔታ የተሳለ ስዕል በ1600 ዓመት ቅ.ል.ክ ለተመሳሳይ ዓላማ የተደረገን ጉዞ ያሳያል::

የጦር ሠራዊቱን በተመለከተ ጥቂር ኑብያኖች ያሉበት ባታሊዮን በዛሬይቱ ግብጽ እንኳዋን ጠንካራ ነው ይባላል:: በጥንቱ ዘመን ደግሞ ኢትዮጵያውያን የግብጽ የጦር መሪዎች እንደነበሩ ማስረጃዎች አሉ:: ይህም የጦር መሪነት ዛሬም በደማቸው ስለመኖሩ ይነገራል:: ኩሾች በዚያን ዘመን፣የግብጽ ጦር ኃይል የጀርባ አጥንት የሆኑበት ምክንያት በግብጻውያን ዘንድ የተዋጊነት ብቃትና ችሎታ ስለመኖሩ ሊሆን፣የግብጽ

ድል ሁልጊዜም በእነዚህ ኩሾች የአመራር ችሎታ የተገኘ እንዲሁም የኩሽ ኢምፖየርም ወደ ምስራቅና ምዕራብ በቅኝ ገዥነት ለመስፋፋት የቻለው በእነዚሁ ኩሾቹ የተዋጊነት ብቃት እንደነበር መገመት ይቻላል:: በመላው አረቢያና በደቡብ ምዕራብ እስያ ብሎም በመካከለኛው ደጋዎች በታላላቅ አለቶች ላይ ተስለውና ተቀርፀው የተገኙት ማስረጃዎች ድምፅ የለሽ ምስክርነታቸውን የሰጡት ኢትዮጵያውያን በግብጽ የጦር አዛዥነትን ደረጃ ተቀዳጅተው እንደነበሩ ሲሆን፣እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሰዎች ለጦሩ የስንቅና የትጥቅ ድጋፍ ለመስጠት ይከተሉት እንደነበር ከጥንቱ የታሪክ ማህደራት ለማረጋገጥ ይቻላል። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ኢምፖየር ከጽንፍ እስከ አጽናፍ የነገሠበትና ኃይሏም የገነነበት ዘመን በመሆኑ ነገሩ ላያስደንቅ ይችል ይሆናል::

የዛሬይቱን ግብጽ፤ነዋሪዎች ስንመለከት ከጥንቶቹ በጣም ተለውጠዋል፣ ምክንያቱም ሄሮደተስ በጎበኛቸው ዘመን ጥቁሮች ነበሩ:: እንደ ሬክሉስ (Reclus) አባባል፣የጥቁር የበላይነት ስሜት ያላቸው ኑብያኖች ግብጻውያንን ከመናቃቸው የተነሳ ዛሬም እንኳን የጋብቻ ዝምድና የላቸውም፣ለግብጻውያን አረቦች ልጆቻቸውን የማይድሩበት ዋናው ምክንያት ኑብያውያን ጥንት የነበራቸው የበላይነት ስሜት በውስጣቸው ሠርጾ ስለቀየ ይሆናል:: አንዳንድ የዘር ግንድ ተራኪ መጻሕፍት በግዴለሽነት ኑብያኖችን ከሴማዊ ዘር ለመመደብ ሲሞክሩ ቢታዩም ከሴማውያን ዘር ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የላቸውም፤እንዲያውም ኑብያውያን አሁንም ቢሆን የዓረብኛን ቋንቋ በሰዋስዋዊ መልኩ



አስተካክለው ለመናገረ ያለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ጥንት ለወረሷቸው ባህሎችና ወጎች ታማኝ ሆነው መገኘታቸው ማስረጃ ነው::

ፕሪቻርድ(Prichard) እንደሚገልጸው ኑብያኖች በሁለት ይከፈላሉ:: አንደኛው ወገን በአባይ ወንዝ አካባቢ የሚኖር ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፊል ደግሞ በባህረ ኤርትራ አካባቢ የሚገኙት ናቸው:: ሄሮዶተስ በነበረበት ዘመን ኑብያና ስናር በተባሉት ሃገሮች ይኖሩ የነበሩት የተለያዩ ሁለት ዘሮች፣አንደኞቹ ኢትዮጵያውያን ተብለው ሲጠሩ ሌሎቹ የአርብቶ አደር ኑሮን የሚኖሩ የሴማውያን ነገድ ተወላጆች ነበሩ::

በቀይ ባህር አካባቢ ተወስነው ይኖሩ የነበሩት ነገዶች የሚታወቁበት በጨካኝነትና ተቀራርበው ለመኖር በአስቸጋሪነታቸው ሲሆን፣የአባይ ኑብያኖች ወይም ባራብራዎች ደግሞ ከኩሽ ኢትዮጵያውያን ጋር የሚመደቡ ኑሯቸውን በእርሻ ላይ የመሠረቱና የጥንቱ የካም ነገድ ልምዶችም የሚታዩባቸው ሕዝቦች ነበሩ:: የቴምር ዛፍን በመትከልና ለመስኖ ሥራ ውሃን በመዘውር በማውጣትና በመጠቀም ይታወቃሉ:: በዜና መዋዕል ዘገባዎቻቸው ላይ እንደተጠቀሰው እነዚህ ኢትዮጵያውያን ለጦርነት ሲሄዱ በሠረገላ የሚጠቀሙ፣ሲቢያኖች ደግሞ የጦር ቃል ኪዳን ተባባሪዎቻቸው እንደነበሩ ተጽፏል:: ይህ ይደረግ በነበረበት ዘመን ሴማውያን ምንም ዓይነት ብረት ነክ ሠረገላዎች አልነበሯቸውም:: ሂረን እንዳለው፣የእነዚህ ኢትዮጵያውያን ቅድመ አያቶች በከተሞች ይኖሩ የነበሩና ታላላቅ ድንቅ ቤተ መቅደሶችንና ሕንፃዎችን የገነቡ ነበሩ:: ሕግና



Scanned by CamScanner

መንግሥት የነበራቸው ዕውቀታቸውንና ሥነ ጥበባቸውን ለጥንቱ ዓለም በሰፊው ያሰራጩ ሕዝቦች ነበሩ::

በጥንታዊ ቅርሳ ቅርሶች ዕውቀቱ አስተማማኝ የሆነው ማውሪስ (Maurice) እንዳረጋገጠው፣ የጥንት ኢትዮጵያውያን ድንቅ የፈጠራ ችሎታ እጅግ ከፍተኛ ዝና አግኝቶ በነበረበት በዚያን ዘመን፣ ኢትዮጵያውያን በዓለም ታላላቅ ህንጻዎችን ሰርተዋል፣ከምድር በታች ዋሻዎችን ቆፍረዋል፣መተላለፊያዎችን ሠርተዋል፣ግዙፍ ግድቦችን በመገደብ ሐይቆችን ፈጥረዋል፣የውሃ ማስተላለፊያ መስመሮችን ዘርግተዋል፣ድልድዮችን ገንብተዋል:: የባቤልና የበሉስን ታላላቅ ማማዎችንና የግብጽ ፒራሚዶችን ገንብተዋል፣የሳልሴትንና የኤሌፋንታይንን ዋሻዎች ቆፍረዋል፣በሜካኒካል ኃይል አጠቃቀምና ክህሎታቸው ለማመን የሚያስቸግሩ ድንቅ ሥራዎችን አከናውነዋል::

በቤልቤክና በቴባይ ፈርሰው በሚታዩት ቤተ መቅደሶች መካከል ከ10 እስከ 20 ሜትር ከፍታ ያላቸውንና ውፈረታቸው ከ3 እስከ 6 ሜትር የሚደርስ ሃውልቶችን ቀርፀው እንዴት እንዳቆሟቸው ዛሬም ለማመን አዳጋች የሆነ ጉዳይ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በሕንድ የተገነቡት ፓጎዳዎች በውበታቸውና በድንቅነታቸው ከግብጹ የሚተናነሱ አይደሉም:: (Maurice`s, Ancient History Hindustan)



# ምዕራፍ ሦስት
# ጥንታዊት ኢትዮጵያና ምድሯ

ከኑብያ እስከ ግብጽ ምድር የነበረው በረሃማው ምድር ውሃ የጠገበና በዛፎች የተሞላ ሲሆን፣ ከጠባቡ የአባይ ሸለቆ በስተቀር ዛሬ ይህ ስፍራ ምድረ በዳ ነው ማለት ይቻላል:: የጂኦሎጂ መረጃዎች እንደሚገልጹት፣በጥንት ዘመን ይህ ምድር እንደዛሬይቱ ኮንጎ በርጥበት የተሞላ የነበረ ሲሆን፣በሰሃራ ምድር በተከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የላይኛውን ግብጽ ምድር ደረቅና ቃጠሏማ አድርጎታል:: እንደ ኬን አባባል፣ ይህን የአየር ንብረት መቋቋም የሚችሉት በዚያ ስፍራ የተወለዱት ነዋሪዎች ብቻ ሲሆኑ፣የአፍሪቃና የአውሮፖ ዲቃላ የሆኑ ልጆች ይህንን ቃጠሎማ የአየር ንብረት ተቋቁመው ቢኖሩ ከ10-12 ዓመት በላይ አያልፉም:: በጥንት ዘመን የነበረው የአየር ንብረት ምቹ ስለነበር በተከታታይ ዘመናት ከመጡት ኢትዮጵያውያን ይልቅ የጥንቶቹ ሰፋሪዎች ከፍተኛ ስልጣኔ ለመመስረት አስችሎአቸዋል::

የኢትዮጵያ ምድር ተብሎ ይጠራ የነበረው በነጭ አባይና በአቢሲኒያ መካከል ያለው ምድር ሲሆን፣ወደ ሰሜን አቅጣጫ እስከ ታችኛው ግብጽ ድረስ ይዘልቃል፣ ስሙም በለድ ኤ ሶኡዳን( Beled es Soudan) ወይም የጥቁሮች ምድር ተብሎ ይጠራ ነበር :: በአንድ ዘመን ከግብጽ እስከ ታችኛው ኑብያ ድረስ የነበረው ምድር የሜሮይ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት የነበረ ሲሆን፣ግዛቱም የእርሻና የግጦሽ ምድር ያካተተ



Scanned by CamScanner

እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ክሮውፋት (Crowfoot-Ancient Meroe. ጥንታዊቷ ሜሮይ) በተባለው መጽሐፉ በገጽ 29 ላይ እንደሚነግረን፣ የሜሮይ መንግሥት በብልጽግናዋ ዘመን የነበረችበት የኢኮኖሚ መሠረት፣በዘመኑ ግብጽና ሜሶፖታሚያ ከነበራቸው ጋር የተመሳሰለ ነበር:: የጥንቱ ጸሐፍት በሥልጣን እንደሚናገሩት ይህ ግዛት የእርሻ መሬቱ ብቻ ከመላው ግብጽ ስፋት የሚበልጥ፣የግጦሽ መሬቱም ስፋት ወሰን የለሽና ዝናብ የሚበዛባቸው ነበሩ:: ግዛቶቹም በከበሩ ማዕድናት የተትረፈረፉ ከመሆናቸው የተነሣ የልዑላኖቻቸው ልብስ ሳይቀር በከበሩ ማዕድናት ያጌጡና የሸክላ ሥራዎቻቸው በጌጥ የተሸለሙ ነበሩ:: ኢትዮጵያውያን፤ለቆንጆ ነገር ለክብረ በዓላትና ለድግስ ጉጉት አላቸው፤ያጌጠ ነገርን ለመልበስ ይወዳሉ ይባላል:: እነዚህን ሁኔታዎችን ስናይ ከሌሎች ጋር ለመመሳሰል የሚያደርጉት ፉክክር ሳይሆን ከሺህዎች ዓመታት በፊት ከነበሩት ቅድመ አያቶቻቸው የወረሱት ሊሆን ይችላል የሚል እምነትን ያሳድራል::

ሄሮደተስ በ2ኛው መጽሐፉ ገጽ 29 ላይ እንደሚለው፣ሜሮይ ታላቅና ዘመናዊ ከተማ በነበረችበት ዘመን በዚህች ከተማ ዚየስና አሞን ይመለኩ ነበር:: እንደ ሳይክሎፒዲያ ኦፍ ቢብሊካል ሊትሬቸር ጽሑፍ የኢትዮጵያ ብልጽግናና ታላቅነት የመነጨው ከሕንድና ከአረቢያ ጋር በአንድ ወገን፤በሌላ በኩል ደግሞ ከአፍሪቃ ሃገሮች በተለይ ከግብጽ ጋር ታደርግ በነበረው የገበያ ግንኙነት እንደነበር ይገልጻል:: በዘመኗ የንግድና የኢኮኖሚ ማዕከልም ከመሆኗ ባሻገር ቴብስና ሜሮይ ሊቢያን በጋራ ቶች



ግዛትነት አስተዳድረዋል::ኢትዮጵያ ከግብጽ ለሚንቀሳቀሰው የነጋዴዎች ቅፍለትና ከሱዳን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ለነበረው የጉዞ መስመር ዋና መተላለፊያም ነበረች:: ጥንታዊቷ ጋዴስ ከመገንባቷ በፊትና በታርቴሰስ ዘመን፤ስለዚሁ የንግድ መስመር ስትራቦ የተባለው የታሪክ ፀሐፊ ጽፏል:: ከሜሮይ በስተምስራቅ በኩል የነበረው የንግድ መስመር፤አፍሪቃ ከደቡብ አረቢያ ጋር ሸቀጥና ምርት የምትለዋወጥበት ሲሆን፣መጠን የለሹ የኩሾቹ ሀብትም የተካበተው እንደድር ከተወሳሰቡት ከእነዚሁ የንግድ መስመሮች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ይላል::

ለመሆኑ ግብጽ ለአስከሬኖቿ የመገነዣ ቅመማ ቅመሞችና መድኃኒቶቿ ከየት ነበር የምታገኘው? በመሰዊያዎቿስ ላይ የምታጥናቸውን የዕጣን ዓይነቶችንስ ከየት ነበር የምታስመጣው? በማለት ቢብሊካል ሊትሬቸር ይጠይቃል:: የፋርሱ ንጉሥ ካምቢሰስ የጓጓለት፤ወደግብጽ ምድር ይገባ የነበረው የኢትዮጵያ ወርቅ ምንጩ ከየትኛው ስፍራ ነበር? ግሪካውያንና ፊንቃውያን ይጎመጁለት የነበረው የዝሆን ጥርስና የኤቦኒ እንጨት መገኛው ከየት ነበር? የአይሁድ ባለቅኔዎችና የግሪክ ገጣሚዎች ያደነቋትና ያመሰገኗት ኢትዮጵያ ስሟ ከመቼ ጀምሮ ነበር መታወቅ የጀመረው? በዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ አኳያስ የትኞቹ የኢትዮጵያ ከተሞች የንግድ ማዕከላትና መተላለፊያ ነበሩ?

መልሱ፤የኢትዮጵያ ዋነኞቹ የንግድ ቀጠናዎች ተብለው የሚታወቁት ከሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻዎች እስከ ሜዲተራንያን ባሕር ጠረፎች



Scanned by CamScanner

የተመሰረቱት ከተሞች ለመሆናቸው የተገኙት የፍርስራሽ ቅርሶች ያረጋግጣሉ:: አዱሊስ፣አክሱም፣ሜሮዶ፣ቴብስና ካርቴጅ ዋናው የንግዱ መስመር አገናኝ ሰንሰለቶች ሲሆኑ፣መጽሐፍ ቅዱስ የኢትዮጵያ ንግድ በማለት የሚጠራው በነዚህ ከተሞች በኩል ይተላለፍ የነበረውን የሸቀጥና ምርት የስርጭት መስመር ለመግለጽ ነው::

Ancient Nations of Africa በተባለው መጽሐፉ ሂረን(Heeren) እንደሚነግረን፣የንግድ ግንኙነቱ የነበረው ከደቡብ እስያ ሃገሮች መካከል በሕንድና በአረቢያ፣በአፍሪቃ ደግሞ በኢትዮጵያ፣በሊብያ፣በግብጽ መካከል ሲሆን፣ይህም በጋራ ፍላጎታቸው ላይ የተመሠረተ ውጤት ነበር:: ይህም በመሆኑ ለሥልጣኔያቸው መዳበር ረድቷቸዋል:: የኢትዮጵያን ሥልጣኔ አስመልክቶ የተናኘው ዝና ወደ ግሪክ የገባው በሆሜር ዘመን ሲሆን፣የአርጎን የባህር ጉዞ፣ የትራይተን ባህርና፣ የሄስፔሪድ የአትክልት ቦታን አስመልክቶ የሚነገሩት ታሪኮች ከኢትዮጵያውያን ዓለም አቀፍ ንግድ ሥራ ጋር በእጅጉ ተዛምደው የሚነገሩ ናቸው:: የኢትዮጵያ ንግድ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ ጥበቃና ከለላ ይደረግላቸው እንደነበር በሄላስ ከተማ በዶዶና የተቀደሰ ስፍራ የተገኙት ማስረጃዎች ይገልጻሉ:: የአሞን ቀሳውስት እንዳሉት እነዚህ ቅዱስ ስፍራዎች ከቴብስና ከሜሮይ እስከ ግሪክ ድረስ ተቆርቁረው ነበር::

የሜሮይ ከተማ የጁፒተር የተቀደሰ ቦታ በመሆን ለእጅግ ብዙ ዘመናት እንደቆየች ሂረን ገልጾታል:: እስከ አንድ ሺ ዓመት ቅ.ል.ክ ድረስ



በዓለም የኃያል መንግሥት መዲና የነበረችን የሜሮይ የፍርስራሽ ቅርሳ ቅርሶቿን ለተመለከተ ቀደሞ የነበራትን ገጽታን ያሳያሉ:: ይህ ግን ለዘመናችን ተመራማሪዎች እምብዛም ስሜት የሚሰጣቸው አይደለም:: ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት ለግብጽ ወርቅ ስታቀርብ የኖረች ሲሆን፣ኤልባ በተባሉ ጋራዎች የወርቅ ቦታዎች ነበሯት:: እንዲያውም እስከ 12ኛው መቶ ዓ.ም ድረስ የወርቅ ቁፋሮ ቦታዎቿ በሥራ ላይ እንደነበሩ፣ይመረት የነበረው ከፍተኛ ብዛት ያለው ወርቅ አለቶችን በመሰባበርና በማድቀቅ ዘዴ እንደነበር መረጃዎች አሉ:: ቶፓዝንና ኤመራልድ የተባሉትን የከበሩ ማዕድናት ለረጅም ዘመናት ታመርት ነበር:: እንደሳንድ ስቶን፣ላይምስቶንና ግራናይትን የመሳሰሉትን የግንባታ አለቶችንም ለዓለም ገበያ በማቅረብ የታወቀች ሃገር ነበረች::

የጥንታዊ ሚሮይ ዜጐች ከቀይ ሸክላ ጡብ በተሰሩ ሕንፃዎች ይኖሩ የነበር ሲሆን የዛሬዎቹ ዜጎቿ ደግሞ ከጭቃ በተሠራ ሣር ቤት ይኖራሉ:: በርዝ እንደሚለው፣በላይኛው ኑብያ የሚገኙት ፍርስራሽ ቅርሶች የጥንቱን ከተሞች ውበት ያረጋግጣሉ:: ሆኖም ግን የዛሬ የታሪክ ተማሪዎች የማያውቁት ነገር ቢኖር በኑብያ የሚገኙት ሃውልቶችና ቤተ መቅደሶች ከግብጹ ይልቅ በቁጥር የሚበልጣቸውን ጉዳይ ነው:: አረቦቹ በበኩላቸው ከቦታ ወደ ቦታ እየተጉዳኙ የሚሄደው የበረሃ አሸዋ ስለሸፈናቸው እንጂ የአውሮፖ ተመራማሪዎች ሊያገኟቸው የሚችሏቸው ቅርሶቻችን በርካታ ናቸው በማለት ይናገራሉ:: ከናጋ በስተሰሜን ወደ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኙትን እጅግ የተወሳሰበ የፍርስራሽ ቅርሶች



Scanned by CamScanner

ስፍራ አረቦቹ ማሳውራት ይሉታል:: በዚህ ስፍራ በማዕከልነት የቆመው ህንፃ የዙሪያው ርዝመት ወደ ስምንት መቶ ሜትር ይሆናል፤ በምሰሶዎቹ ላይ ግን የሃይሮግሊፊክስ ጽሑፍ የላቸውም:: (Reclus, The Earth and Its Inhabitants, Vol. I, P.246).

እዚህ ላይ ቆም ብለን ኬን(Keane) ስለፋዩም ወረዳ የገለጸውን እንመልከት:: ወረዳው በእርሻ ምርት የታወቀ ሲሆን፣እንደ ወይን፣ወይራ፣ሸንኮራ አገዳ፣ጥጥና ጽጌረዳ የመሳሰሉትን ይመረትበት ነበር:: የብርቱካንና የሎሚ ዛፎች ቁመት ከአፕል ዛፍ አያንስም ነበር:: ስፍራው ጥንት ደረቅና ጎድጓዳማ ሲሆን፣በዘመኑ የነበረው ፈርዖን በስተምዕራብ ከነበረው የአባይ ወንዝ ውሃ ለመጥለፍ በነበረው ዓላማ አለታማውን ጋራ በማስፈልፈል የውሃ ማስተላለፊያ ዋሻዎችን አሠርቷል:: ይህ ደረቅና ጎድጓዳ የነበረው ወረዳ በታላቅ ሐይቅ በመሸፈኑ የተነሳ ከ12ኛው የግብጽ ሥርወ መንግሥት ጀምሮ ይህ በረሃማ ስፍራ ምድረ ገነት ሲሆን በቅቶ ነበር::

ሞኢሩስ ተብሎ የሚጠራው ይህ ሐይቅ ወደ ግብጽ ይገባ ከነበረው የአባይ ወንዝ ውሃ ግማሹን ያህል ሳይዝ እንዳልቀረ ይገመታል። በጥንት ዘመን ከተከናወኑት ታላላቅ የኢንጅነሪንግ ስኬታማ ሥራዎች መካከል እንዳንዱ ይጠቀሳል:: ዛሬ ምንም እንኳን ይህ ሐይቅ ቢደርቅም ወረዳው አሁንም ቢሆን ለምለምና ተፈላጊ ቦታ ነው:: በጀበል አርደገ ስለሚገኙት ሁለት ቤተ መቅደሶች መለስ ብለን ብናይ ተቀርጸው የሚታዩት ቅርጻ ቅርጾች የአንድን የግብጽ ፈርዖን የድል ገድል



ይገልጻሉ:: ወደ አንደኛው ህንጻ ሲቀረብ የሰው ራስና የአንበሳ አካል ያላቸው ሀውልቶች (ስፊንክስ) ተደርድረው ይታያሉ::

በሜሮይ ጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ ፒራሚዶች፣ቤተ መቅደሶች አደባባዮችና የእንስሳት ሃውልት ቅርሶች አሁንም ቆመው የሚታዩ ቢሆንም፣የተሠሩበት የሳንድስቶን አለት ግን እንደ ግብጽ ጠንካራ አለመሆኑ ይታያል:: ወደስማኒያ የሚጠጉ ፒራሚዶች በጎብኝዎች ለጉዳት የተዳረጉ ሲሆን፣እንደ ሴፒየንስ ጥረት ባይሆን ኖሮ እነዚህ ቅርሶች ፈጽመው በወደሙ ነበር:: ለምሳሌ ካይሮ በተቆረቆረችበት ወቅት ነዋሪዎቹ የፒራሚዶቹን ግድግዳ ይሸፍን የነበረውን ዕብነ በረድ በመንቀል እንደተጠቀሙበት ይታወቃል:: ይህም የሚያመለክተው፤በዚህ ዓይነት ብዙ ቅርሶች ፈጽመው የመጥፋታቸውን ጉዳይ ነው:: በሜሮይ ያሉት እንደ ግብጽ ፒራሚዶች የገዘፉ ባይሆኑም በውበታቸውና በሥነ ጥበብ ሥራቸው ይበልጣሉ:: በአቡ ሲምበል ያሉትን የሁለት ቤተ መቅደሶችን ሁኔታ ሬክሉስ ሲገልጽ፣ጥንታዊው ቤተ መቅደስ ከአለት ተቦርቡሮ የተሠራ መሆኑን፣ከዋናው መግቢያ በራፍ ፊት ለፊት አራት ግዙፍ ሀውልቶች እንዳሉትና ከፍታቸው ወደ 18 ሜትር የሚጠጋ ስለመሆናቸው፣ዙሪያቸውም በጽሐፍ የተሞሉ፣በህንፃው የውስጥ ክፍሎች ሦስት ሰፋፊ አዳራሾች በተከታታይ እንደአሉትና፣እንዲሁም በብሩህ ቀለማት የተዋቡ ስዕላት በአስራ ሁለት አነስተኛ አዳራሾች ስለመኖራቸው ነው:: **እነዚህን ሐውልቶች በጥንቃቄ ላጠና፣የሰዎቹ ገጽታ ያለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያዊ መሆኑን ይመለከታል::**



Scanned by CamScanner

ከምድር በታች የሆኑ የቀሻ መቃብሮች፣መተላለፊያዎችና ማማዎች የሞሉባቸው ቤተ መቅደሶች እስከ ላይኛው አባይ የመጀመሪያ ፏፏቴ ድረስ የሚታዩ ሲሆን፣በበረሃ አሸዋ ተቀብረው ከነበሩበት ከተሞች በአጥንዎች የተገኘው አንዱ ማክንዳ የተባለው ነው:: በዚሁ ስፍራ ከምድር በታች ያሉት ዋሻዎች በድንቅ አዳራሾች የተሞሉ ሲሆኑ፣ተመሳሳይነት ያለው ሌላ ጥንታዊ ከተማም በከሬት ሀገር ተገኝቷል:: በቤት ኡል ዋሊ በተገኙት የመቃብር ስፍራዎች ላይ ተቀርፀው የተገኙት ምስሎች ደግሞ ስለድል በዓል አከባበር፣ስለድንገተኛ ጥቃት፣ስለፍርድ ቤትና ስለውጊያ ውሎ የሚገልጹ ሲሆኑ፣የእነዚህ የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎችና የቀለም ቅቦች አሁንም እንኳን አላረጁም" (The Earth and Its Inhabitant. Vol. I. P. 306)

በዳቦድና በዳካ የሚታዩት ቤተ መቅደሶች የተገነቡት በኢትዮጵያዊው ንጉሥ ኤርጋሜነስ ዘመን ነው:: ሳይስ እንደሚለው ብዙዎቹ ቅርጻ ቅርሶችና የጥበባት ውጤቶች የግብጽ ስልጣኔ ውጤቶች ተደርገው ሊወሰዱ ይችል ይሆናል፤ሆኖም ግን በኑብያ ውስጥ ቶትመስ ሣልሣዊ(3ኛ) በአማንዳ ቤተ መቅደስ ለወጣት ሚስቱ ማስታወሻ ያሠራው ሃውልትና ያሳለው ምስል ራምሴስ ካልዓይ(2ኛ) ከገነባቸው ግዙፍ ሐውልታት ቢበልጡ እንጂ የሚያንሱ አይደሉም:: በነዚህ ዘመን የታዩት ሕንጻዎች ረጋ ሠራሽና ውበት አልባ፤የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎቻቸው ደርዝ የሌላቸውና የማይማርኩም ናቸው በማለት ሳይስ ገልጾታል:: በኑብያ የተገኘው የአቡ ሲምበል ሃውልት ግን በስነ ጥበብ



ረገድ ሲነጻጸር የዓለማችን ድንቅ የተጠረበ አለት ሥራ ነው ማለት ይቻላል:: ከራምሴስ ሴሶስትሪስ ከንቱና የባዶ ዝና ጦርነት ጥፋት የተረፈ ይለዋል:: (A. H. Sayce, Ancient Empires of the East.)

የሜሮይ መንግሥት ሰርያን በገዛችበት ዘመን 250 ሺህ የሰለጠነ ጦር ሠራዊትና 400 ሺህ ድጋፍ ሰጪ ኃይል ነበራት፤ከተማይቱም እጅግ ታላቅና ሰፊ ነበረች:: ስለዚህች ከተማ ፍርስራሽ የጻፈው ፕሊኒ እንደሚለው፤በሮማውያን ዘመን እነዚህ ፍርስራሾች አልተገኙም:: ምክንያቱም በሁለቱ መንግሥታት መካከል በሺህዎች የሚቆጠሩ ዘመናት አልፈው ነበርና:: ስለዚህም ነው የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ብቻ በማጥናት ብዙ መረጃዎች ሊገኙ ያልተቻለው:: በርግጥም የኢትዮጵያን ጉዳይ ካለንበት ዘመን አኳያ ስናይ ማለት የምንችለው በጣም ጥንታዊት ሀገር ስለመሆንዋ ነው::

ሆስኪንስ(Hoskins) እንደሚለው፣ በግብጽ ጊዛ በተባለው ስፍራ የቆሙት ፒራሚዶች በሥነ ጥበብ ንድፍ ደረጃ አእምሮ ላይ የሚያሳድሩት ስሜት ታላቅ ቢሆንም፤በሜሮይ ከተማ ለመቃብር አገልግሎት የታነጹ ተመሳሳይ ፒራሚዶች ስለመገኘታቸው እምብዛም አይታወቅም:: በሜሮይ የአርኪኦሎጂ ስፍራዎች በግድግዳዎች ላይ ተቀርጸው የሚታዩት ምስሎች የኩሽ ገዢዎች ገጽታዎችን የሚያሳዩ ናቸው:: በተጨማሪም፤ሚሮይ፣ የጁፒተር የተቀደሰ ከተማ ነበርች፣ከዚህች ከተማ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ፣ሥነ ጥበብ፣ሃይማኖት ወደታችኛው አባይ ምድርና



Scanned by CamScanner

ወደ ግሪክ እንዲሁም ወደ ኖርዲክ ምድሮች ይሰራጭ እንደነበር ሂሪን ዘግቦታል፡፡ የማሳውራት ከተማ ደግሞ፤በግብፅ ውስጥ ወደር የማይገኝለት የታላቅ ኮሌጅ መቀመጫ እንደነበር ካሊአንድ(Calliund) ጽፏል፡፡

እንደ ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፤ኑብያኖች አሁን ካሉት የግብጽ ቅብጦች(Copts) ይልቅ ከጥንታዊያኑ ጋር ይቀራረባሉ፡፡ እንደ ዶክተር ፕሪትቻርድ ግምት፤የባራብራ ነገድ በግብጽና በኑብያ ከሰፈረው ከመጀመሪያው የኩሽ ዘር የወጡ ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ በግብጽ፤የፈርዖኖች ሥርወ መንግሥት ከመመስረቱ በፊት ግብጽን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የገዛው የጥንቱ ዘር መነሻው ከላይኛው አባይ ሲሆን አጉ ወይም አኑ ይባላል፡፡ ከዚህ ዘር የፈለቀ ሥልጣኔ፤ወግና ባህል ቀስ በቀስ ወደ ግብጽ ከዚያም ወደ ኤጅያን ምድር፤ከሲሲሊ ወደ ኢጣልያና እስፖኝ ተሠራጨ፡፡ሞሶ አንጄሎ እንደሚለው፤በሜዲተራንያን ጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች ይጠቀሙባቸው የነበሯቸው የሸክላ ቁሳቁሶች ከግብጾች ጋር አንድ ዓይነት ናቸው፡፡

በአባይ ሸለቆ ተቀብረው የነበሩ የአንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰዎችን አጽም ራይዝነር(Reisner) በ1899 ዓ.ም መርምሮ ነበር፤ምርመራው ያረጋገጠው ሟቾቹ ሲቀበሩ እግሮቻቸው በሆዳቸው ላይ ታጥፈው [illegible] የሚያሳይ ሲሆን፤ድምዳሜው ደግሞ ይህ አቀባበር [illegible] ኢትዮጵያዊያን ሥርዓት እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡



ስለኢትዮጵያ እውነቱን ለማወቅና ትክክለኛ የህሊና ዳኝነት ለመስጠት የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ከዘመናችን መጻሕፍት አጥጋቢ መረጃዎች ሊያገኙ ያልቻሉበት ዋናው ምክንያት ፊታቸውን ወደ ጥንታውያኑ ያረጁና ያፈጁ መዛግብትና ማህደራት ያለማዞራቸው ሲሆን፤ ወደጥንቱ መጻሕፍት ፊታቸውን መልሰው ቢሆን ኑሮ ተዝቆ የማያልቁ የምስክርነት ማስረጃዎች ባገኙ ነበር፡፡ እንግዲህ ከነዚህ ማስረጃዎች ውስጥ የዘመናችን የታሪክ ጸሐፍት ለዓላማቸው የሚስማማቸውን ብቻ በመውሰድ ስለ ኢትዮጵያ ተገልፆ ያለውን ብዙውን እውነተኛ ታሪክ ባለመቀበል ወደጎን ትተውት እናያለን፡፡

ስለዘር ግንድ ጥናት ስናነሳ፤ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ የለየለት ቅራኔ ፈጦ ይታያል፡፡ እነዚህ እንደድርና ማግ የተጠላለፉ ውስብስብ አተረጓጎሞች ካልተፈቱ እውነተኛው ታሪክ ሊገለጽ አይቻልም፡፡ አንዱ መጽሐፍ ኢትዮጵያውያንን የሴማውያን ዘር ናቸው ይላቸዋል፤ሌላው ደግሞ የያፌት ዘር ናቸው ይላቸዋል፡፡ ዛሬ እየተነገረ ያለው ይህ ንድፈ ሃሣብ ነው፤ነገር ግን ኢንሳይክሎፒዲያው የሚገልጸው ኑብያውያን ጨምሮ ኢትዮጵያውያን የጥቁር ዘር ስለመሆናቸው ነው፡፡

የግብጹ ፈርዖን፤ለፋርሱ ንጉስ ካምቢሰስ ልጁን በጋብቻ ለመስጠት እምቢ በማለቱ የተነሳ ጦርነት ተከፍቶበት እንደነበር የተዘገበ ታሪክ አለ፡፡ ይህ የሚያሳየው የአፍሪቃ ነገሥታት በጥንቱ ዘመን ኩሩ የመሆናቸውን ጉዳይ ሲሆን፤ በብሪቲሽ ሙዚየም ውስጥ በሚገኝ በአንድ ሃውልት ላይ



Scanned by CamScanner

ተቀርጾ የሚታይ ምስል የሚያሳየው፣ኢትዮጵያውያን በአባይ ወንዝ ላይ ይጓዙ የነበረውን የፋርስን ንጉሥ ካምቢስስ የባሕር ኃይል ሠረዊት እንዴት እንደደመሰሱትና በረሃብ እንደቀጡት ነው። ከዚህ ጦርነት ቀደም ብሎ በናፓታ ይገኙ የነበሩ ቤተ መቅደሶች በጦርነት ፈራርሰው ነበር።

ሌላው ልዩ የሆነ ጉዳይ ደግሞ፣በዚያን የጥንት ዘመን ካንዳስ ተብሉ ይታወቅ የነበረ የንግሥቲቶች ዘር መላውን የኢትዮጵያ ኤምፓየርና አቢሲኒያን ጭምር ይገዛ እንደነበር፣የንግሥቲቶቹም መቀመጫና የቀብር ስፍራ በዚሁ በሜሮይ ከተማ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል። በሜሮይ የተተከሉት ፒራሚዶች ካንዳስ(Candace) ተብለው ለሚጠሩት ንግሥቲቶች ክብር የተገነቡ ሲሆን፣ሐዋርያው ቅዱስ ፊሊጶስ ወንጌልን በሰበከበት ዘመን ከነዚህ ንግሥቲቶች መካከል የአንዷ ሀብት የክርስትና ሃይማኖት ለማስፋፋት እንዲውል ተደርጎ እንደነበር ይታወቃል። ስለሃይማኖት ከተነሳ በዘመናችን በምስራቁ የዓለም ክፍል የክርስትና ሃይማኖት ጠብቃ የቆየች ብቸኛ ሃገር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗ በቂ ምስክር ነው።በኢትዮጵያውያን ልብ ጽላት ሃይማኖት የተጻፈ ስለመሆኑም ማረጋገጫ ነው። መጽሐፍት እንደሚያስረዱት፣የእነዚህ ንግሥቲቶች የሀብት ከምርት ምንጩ የኢትዮጵያ የሽቀጥ ንግድ ሲሆን፣የአዜብ ንግሥት በመባል የምትታወቀውና የአይሁዱን ንጉሥ ሰሎሞንን ለመጎብኘት የሄደችው ንግሥተ ሳባ ከነዚህ የንግሥቲቶች የዘር ግንድ መካከል አንዷ እንደነበረች፣ከንግሥቲቶች መካከል ሌላዋ ደግሞ



በተዋጊነቷ የምትታወቅ የኢትዮጵያ ንግሥት እንደነበረች ስትራቦ ጽፏል።

ከሜሮይ እስከ ሚምፊስ በነበሩት ቤተ መቅደሶች ውስጥ ከአለት ተቀርፀው አሊያም በግድግዳ ላይ ተስለው የሚታዮት ምስሎች የሚገልጹት የዕጣን ማሳረጊያ ጽሕና ስለያዙ ካህናት ነው። ምስላቱ የሚያሳዩት ካህናቱ ከወርቅና ከብር ከተሰሩ ንዋየ ቅድሳትና በከበሩ ማዕድናት ባጌጡ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በአምላካቸው ፊት መስዋዕት ሲያቀርቡ ነው። የሚቃጠል መስዋዕት ለተለያዩ ሥርዓቶች ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ቢሆንም፣ ከሁሉ የከበረው የመስዋዕት ዕጣን ግን ይመጣ የነበረው ከኢትዮጵያ ነበር። እንዲሁም በተጨማሪ የጥንቱን ዓለም የሽቶ ፍላጎት ታሟላ የነበረችው ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ከእነዚህ ውድ ሸቀጦች የገቢ ምንጮች የነበሯት ቢሆንም፣አስከሬኖች እንዳይበሰብሱ ለማድረግ ይውል ከነበረው ቅመማ ቅመም ከፍተኛ ጥቅም ታገኝ እንደነበር ማስረጃዎች ያሳያሉ። አስከሬን እንዳይበሰብስ የሚያደርግ አሠራርን ሂንዱዎችና ግብጻውያን ለረጅም ዘመናት ተጠቅመውበታል። በዚህም የተነሳ የዕጣንን ፍላጎት ለማርካት ይደረግ የነበረው የአቅርቦት ንግድ እጅግ ከፍተኛ ነበር። በነነዌ፣በፐርስፐሊስና በቻይና የተገኙት የሸክላ ዕቃዎች ብዙዎቹ የዕጣን ማሳረጊያ ጽንሐ ተስሎባቸው ተገኝተዋል። ዕብራውያን ግን ዕጣንን ለሚቃጠል መስዋዕት ብቻ ይጠቀሙበት የነበር። በግሪክና በሮም ጥንት ይህ የዕጣን ሥርዓት ይካሄድ እንደነበርና በዘመናችንም ካቶሊኮች ሥርዓተ ዕጣንን ሲያካሂዱ



Scanned by CamScanner

ይታያል። በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀብር በሚከናወንበት ጊዜ ዕጣን ይቃጠል እንደነበር ይታወቃል።

የጥንታዊቷ ኢትዮጵያን ታላቅነት ጠቅሰው የጻፉ የጥንት ዘመን ታሪክ ጸሐፍት እንደሚሉት፣ የኃያልነቷ መሠረት በተፈጥሮ ሀብቷ ክምችቷ፣ በዓለም አቀፍ ንግዷና በሚሊዮን ቁጥር የተደራጀው የጦር ሠራዊቷ ነበር። ጥንታዊ ከተሞቿ ደግሞ ወደ አየር በሚወነጨፉና የወይን ጠጅማ በሚመስሉ የውሃ ሻሻቴዎች ያጌጡ እንደነበረ ቀደምት ታሪክ ጸሐፍት ጽፈዋል።

በዚያ ዘመን ማይክሮቢያኖች የተባሉ አስደናቂ ሕዝቦች በኢትዮጵያ ኤምፓየር ይኖሩ ነበር። ሄሮዶተስ እንደጻፈው፣ የፋርሱ ንጉሥ ካምቢሰስ የእነዚህን ሕዝቦች የሀብት መሠረት እንዲሰልሉ ሰላዮችን መልእክተኞች አስመስሎ ይልካል። መልእክተኞቹም ለንጉሡ የሚቀርብ ገፀ በረከት ይዘው ተጉዘው ሄዱ። የተቀበላቸው ንጉሥ ዘለግ ያለ ቁመት የነበረው፣ የሚያስተዳድራቸው ሕዝቦች ስልጡን፣ የሕግ ተቋማትም ባለቤቶች ነበሩ። ከፋርሱ ንጉሥ የተላኩት እነዚህ ሰላዮች በማይክሮቢያኖች ንጉሥ ፊት ሐምራዊ ቀለም ያለው ሸማ፣ ወርቅና ሽቶዎች እንዲሁም ከፖልም ፍሬ የተጨመቀ ጠጅ አቀረቡ። ንጉሡ ግን የቀረበለትን ገፀ በረከት እንደመናኛ ስጦታ በመቁጠር በንቀት ዓይን ተመለከተው። ቀጥሎም፣ በሃገራቸው ስለአለው የአመጋገብ ሁኔታ፣ በሃገራቸው ረጅም ዕድሜ ስንት እንደሆነ ይጠይቃቸዋል። እነርሱም በሃገራቸው የዕድሜ ባለጠጋ የተባለ ሰው ሰማንያ ዓመት ሲመልሱ በሃገራቸው



እንደሚኖር ይገልጻሉ። ስለአመጋገባቸውና ስለዕድሜያቸው ሁኔታቸው የተረዳው ይህ ንጉሥ እንዲህ አላቸው "እንደዚህ የመሰለ ግብስብስ ምግብ የሚመገብ ሰው ከዚህ በላይ ዕድሜ ለመኖር አለመቻሉ አያስደንቀኝም፣ እኛ ማይክሮቢያኖች የዕድሜ ዘመናችን በአማካይ አንድ መቶ ሃያ ዓመት ሲሆን፣ አንዳንዴም ይጨምራል፣ ምግባችን ወተትና ሥጋ ነው" በማለት ይመልስላቸዋል። ይህ አመጋገብ በዚያን ዘመን የሰለጠነ ሕዝብ መለያ መሆኑን ለማመልከት። መልእክተኞቹ ለስለላ መምጣታቸውን የተረዳው ንጉሥ፣ "ይህንን የላኩልህን እንጨት እንደደጋን ማጉበጥ በቻልክ ጊዜ እኛን ማይክሮቢያኖችን የሚዋጋ ሠራዊት መላክ ትችላለህ" ብላችሁ ለንጉሣችሁ ንገሩት የሚል መልእክት ጨምሮ አስተላለፈ። ይህን መልእክት የተቀበለው የፋርሱ ንጉሥ በቁጣና በንዴት ከመብገን በስተቀር ሊያደርግ የቻለው ነገር አልነበረም።

የፋርሱ ንጉሥ አምባሳደሮች በቆይታቸው ወቅት በከተማይቱ ዳርቻ ይገኝ ወደነበረ የ"ፀሐይ ጠረጴዛ" ተብሎ ወደሚጠራ ለጥ ያለ ሜዳ ተወስደው የሚደረገውን ተመልክተዋል። በዚያ ስፍራ በየምሽቱ ከፍተኛ ብዛት ያለው የተቀቀለ ሥጋ ተዘጋጅቶ ይቀመጣል። ይህ ግራ የሚያጋባ ድርጊት ለብዙዎቹ አስገራሚ ቢሆንም፣ ድርጊቱ የኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ ውጤት ነበር። ኢትዮጵያ፣ በሃገሯ እንደጎርፍ የሚተመውን የነጋዴዎች እንቅስቃሴ እንዳይቋረጥ ለማድረግ በ"ፀሐይ ጠረጴዛ" ለመብላት የሚፈልግን ነጋዴ ሁሉ በነፃ መመገብዋ ሆን ብላ ያደረገችው ዘዴ ነበር። የካምቢሰስ አምባሳደሮች፣ የጦር ምርኮኞችን የአኗኗር ሁኔታ ይመለከቱ



Scanned by CamScanner

ህደእስር ቤት ለገብኝት በተወሰዱበት ወቅት፣ የጦር ምርኮኞች በተሠራ ካቴና ታስረው ለማየት ችለዋል፡፡

ጵያ የሆነና ከግብጻውያኑ ይልቅ እጅግ በላቀ ደረጃ ይገኝ የነበረው ጥበብ ደግሞ ሰው በሚሞትበት ወቅት አስከሬኖች እንዳይበሰብሱ ረግ ዘዴ ሲሆን፣አስከሬኖች እንዳይበሰብሱ መደረጉ ብቻ ሳይሆን ለገው አቅጣጫ ለዕይታ እንዲመቹ አድርገው ከመስተዋት በተሠራ ሣጥን ውስጥ የማስቀመጥ አሰራርም ነበራቸው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ሬኖችን በጀሶ ከሸፈኑ በኋላ የሟቹን ምስል በላዩ ይስሉና ከክሪስታል ሥራ የአስከሬን ሣጥን ውስጥ ይከቱታል፡፡ የግብጻውያኑ የአስከሬን ማመጥ ደግሞ የሰውየውን ገጽታ ብቻ ከላይ ለማሳየት በሚያስችል ኚን ነበር፡፡ ስለጥንታውያኑን ኢትዮጵያውያን በመደነቅ ብዙ የጻፈው ዶተስ(Herodotus)፤ኢትዮጵያውያኑ በዚያን ዘመን በዓለም አቀፍ ድ እንቅስቃሴያቸው፣በሜታል ነክ ሥራቸው፣በኪነ ጥበባት ጤቶቻቸው፣በሕግና አመራር፤በእስር ቤት አስተዳደር ዕውቀትና ሎታው የታወቁው ነበሩ ብሏል፡፡



# ምዕራፍ አራት
# የኢትዮጵያ አስደናቂ ሥልጣኔ

የግብጽ ታሪክ መዘገብ ከተጀመረበት ዘመን ጀምሮ ተጽፎ የተገኘው ታሪክ እንደሚገልጸው በዚያች ምድር ይኖሩ የነበሩት ቀደምት ሕዝቦች እንደ አራዊት ጨካኝና ሥነ ምግባር የማይታይባቸው ነበሩ፡፡ በምዕራብ አውሮፓና ሰሜን እስያ ደግሞ ከፊል የሰው ባህርይ የነበራቸው ኒአንደርታል ተብለው የሚጠሩ ሰው መሰል ዝርያዎች በተፈጥሮ ብቻ የበቀለውን እየተመገቡ በዋሻዎች ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ኒአንደርታል የተባሉት ሰዎች ይጠቀሙባቸው የነበሩት መሣሪያዎች ከተፈጥሮ የሚገኙትን እንደ ባልጩት መሰል ድንጊያዎችን ብቻ ሲሆን፣ወደሰለጠነው የሰው ዘር ለመደባለቅ ረጅም ዘመናትን አስቆጥሮአቸዋል፡፡ በአፍሪቃ፣የሰው ዘር ከሥልጣኔ ቁንጮ ለመድረስ ረጅም ዘመናትን ለማስቆጠሩ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡

ይልቁንም አፍሪቃ የድንጋይ ዘመን የተባለውን ሳታይ በቀጥታ ወደ ሜታል /ብረት ነክ/ ዘመን ነበር የተሸጋገረችው ተብሎ ይታመናል፡፡ በሰሜንና በምስራቅ ጠፍ መሬት ሰፍረው የነበሩት የሴምና የያፌት ዘሮች የከብት እረኞች በነበሩበት ወቅት በግብጽና በላይኛው አባይ የላቀ ሥልጣኔ እንደነበር ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ሁለቱ የሰው ዘሮች ወደ ተረጋጋና የሠፈረ ሕዝብ የአኗኗር ዘይቤ ራሳቸውን ለመለወጥ በርካታ ዘመናት የወሰደባቸው ምክንያት ወደ ዕደ ጥበብና ምርት የሚወስደውን



Scanned by CamScanner

የግብርና መሠረት ስላልጣሉ ነበር። እናም 5 ሺህ ዓመታትን ወደ ኋላ መለስ ብለን እነዚህን ሁለት ዘሮች ብንመለከት፣መሃይምና ኋላቀሮች ነበሩ። ሥልጣኔን ከኩሽ ዘር በከፊል የተማሩት ከለዳውያንና አሦራውያን እስከ ገነነበት ዘመን ድረስ ሴማውያን ምንም ዓይነት የሥልጣኔ ምልክት የማይታይባቸው ነበሩ፣ዕብራውያን ራሳቸው እርሻንና ሥነ ሕንጻን የተማሩት ከከነዓን ምድር ይኖሩ ከነበሩት ከካም ነገዶች ለመሆኑ በቂ ማስረጃዎች አሉ።

ስለጥንቱ የኩሽ ዘር ሥልጣኔ ማውጋት ከተነሳ፣አራዊቶችንና እንስሳትን ለማዳ በማድረግ፣አትክልቶችንና ዕፅዋቶችን በማዳቀል የመጠቀ ክህሎትና ችሎታ እንደነበራቸው መገንዘብ የግድ ይላል። ሌሎች የሰው ዘሮች የእርሻን ምንነት ሳያውቁ የኩሽ ዘር ይህንን ያክል የተራቀቀ እንደነበር መካድ አይቻልም። የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ለስልጣኔ መሰረት ለመጣል በአንድ ስፍራ ረግቶ የመኖር ባህል የግድ ነው ይላሉ። ይህ ባሕርይ የሌላቸው፣ነገር ግን ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር የሚኖሩ ሕዝቦች ትዕግስት የለሾችና ኃይለኝነት ከጭካኔ ጋር የሚታይባቸው ከመሆናቸው የተነሳ፣ ወደ ሥነ ጥበብና ሥነ ጽሑፍ የሚያመራውን የሥልጣኔ ጕዳና በትዕግስት፣ በእርጋታ፣በጽናት ለመንዝ ያስችላቸዋል ተብሎ አይታመንም፣ምክንያቱም ባህርያቸው ለተረጋጋ ሕይወት ተቃራኒ ነውና። ባለግብርናው ኢትዮጵያዊ ግን በአንድ ስፍራ ረግቶ መኖርን፣ ቤትና ጉልቻን መመሥረትን አስተምሯል።



ታሪክ ከመመዝገቡ በፊት ኩሻውያን ብረት ነክ መሳሪያዎችን በመፈልሰፍ የተፈጥሮ ኃይልን ለመጠቀም የቻሉ ነበሩ። ዛሬ ለግንባታ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ያበረከቱልን ለመሆኑ የግብጽ ቅርስን ላጠና የማያወላዳ ማስረጃዎች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል። ከነዚህም መካከል ለሰው ልጅ የዕድገት ግስጋሴ መነሻ የሆኑትን ሦስት ነገሮች ማለትም የብረት ማቅለጫ ምድጃን፣እሳትንና የመሰዊያ ስፍራን አፍሪቃዊው ለዓለም ያበረከታቸው ስጦታዎች ናቸው። ጥንታውያኑ እንደሚሉት አምልኮተ ፈጣሪንና መሰዋዕት ማቅረብን ያስተማሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ማንም ስለብረት ነክ ማዕድናትና የማቅለጥን ጥበብን ሳያውቅ ኢትዮጵያዊው ይህን ጥበብ አውቋል፣በፒራሚዶቹም ላይ ተጠቅሞበታል፣የአመራረቱንም ዕውቀትና ጥበብ ለዓለም አበርክቷል።

ዶነሊይ(Donnelly) እንደጠቀሰው ዛሬ በታሪክ የምንጠቅሳቸው ብሔሮች ባለፉት ሺህ ዓመታት ውስጥ አንድ የወፍ ዝርያን ብቻ ነበር ለማዳ ለማድረግ የቻሉት። ይህም ሆኖ ግን፣ሥልጣኔ የመነጨውና የተስፋፋው በኋላ ከተነሱት የሰው ዘሮች ነው በማለት እንደጉራ የምናወራውን ወሬ ወደ ጎን በመተው እውነቱን ለመቀበል ብንዘጋጅ ለሰው ዘር ሁሉ ጠቃሚ ይሆናል ብኋል።

የጥንቱ አፍሪቃዊ በሬን በቀንበር ማጥመድ አስተምሯል፣ላምን፣ በጎችንና ፈረሶችን ለማዳ አድርጓል። ለዚህም በቂ መረጃዎች አሉ። ስለዚህም ነበር በጥንቶቹ ኩሽ አፈታሪክ ውስጥ የእንስሳት ሚና በሰፊው ተጠቅሶ



Scanned by CamScanner

የሚገኘው:: በእስያ እንደነበሩት ኩሾች የአፍሪቃውም ኩሽ በተመሳሳይ ጊዜ ዝሆንን ለማዳ ለማድረግ ችሉአል:: ተቀርጸው የተገኙት ሃውልቶች እንደሚያሳዩት የአፍሪቃ አንበሳን ጭምር ለማዳ ማድረግ ችሎአል። እነዚህ ተስፋ የማይቆርጡ ኩሾች እንደ ስንዴ፣ገብስ፣አጃ፣ሩዝ የመሳሰሉትንና ሌሎች ለምግቦቻችን የምንጠቀምባቸውን ዕፅዋት ሁሉ ለስውነቶችን ተስማሚ በሚሆንበት ዘዴ የማዳቀል ጥበብ ካበረከቱልን እጅግ ብዙ ዘመናትን አስቆጥሯል፤የእነዚህ ዕፅዋትና አዝዕርት ወፍ ዘራሽ ምርጥ ኦሪጂናሌ ዘሮች ዛሬ ከዓለማችን ጠፍተዋል:: ያለእነዚህ ድንቅ የጥበብ ውጤቶች ምን እንመስል ነበር? እንደ ሬክሉስ አባባል፣ማሽላንና ቴምርን፣ ካፊርንና ቡናን እንዲሁም ሙዝን በተጨማሪም ከእንስሳት ውሻንና ድመትን አሳማንና አህያን፣በሬን፣በግንና ፍየልን ላበረከቱልን አፍሪቃውያን ባለውለታዎች ነን:: ለመጀመሪያ ጊዜ አፍሪቃን የጎበኙ ተጓዦች ምድሪቱን ሲገልጹ፤በከብቶች በረት የተሞላችና በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ልዩ የሆኑ የእንስሳት ዝርያዎች የሚኖሩባት፣እንስሶቻቸውን በልዩ ችሎታና ክህሎት የሚንከባከቡ ሰዎች ያሉባት ምድር መሆኗን ለማወቅ ችለዋል::

ከስሚዞንያን ኢንስቲትውት የተላከ ቦታኒስት በአፍሪቃ ምድር ወደ 15 ሺህ ኪሎ ሜትር በመጓዝ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የእጽዋትንና የአዝዕርትን፤ የሣር ዓይነቶችንና የፍራፍሬዎችን ዘር ለማሰባሰብ ችሏል:: እነዚህ ሁሉ የዕውቀትና ጥበብ ውጤቶች የጥንቱ ዘመን ሰዎች ስለተላለፉልን ተጠቃሚዎች ለመሆን በቅተናል:: የጥንቶቹ ድንቅ



ኢትዮጵያውያን የግብርና ሰዎች ያመርቷቸው የነበሩት ሎሚና የስኳር ድንች እኛ ከምናመርታቸው በጣም የተለየ ጣዕም ነበራቸው:: እነዚህ በአፍሪቃ የሚመረቱት ፍራፍሬዎች ጣዕማቸውና መጠናቸው ከሌላው የሚለዩትበት ምክንያት እንዲያው በአጋጣሚ የመጣ ሳይሆን ለዘመናት ባላሰለሰና ባልተቋረጠ የማዳቀል ጥበብና ጥረት የተገኙ በመሆናቸው ብቻ ነው::

እነዚሁ የጥንታዊቱ ዓለም ሰዎች ቋንቋን በተጨማሪ አበርክተውልናል:: ሜየርስ(Myers) እንደገለጸው፣ታሪክ መዘገብ ከተጀመረበት ዘመን ጀምሮ ዓለማችን በቋንቋ የበለጸጉ ሕዝቦች የመኖሪያ ስፍራ እንደነበረች ለማረጋገጥ ተችሎአል:: ይህም ለቀጣዩ ትውልድ ታላቅ ጠቀሜታ ነበረው፤ይህም ብቻ አይደለም፤ቋንቋውን ከፊደላት ጭምር ጋር ነው ያበረከቱልን:: እንደ ባልድዊን (Baldwin) መሰረት የመጀመሪያው የታሪክ ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረው ጽሑፍ የተገኘው ከአንድ የጋራ ምንጭ ሲሆን የፊንቂያውያን ሥነ ኪነት ደግሞ የተገኘው ከታውት ነው ይላል::

በአምልኮት ረገድ፣የጥንታውያኑ የኢትዮጵያ ሰዎች የሁሉ የበላይ የሆነውን አንድ ፈጣሪ አምላክ ብቻ ያመልኩ ነበር፣ አምልኮቱም ንፁህ ነበር:: መሪዎቻቸው፤ክህነትን ከንጉሥነት ጋር አጣምረው ከመያዛቸው ባሻገር በሞት በሚለዩበት ጊዜ ደግሞ የቅዱስነት ማዕረግ ይሰጣቸው ነበር:: ዘመናቱ እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ቅድመ አያቶቻቸው የነበሩትን እነዚህን ቅዱሳን በአማልክት ደረጃ በማክበር እስከ ማምለክ ተደርሶ



Scanned by CamScanner

ነበር:: ይህ ሁኔታ በአፍሪቃ ምድር ዛሬም በአንዳንድ ስፍራ አቆጥቁጦ በመታየት ላይ ይገኛል:: ስለሰው ዘር ምንጭና ዕድገት በማጥናት የሚታወቀው ተመራማሪው ፍሮቤኒየስ እንደሚለው፣"ኢትዮጵያ የጥንትነት ቀዳማይ ምድር ናት::" የጥንት ነዋሪዎቿ ከሰው ልጆች ሁሉ እጅግ ሃይማኖተኞች ነበሩ:: ሃይማኖትን በተመለከተ፣አንዳንድ ወገኖች ግብጽ ለሜሮይ ባለውለታዋ ናት ይላሉ:: ነገር ግን፤ይህንን አባባል ከኤትኖሎጂ አኳያ በጽኑ መቃወም ይገባል፣ምክንያቱም ኑብያኖች የራሳቸው የሆነና ለኋላ ቀራቱ ግብጽ ለማስተላለፍ የቻሉት ሃይማኖት የነበራቸው ስለመሆኑ ግብጻውያኑ ራሳቸው የሰጡት ምስክርነት ስላለ። (Voice of Africa, Vol. II, P.621)

በግብጽ ጥናት ሊቅ የተባለው ቻምፖሊዮን(Champollion) እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን መረጃዎቹን ባሰፈረበት ማስታወሻዎቹ ውስጥ እንደገለጸው፤በመጀመሪያ ከአቢሲኒያና ከሜሮይ የመጡ ሰዎች በግብጽ ታችኛው አባይ በመስፈር ቴብስና ኤድፎ የተባሉትን ጥንታውያን ከተሞች ቆረቆሩ ብሎአል:: የኋላ የኋላ ግን ይህ የተቀደሰ የኩሽ ወገን በ2ሺህ ዓመት ቅ.ል.ክ በተዋጊነቱ በሚታወቅና በተናቀ መደብ ተገልብጦ ስልጣኑን ተነጥቋል::

በንጉሥ ቶት፣በንጉሥ አሜን ራዕ እና በንጉሥ ኦሲሪስ አማካኝነት በተለያዩ ዘመናት ገዥ የነበረው የጥንቱ ዘር ሥርወ መንግሥቱን በመነጠቁ የተነሳ ለአዲሶቹ ገዥዎች ሥልጣኑን በመልቀቅ ወደ ምስራቅ



አቀጣጫ አቅንቶ የሚሰጹታሚያን ሜዳዎች በመቆጣጠር እስከ ሕንድ ድረስ ዘለቀ ነበር:: ምንም እንኳዋን ከግብጽ ጋር የነበራቸው ቅራኔና ጥላቻ በየጊዜው እየከረረ ቢሄድም፣በግብጽ የቀጠለው ንጉሣዊ አገዛዝ ግን በደማቸው ኢትዮጵያውያን በሆኑ ነገሥታት እየተያዘ ቆይቷል::

ሂረን(Heeren) እንደሚለው፣ በትክክል ለማገናዘብ የሚችልና በጥሩ መረጃ ላይ የተደገፈ ማንኛውም ተንኘ፣በግብጽ ሃውልቶች ላይ ተቀርፀው የሚያያቸውን ምስላት፣ቀለማት፣የፊት ገጽታ፣የአለባበስ ዘየ፣የመሣሪያ አስተጣጠቅ ከላይኛው አባይ ነዋሪዎች ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ይገነዘባል:: ዛሬ በኑብያኑ ምድር ማንነቱንና ሃይማኖቱን አጥቶና ተዋርዶ የሚታየው ዘር በአንድ የታሪክ ወቅት የግብጽ የገዥ መደብ እንደነበር አያጠያይቅም:: መታወቅ ያለበት ጉዳይ፣የኑብያ ዘር ከአረቢያ የመጣ አለመሆኑንና የቆዳ ቀለሙ፣ቋንቋው፤የአኗኗር ዘይቤው የተለየ ስለመሆኑ ነው:: ግብጻውያን፣ራሳቸው እንደሚሉት "በመጀመሪያ በእነርሱ ዘንድ እርሻም ሆነ መንግሥት ያልነበራቸው፣ያልሰለጠኑ፣ ከቁጡማ በተሠሩ የጐጆ ቤቶች ይኖሩ የነበሩ ሲሆን፣ቀጥሎ ከእነርሱ ለየት ያለ ቀለሙ የተለየ አንድ የሰው ዘር በመካከላቸው መጥቶ እንደሰፈረና ወደ ስልጣኔ ደረጃ እንዳደረሳቸው ይናገራሉ:: እነዚህ የተለዩ ናቸው የሚሏቸው ዘር ለኑብያኖች ቅድመ አያቶች እንደሆኑና ቅኝ ግዛቶቻቸውን በሌሎች ስፍራዎች ማለትም በግሪክ፣በካልቸስ፣በባቢሎንና በሕንድም ጭምር እንዳቋቋሙ ይናገራሉ::" በነዚህ ግዛቶች ገዥዎች የነበሩት መሪዎች ሁሉ ሥልጣነ ክህነትን ከንጉሥነት ጋር ያጣመሩ እንደነበሩ፤ይህንን



Scanned by CamScanner

በተመሰከተ የሚያረጋግጡ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሶሳን ጽሑፎች እስከ ክርስቶስ ልደት ዘመን ድረስ ዘልቀዋል:: በአሁኑ ወቅት እንኳን ከ2ሺህ የሚበልጡ የኢትዮጵያ ጽሑፎች ይገኛሉ:: በክርስትና ሃይማኖት ሰባኪነት ስም ወደኢትዮጵያ የገቡ የውጭ ሚሲዮናውያን፣እነዚህ ጽሑፎች የአረማውያን ጽሑፎች ናቸው በማለ ሰበብ ለማጥፋት ተልዕኮ ስለነበራቸው አጥፍተዋቸዋል የሚል እምነት አለ::

ከጥንቶቹ ጽሑፎች ከተረፉትና ወደ 2ሺህ ከሚጠጉ የኢትዮጵያ ጽሑፎች ብቻ ይህንን ያክል እውነተኛ መረጃ ከተገኘ፣መላው ጽሑፎች ተገኝተው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ሊፈቱ ስላልተቻሉት ሚስጢሮች ባወቅን ነበር:: ስለ ኢትዮጵያ ተጽፈው አሁን የተገኙት ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ ክርስትናን በተመለከተ ብቻ ናቸው ማለት ይቻላል::

ባራብራዎች/ኑብያኖች በቱርኮችና በአረቦች ላይ ጥላቻ አላቸው:: ፍሮቤኒየስ (Frobenius) እንደሚለው፣ኑብያኖች ክርስትናን የተቀበሉት በ500 ዓ.ም መጀመሪያ ገደማ ሲሆን፣ለአንድ ሺህ ዓመታት መሐመዳውያኑን በጽናት ተቋቁመዋል:: እስልምና በምድረ ግብጽ ክርስቲያኖችን ማስቃየት ሲጀምር "እጃችሁን አንሱ" በማለት ለአረቦቹ ባስተጋቡት የማስጠንቀቂያ ድምጽ የተነሳ፣ መሐመዳውያኑ ኑብያኖቹን በመፍራት ከግብጽ እጃቸውን ለማንሳት ተገደው ነበር:: ወደ ምድራቸው ዘልቀው ለመግባት የሞከሩት ፀጉረ ልውጥ የሚሉአቸውን ሁሉ ለመቋቋም ኑብያውያን ብዙ ጊዜ ሞክረዋል፤በጦርነት ጊዜ በእነዚሁ ፀጉረ ልውጦች እንዳይደፈሩ፤የኑብያ እናቶች ሴቶች ልጆቻቸው እስከመግደል



ይደርሱ እንደነበርና ይህንንም እንደመልካም የሞራል ግዴታቸው አድርገው ስለመቁጠራቸው ይነገራል::

የወረራው ዓላማ በርግጥም በሀብት የበለጸገችውን ይህችን የመሰለች ምድር ለመንጠቅ ያነጣጠረ ስለነበረ፤እነዚህን ወራሪዎች ለመከላከል በጽኑ ቁርጠኝነት መቆማቸውና መዋጋታቸው ተገቢና ትክክልም ነበር:: መጨረሻው ሳያምር ቀረና ምድራቱ በፍርስራሽ ክምር ተሞላች እንጂ! እንደ ሰር ሳሙኤል ቤከር (Sir Samuel Baker)አገላለጽ እስከ 1862 ዓ.ም እ.ኤ.አ በበርበርና በካርቱም መካከል የሚገኘው የአባይ ወንዝ ዳርቻ በሕዝብ የተሞላ፤ መላው መሬት የታረሰ ይገኝ የነበረው ምርት የደለበ ነበር:: ቱርኮች ምድራቱን በተቆጣጠሩበት በሠላሣው ዓመታት ግን ወደ ምድረ በዳነት ተለውጦ ነበር::

እነዚህ ወራሪዎቹ ቀድሞ ለመስኖ ቦይ ውሃ መሳቢያነት ይውሉ የነበሩትን መዘውሮች ደብዛቸውን አጠፉ፣በዚህም የተነሳ የመስኖ ቦዮቹ በደለል ተሞልተው የታነቀ ጉሮሮ ይመስሉ ነበር::በጅ የተባለው ጸሐፊ እንደዘገበው፣ከጦርነት የተረፉት ጥቂት ነዋሪዎች ራቁታቸውን ሆነዋል፣በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ ቀስ በቀስም ወደ ሞት አፋፍ እየተንዙ ነበር:: በዚያ ቀዝቃዛ ለሊት ያለ ልብስ ያድራሉ፣መድረሻ የላቸውም:: ሃገራቸውን ይወድዳሉና ወዴት ይሂዱ! በማለት በስዕላዊ አገላለጽ ገልፆታል:: የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ አረቦች የታችኛውን ግብጽ በ700 ዓ.ም በተቆጣጠሩ ጊዜ ለዘመናት «ረቱ » በመባል የሚታወቀውን የግብጽ ዜጋ ዛሬ ፈላሂን ተብሎ ለሚጠራውና አረብኛን ብቻ ወደሚናገር



Scanned by CamScanner

ሰው ስለጠጠውታል:: የጥንቶቹ ግብጻውያን፣ከግሪኮች፣ከሮማውያንና ከአረቦች ጋር በመጋባታቸው የተነሳ ዛሬ የሚታየው የግብጻዊ አካላዊ ገጽታ ከቀድሞዎቹ የተለየ ለመሆኑ በቅቷል:: የአባይ ኑብያዎች ግን ክብራቸውን ጠብቀው አልተዳቀሉም:: የጥንታዊት ኢትዮጵያ ኤምፓየር በደቡብና በሰሜን በነበሯት መዲናዎች አማካኝነት የእስልምናውን ግስጋሴ በመግታት ለአንድ ሺህ ዓመታት እስከ 1316 ዓ.ም ቆይታለች:: ሆኖም ግን በኑብያ የነበረው የክርስቲያን ንጉሣዊ አገዛዝ ከተገረሰሰም በኋላ፣የኑብያ አርሶ አደር ይወደው የነበረውን የካም ነገድ ቋንቋ እስካሁን ድረስ በጥንቃቄ ጠብቆ አቆይቶታል፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት የማንነት መገለጫው ስለነበር ነው:: ከ1316 ዓ.ም በኋላ ግን ኑብያኖቹ የክርስትና እምነታቸውን በግድ እንዲቀይሩ የጅምላ ጭፍጨፋና ለማመን የሚዘገንን ጥፋትና ውድመት ደርሶባቸዋል:: ከነዋሪዎቹ ሰማንያ በመቶው ተገድለዋል፣የታወቀው የእርሻ ቀጠናቸው ወደ ባድማነት ተለውጧል፣ከብቶችና ሰዎቻቸው ታርደዋል፣የኢትዮጵያ ልጃገረዶችም ተደፍረዋል::

የዛሬይቱን ኢትዮጵያ እንደዚህ ባድማ ሆና ለተመለከታት፣የቀድሞ ተንኮኞችና የሰው ዘር ተመራማሪዎች እንዲሁም ጂኦሎጂስቶች የሰጡትን ድምዳሜ ለመቀበል ያዳግተዋል:: ዘመኑ የራቀ በመሆኑ የስልጣኔዋን ዱካ ለማወቅ እስኪያዳግት ድረስ ደብዛው ጠፍቷል:: የኢትዮጵያ ሥልጣኔና ኃይል መዳከም የጀመረው በፋርስ ንጉሥ ካምቢሰስ ዘመነ መንግሥት እንደነበር የታሪክ መጽሐፍት ዘግበዋል::



ቅርስን በተመለከተ በጥንቱ መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሰው የሚገኙት ፍርስራሽ ከተሞች መገኛቸው ከላይኛው አባይ ምድር መሆኑ በግልጽ ይታወቃል፣ሆኖም ግን አንባብያን ከታችኛው አባይ ምድር እንደሆነ አድርገው ሲገነዘቡት እናያለን:: የዓለማችን ሙዚየሞች የተሞሉት በኢትዮጵያ ሥነ ጥበባት ውጤቶች ሆነው ሳለ የቀረቡት እንደግብጽ ቅርስ ተደርገው ነው:: በ1820 ዓ.ም ፌርሊኒ (Ferlini) የተባለ ተመራማሪ፣በአንዲት ታላቅ የሜሮይ ንግሥት መካነ መቃብር ውስጥ እጅታው በዳዮኒሰስ ጭምብል የተጌጠ፣ከነሐስ የተሰራ ጽዋ፣የአንገት ሀብሎች፣የእጅ አምባሮች፣ቀለበቶችና ሌሎች የጌጣ ጌጥ ቁሳቁሶችን ለማግኘት ችሏል:: ዳዮኒሰስን፣ግሪኮች ባኩስ ይሉታል:: እነዚህ ጌጣ ጌጦችና የነሐስ ጽዋዎች፣ ዛሬ በሙኒክ ቤተ ቅርስ ይገኛሉ:: ፌርሊኒ፣ባገኛቸው በእነዚህ ቅርሶች ዕደ ጥበባዊ ጥራት በጣም ከመደነቁ የተነሳ፣ ግሪኮች እንኳን እንደዚህ የሚቀራረብ ያማረ ሥራ ለመሥራት እንዳልቻሉ ገልጿል::(Egyptian Soudan, Budge).

በ1863 ዓ.ም፣ማርየት(Marriette) በጀበል ባርካል ከሚገኙት ሃውልቶች መካከል ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን አምስት ምሰሶዎችን አግኝቷል:: በእነዚህ ምሰሶዎች ላይ የተገኘው መረጃ የሚያረጋግጠው በኋለኞቹ የግብጽ ታሪክ ዘመናት፣ኢትዮጵያ በግብጽ ሥርወ መንግሥት ውስጥ የነበራትን ቦታ ነው:: እነዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታት መዲናቸውን በኑብያ አድርገው ግብጽን ይገዙ እንደነበርና፣ከነገሥታቶቹም መካከል ንጉሥ ታርካካ የተባለው የጦር ሠራዊቱን እስከ እስያ ድረስ ስለማዝመቱ



Scanned by CamScanner

Brought to you by:
**Ethiopian Bookstore**

https://t.me/etbookstore

Scanned by CamScanner

ተጽፏል። ይህ ድርጊቱ፣ከቀድሞቹ የኢትዮጵያ ገዥዎች ያልተለየ የሚያደርገውና የቀድሞ ነገሥታቶችን ፈለግ ስለመከተሉ አመላካች ነው።

በአውሮፓ የሚገኙት ሙዚየሞች ወይም ቤተ ቅርሶች፣ከጀበል ባርካ ጥቂት ሃውልቶችን እንዳሰባሰቡ ይታወቃል። ስፍራው በቤተ መቅደሱ አካባቢ በርካታ የፒራሚድ ስብስቦች ያሉበት ነው። ኑሪ በተባለው ቦታ ደግሞ ወደሃያ አምስት የሚጠጉ ምሰሶ መሰል ቅርጽ ያላቸውና ሕንጻውን ተሸክመው የሚታዩ የድንጋይ ማዕዘናት ይታያሉ። እስከ ቅርብ ዘመናት ድረስ ኢትሩስካኖች የፈለሰፉት የሕንጻ አሠራር ነው ተብሎ ይታመን ነበር። በ6ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ኑብያ፣የግብጽ ንጉሣዊ መንግሥት አካል በነበረችበት ወቅት፣በሃውልቶቹ ላይ ተጽፈው የተገኙት የኢትዮጵያ ጽሑፎች የሚያሳዩት ንጉሡ በግብጽና በኢትዮጵያ ምድር ላይ ባለሙሉ ሥልጣንና የሁለቱ ምድሮች ገዥ ስለመሆኑ፣ኡ፣ራ፣ኤ የሚል ቃል የመንግሥቱ ምልክት እንደነበረ፣ ሲሆን፣ በሜሮይ ከተማ ፒራሚዶች ላይ ተጽፈው የተገኙት መረጃዎች ይህንኑ ያጠናክራሉ።

የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች፣በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ከተማ ናፓታ፣2ሺህ ዘመናትን ያስቆጠሩ የንጉሣውያን ቤተሰቦች መካነ መቃብራት በቁፋሮ አግኝተዋል። በተለይ ኑሪ በተባለ ስፍራ፣የሃያ ነገሥታትና የሃያ አምስት ንግሥቲቶች መቃብርን መርምረዋል። እነዚህ



ገዥዎች የነገሡበት ዘመን ከ600 እስከ 250 ቅ.ል.ክ ሲሆን፣ ካንዳስ ተብሎ ይጠራ ለነበረው የተከበረ የነገሥታት ዘር መካነ መቃብር እንደ ነበር ያሳያል። የተገኙት ጌጣ ጌጦች በጣም የተዋቡና የዕደ ጥበብ ሥራዎቻቸው ንጹህ የሜሮይ ውጤቶች ነበሩ፣በታላቋቱ ንግሥት እግር ስር የሚታየው ቅርጽ የሰሜንና የደቡብ አማልክት ሁለቱን ምድሮች ሲያስተሳስሩ የሚያሳዩ ሲሆን፣ ለሁለት የተከፈሉት እነዚህ ምድሮች አስቀድሞ አንድ ስለመሆናቸው የሚገልጽ ይመስላል። ይህንን ትስስር የሚያመላክቱ መረጃዎች በግብጽ የመጀመሪያ ታሪክ ገደማ ተጽፈው የተገኙ ሲሆን፣ እንደ ማስረጃዎቹ መሰረት የግብጽ ፈርዖኖች የሹመት ስም የሁለቱ ምድር ገዥዎች መሆናቸውን የሚያመላክት ነው። የሜሮይን ፍርስራሾች ያጠናው ተመራማሪ ሆስኪንስ በዚያ ስፍራ የሚታየው ሁሉ የአንድ ታላቅ ሕዝብ ድንቅ የሕንጻ ንድፍ ዕውቀት እንደነበር የሚያረጋግጥ ነው ብሎታል። ጊዛ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ከሚታዩት ፒራሚዶች ይልቅ በሥነ ሕንጻ ንድፍ የላቁና በውበታቸውም የተለዩ ያደርጋቸዋል ብሏል። የተገኙት መረጃዎች የሚያመላክቱት የገዥዎቹ የፊት ገጽታና የፀጉር አሠራር የኢትዮጵያዊ መለያ እንደነበርና በወቅቱ የሚጠሩበትም የንጉሥነት ስም፣ከአሜን ራዕ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ነው።

በኑብያ ተገንብተው ከነበሩት ቤተ መቅደሶች ጥቂቶቹ በአሜን ራዕ ስም ይጠሩ በነበሩት ነገሥታትና ንግሥቲቶች ስም ሲሆን፣ከነዚህም ነገሥታት መካከል ንጉሥ ታርካካና ንጉሥ ፓንክሂ ግብጽን በኃይል በያዙበት ጊዜ ስላደረጉት ጦርነት የሚያሳይ የተቀረጸ ምስል ተገኝቷል።

ከ22ኛው የግብጽ ንጉሣዊ ሥርወ መንግሥት በኋላ ግብጽ በእጀጉ በውጭ ዜጎች በመዳቀሏ የተነሳ ለብዙ ዘመናት ቴብስ ላይ ሆነው ግብጽን ሲገዙ የነበሩት የአሜን ካህናትና ነገሥታት ዝርያዎች ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል:: በዚህ በተከሰተው ሁኔታና እንዲሁም በግብጽ ውስጥ ለውጭ ዜጎች ይደረግ የነበረውን እንክብካቤ በመቃወም 240 ሺህ የግብጽ ወታደሮች ከድተው ወደ ኢትዮጵያ ተቀላቅለዋል:: የግብጹ ፈርዖን በሚቻለው ሁሉ በማግባባት የከዱትን ወታደሮች ወደሃገራቸው እንዲመለሱ ሙከራ ቢያደርግም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የተነሳ በኢትዮጵያ ቀርተዋል::

ከግብጽ በስተደቡብ የሚገኘው ምድር የኢትዮጵያ ምድር በመባል ይታወቅ ስለነበር፤ኑብያ የሚለውን ስም የጥንቶቹ ሰዎች አያውቁትም፤ የኑባ ነገድ ኮርዶፋን ተብሎ ከሚጠራ ስፍራ የመነጨ ነው ተብሎ ይታመናል:: በአባይ ወንዝ ዙሪያ ያሉት ኑባዎች ከኮርዶፋኖቹ ጋር በጣም የተሳሰሩ በመሆናቸው የተነሳ ብሪታኒካ በቅጽ 17 ላይ ይህንኑ ነገድ የኔግሮ ዝርያ ይለዋል:: የመኖሪያ ስፍራቸው የሚገኘው ግብጽን ከሶአዳን በሚያካልለው ድንበር አካባቢ ነው:: ነዋሪዎቹ በአነስተኛ ንግድ፤በዕደ ጥበብ አምራችነት፤በተሸካሚነትና በወታደርነት ሙያ በግብጽ ውስጥ ይኖራሉ::የታማኝነት፤የደስተኛነት እንዲሁም የቁጡነት ባህርያት ይታይባቸዋል::የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ገላጭነት ያለው ሆኖ የሚያስተጋባ ዓይነት ድምጽ አለው:: እንደኬን አገላለጽ፤ ከነዚህ ሕዝቦች መካከል ከሞላ ጎደል ማንበብ፤መጻፍና ሂሣብን የማያውቅ አልነበረም::



በርካታ ኑብያውያን በግብጻውያን ሃውልቶች ላይ ስለተቀረጹትና «ረቱ» ስለሚባሉት ምስሎች ያውቃሉ:: ኢትሩስካኖች በቀረጿቸው ሃውልቶች ላይ የሚታየው ደግሞ አሁን እየተጠቀምንበት ያለውን የግብጻውያን አማልክት የፀጉርና የጽሒም አሠራር ፋሽን ነው:: የኢትዮጵያ አምላክ ተብሎ ይጠራ የነበረውና የበርካታው የግብጽ ንጉሣውያን ቤተሰብ የዘር ግንድ መሠረት መሆኑ የሚታወቅለት አሜን ራዕ ከግብጻውያን ነገሥታት መካከል አስፈሪ ነበረ ይባላል:: የቆዳው ቀለም ጥቁር ሰማያዊ ነበረ:: ግብጻውያን የርሱን የፊት ቀለም ለመግለጽ ፈልገው በስዕላታቸው በጥቁር ቀለም ላይ ሰማያዊ ቀለም በመደረባቸው የተነሳ የፈለጉትን ለማሳየት ሳይችሉ ቀርተዋል፤ስለሆነም የለየለት ባለጥቁር ቆዳ አስመስለውታል:: ነገሥታት እንደ አምላክ በሚቆጠሩበት በዚያ ዘመን፤ የሶአዳን ምድር የግብፅ ተቀጥያ ተብሎ በሚታወቅበት በዚያ ዘመን፤ ከደረጃ አኳያ ሲታይ የሶአዳኖቹ አምላክ ከግብጾቹ አምላክ ጋር እኩል ነበር:: በግብጽ ቴልሜስ ቤተ መቅደስ ውስጥ ተስሎ እንደተገኘው ራሱን የደቡብ ንጉሥ ልጅ ብሎ የሚጠራው ቶትመስ ሣልሳዊና የእርሱም ልጅ አሜን ሆቴፕ ለኑብያ አምላክ መብዓ ሲያቀርቡ ይታያል::

ሬክሉስ እንደሚገልጸው፤ዶንጎላ ተብሎ በሚጠራው በቀድሞዋ የኑብያ መዲና ፍርስራሾች ውስጥ የሚታዩት ብዛት ያላቸውና ምርጥ የሆኑ የጥንት የሕንጻ ሥራዎች አስደናቂ ከመሆናቸም በላይ የሕንፃዎቹ ምሰሶዎች ውበት ከግሪኮች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ቢባል ማጋነን

አይሆንም። በኑብያ የተገነቡ የመከላከያ ምሽጎችና የጥበቃ ማማዎች በብዛት ይታያሉ። እነዚህ ምሽጎች በአውሮፓ የፊውዳል ስርዓት በነበረበት ዘመን ከተሠሩት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ፣እነዚህን ምሽጎች የገነቡት የኩሽ ሰዎች ናቸው ተብሎ ይገመታል። ይህ አሠራር በአቢሲኒያ ያለ ሲሆን፣የኑብያኖቹ ምሽጎችና ማማዎች ከመሠረታቸው ሰፋ ያሉና ወደ አናታቸው እየሾጠጡ የሚሄዱ ናቸው። ፈርዖን ራምሴስ ካልዓይ /2ኛ/በናፓታ ከተማ ለአሜን ራዕ ቤተ መቅደስ ከቋጥኝ አስፈልፍሎ ያሠራው ቤተ መቅደስ በታላቅነቱና በውበቱ በመላው ግብጽ ምድር ለተመሳሳይ ዓላማ ከተሠሩት ሁሉ የሚበልጥ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የሃርቫርዱ ዩኒቨርሲቲ የቁፋሮ ተልዕኮ ቡድን ያገኘው መረጃ የሚያመላክተው ከጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ንጉሣዊ መንግሥት ግዛት አንዱ ሳባዊ ወይም ሼባዊ በሚል የመጠሪያ ስም የነበረው ሲሆን በዚሁ ዘመነ መንግስት ነበር ንግሥት ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን ከፍተኛ ገፀ በረከት በመያዝ የሄደችው። የዕብራውያኑ ታሪክ ፀሐፊ ጆሴፈስ፣ንግሥተ ሳባን የኢትዮጵያና የግብጽ ንግሥት ብሏታል፣ይህንን ያለበት ምክንያት በዚያን ዘመን ሁለቱ ምድሮች ተብለው ከሚጠሩት ውስጥ ግብጽ አንደኛዋ በመሆኗ ነበር።



# ምዕራፍ አምስት

## ቅድመ ታሪክ ግብጽ የአስደናቂ ነገሮች ምድር

ግብጽ የቀድሞ መጠሪያ ስሟ ክሜም ወይም ጥቁር ምድር ይባላል። ይህ ስም ለግብጽ የተሰጣት ስለአፈርዋ ጥቁርነት አልነበረም፣ የስሙ ይዘት የጥንት ነዋሪዎቿን የቆዳ ቀለም የሚያመላክት ስለሆነ እንጂ። የአባይ ገፀ በረከት ተብላ የምትጠራዋ ታችኛዋ (ታህታይ) ግብጽ፣ ከዚህ ታላቅ ወንዝ በተገኘ አፈርና ደለል የተመሠረተች በመሆንዋ፣ ግብጽ ያለአባይ ወንዝ ጭው ያለች በረሃ ትሆን እንደነበር አሌ አይባልም። በዚህም የተነሳ የቀደምት ነዋሪዎቿ ከኋለኞቹ ይልቅ ስለ አባይ ወንዝ መነሻ ምድር ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። እንዲሁም በዘመናችን፣ሊቭንግስተን የተባለው ተጓዥ፣የነጭና የጥቁር አባይ ወንዞችን መነሻ ስፍራ ለማወቅ እስከ ምድር ወገብ ድረስ ተጉዟል። የአባይ ወንዝ ዙሪያ ገብ የሆነው ምድር በየዓመቱ ከሚያገኘው የደለል አፈር ክምችት የተነሳ ከፍታው ጨምሯል፣ወንዙ በክረምት ወራት ከዳርቻው ወጥቶ ካልፈሰሰ ደግሞ ድርቅና ረሃብ ይከተላል ተብሎ ይፈራል። በሌላ በኩል በወንዙ መሙላት ወቅት የግብጽ ከተሞች መጥለቅለቀ የተለመደ ሁኔታ ነበር።

ግብጽ፣በዚያ ሩቅ ዘመናት በሁለት የተለዩ ዘሮች ወይም ከአንድ ዘር በወጡና በግልጽ ልዩነት በነበራቸው የሁለት ዘሮች የመኖሪያ ምድር

ነበረች። ጥንታዊ መዛግብት እንደሚመሰክሩት በዚያ ዘመን የግብጽ የገዥ መደብ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ኃያልና ተደማጭነት በነበራቸው የካህናት ወገን ይደገፉ ነበር።

"ይህ ወገን፣ከካህናት በተጨማሪ ዳኞችን፣ሐኪሞችን፣የሥነ ክዋክብት ጠበብቶችን፣የሥነ ህንፃ ንድፍ ባለሙያዎችን በአጭሩ ከፍተኛ ባህልና ዕውቀት በነበራቸው ሰዎች የተሞላ ከመሆኑ ባሻገር፣ በግብጽ የነበረውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አደራጅቶ ይመራ ነበር"። (Biblical Literature)

ካሉሜት(Calumet) ከጥንት መረጃዎች እንዳገኘውና እንደመሰከረው፣ እንዲሁም በቅርብ የተደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዳረጋገጡት፣ሥልጣኔና ባህል ወደ ግብጽ የገባው ከደቡብ አቅጣጫ በተለይ ከሜሮይ ነበር። ግብጽ በመጀመሪያ በተለያዩ ጊዜያት በበርካታ ንጉሦች ስትገዛ ቆይታ ቀስ በቀስ በአንድ ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት የአገዛዝ ሥርዓት ሥር ለመሆን እንደበቃች ታሪክ ያረጋግጣል። መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት፣የመንግሥቱ መሪ ብዙውን ጊዜ ሥልጣነ ክህነትንና ንጉሥነትን ጨምሮ ይይዝ ነበረ። በሂንዱዎች ቅዱሳት መጽሐፍት ተጽፎ እንደተገኘው "የጥንቱ ዘር" ግብጽን ለማስተዳደር ወደታችኛው ግብጽ ወርዶ የአባይ ወንዝ ወደ ባህር በሚገባበት ደለላማ ምድር/ዴልታ/ መስፈሩን ይናገራሉ። መጽሐፍቱ፣የአባይ ወንዝ የጨረቃ ተራሮች በሚባለው ስፍራ አልፎና የባራብራ ምድርን አቋርጦ



እንደሚጓዝ ይገልጻሉ። በንጉሥ ሜነስ ዘመነ መንግሥት ደግሞ መላው ግብጽ ከቴብስ በስተቀር ረግረጋማ ምድር እንደነበረ ሄሮዶተስ በ2ኛው መጽሐፉ ጽፏል። የሞኢሪስ ሐይቅ የሸፈነውን ምድር ጨምሮ እስከ ሜዲተራንያን ባሕር ዳርቻ ለመጓዝ ሰባት ቀናት ይወስድ ነበር። ዳዩደረስ ሲኩለስ በጻፈው 3ኛው መጽሐፉና እንዲሁም በኢትዮጵያ መጻሕፍት ተጽፎ እንደሚገኘው፣ ኦሲረስ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ግብጽ በኋለኞቹ ዘመናት ከኢትዮጵያ ግዛት ተቆርሳ የተወሰደች ምድር ናት።

ግብጽ፤ በኢትዮጵያ ከመያዟ በፊት የማንም አልነበረችም፤ ምክንያቱም በባህር የተሸፈነች ምድር ስለነበረች። ከባህሩ መሸሽ በኋላ ደግሞ ከአባይ ወንዝ በተገኘው ደለላማ አፈር ላይ የተመሠረተች ሆነች። ይህ ምስክርነት በጂኦሎጂም ጥናት ተረጋግጧል። እንደ ሬኔል(Rennel) ጥናት መሠረት፣ፒራሚዶቹ የሚገኙበት ሥፍራ በባህር ተሸፍኖ እንደነበር ያለ ጥርጥር አረጋግጦአል። ዛሬ ከሜዴተራኒያን ባህር ውሃ ልክ ከ20 ሜትር እስከ 24 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘው የአባይ ወንዝ ሲሞላ እነዚህኑ አለቶች ሲሸፍናቸው ይታያል። ግብጽ በራሷ የተመራ ረጅም የሚባል የሥልጣኔ ዘመን እንደአላሳለፈች ሬናን(Renan) ይገልጻል።ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት አቅኚዎች የሆኑት ኩሾች ሥልጣኔን በቀጥታ ከኢትዮጵያ ይዘው ስለ መጡ ወደ ስልጣኔ ጎዳና እንድታመራ አድርገዋታል ባይ ነው። ለይህም ነው የግብጽ ሥልጣኔ ሜነስ ከተባለው ንጉሥ ጋር የተያያዘ አይደለም ተብሎ የሚነገረው። የነገድ አባት

አብርሃም ከ4 ሺህ ዓመታት በፊት ወደ ግብጽ ምድር በወረደበት ዘመን፣በግብጽ ተገንብቶ ስለነበረው ስፊንክስ(Sphinx) ምንነትና ትርጉም እንዲሁም ምስጢርና መቼ እንደተገነባ በግልጽ የሚታወቅ ነገር አልነበረም በማለት ሳይስ ጽፏል።ስፊንክሱም ሆነ ፒራሚዶቹ የአንድ የጥንታዊ ዘር ሃይማኖታዊ ምልክትና መገለጫ እንደሆኑ ይታመናል።

ባልድዊን(Baldwin)፤ ዳዮዶረስ ሲኩለስን (Diodorus Siculus) ጠቅሶ እንደጻፈው የጥንታዊት ግብጽ ሕጎች፣ባህሎች፣ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት፣ፊደላቶች ከጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላሉ። ይህም የሚያረጋግጠው ግብጽ የቅኝ ገዥዋን ባህል መውረሷን ብቻ ነው። የኋለኞቹ ዘመናት ግብጻውያን ደግሞ እንደሚሉት እነርሱም ሆኑ ሥልጣኔያቸው የተገኘው ፑንት ተብሎ ከሚታወቅ የጥቁር ነገድ ነው። አንዳንድ ተመራማሪዎች የግብጽን ሥልጣኔ ከምስራቅ አቅጣጫ እንደመጣ አድርገው ሊገልጹ ቢፈልጉም በርግጠኝነት የተገኙ መረጃዎች የሚገልጹት ግን የግብጻውያን ስልጣኔ ከራሳቸው የፈለቀ እንዳልሆነ ወይም ከነርሱ የቀድሞ ዘር የተላለፈ አለመሆኑን ነው። ሥልጣኔው ከምስራቅም ይሁን ከሰሜን አቅጣጫ ወደግብጽ አልገባም፤ይልቁንም በጅ(Budge) እንዳረጋገጠው ያለ ጥርጥር ከግብጽ በስተደቡብ አቅጣጫ ካለ አንድ የጥቁር ሕዝብ ምድር ብቻ ነው። ሰርጊ(Sergi) እንደገለጸልን፤ በፍሊንደርስ፣በፔትሪና በዳሞርጋን አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች የሚያረጋግጡት የቅድመ ታሪክ ግብጽ ሥልጣኔ ከቶም የምስራቁ ስልጣኔ ተጽዕኖ የሌለበት መሆኑን ነው።



የመጀመሪያዋ የግብጽ ነዋሪዎች የከብት ቆዳ ለባሾችና በተፈጥሮ የተሳሉ የድንጋይ መሣሪያዎች ብቻ የነበሯቸው ስለመሆኑ አርኪኦሎጂካዊ መረጃዎች አሉ። ቤቶቻቸው ከጭቃ የተሰሩና የሳር ክዳን የነበራቸው ምግባቸውን የሚያገኙት ደግሞ እንስሳትን በማደን ሲሆን፤ በሶሁዳን ምድር ይኖሩ በነበሩት ሕዝቦች ግን እንደዚህ የመሰለ ኋላቀር የአኗኗር ዘይቤ አልታየም። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ግብጻውያን እየኖሩ ሳሉ ነበር ከደቡብ ምድር የመጡ አቅኚዎች የመዳብና ነሐስ ሥራን፣የአዝዕርትና የእንስሳት ማዳቀልን፣የጠብ ሥራ ጥበብን ለምጽራይም ልጆች ይዘውላቸው መጡ የሚባለው፣ ስለዚህም ነው የታሪክ ሰዎች ጥንታዊቷ ግብጽ ከቀደምት ነዎሪዎቿና ከአቅኚዎቿ ውህደት የተነሳ በእግሯ ለመቆም የበቃችው የሚሉት።

የግብጽ የበላይነት በሰፈነበት ዘመናት የነበረው የሰዎች ራስ ቅል ቅርጽ ሞላላ የመሆኑ ጉዳይ የሚያመለክተው የኢትዮጵያዊነት መለያ መሆኑን ሲሆን፣እንደ ሳይስ አባባል ጥንታውያውኑ ግብጻውያን የዚህን ዓይነት የራስ ቅል ቅርጽ ነበራቸው፤በኋላ ግን ከሌሎች ዘሮች ጋር በመደባለቃቸው የተነሣ የራስ ቅላቸው ከሞላላነት ይልቅ ወደጎን የተለጠጠ ሆኖአል።ጀምስ ሔንሪ ብሬስትድ(James Henry Breasted) የተባለው የዓለማችን ታዋቂ አርኪኦሎጂስት በግብጽ ባደረገው የቁፋሮ ጥናት 1400 ዓመት ቅ.ል.ክ የነበረን አንድ የስዕልና የቅርጻ ቅርጽ እስቱዲዮ አግኝቷል። ይህ ስቱዲዮ የቀራጺው የቱትመስ ሲሆን፣በዚያ

የተገኙት ስዕላትና ቅርጻ ቅርጾች ሁሉ የአፍሪቃዊ ገጽታን ያለጥርጥር የሚያመላክቱ ነበር::

ፈርዖን ሜኔስ በግብጽ የነገሠበት ዘመን ቢያንስ 4 ሺህ ዓመታት ቅ.ል.ክ እንደነበር ይታወቃል:: በአንድ ቤተ መቅደስ ስለዚሁ ፈርዖን የተገኘ ቅርስ እንደሚያሳየው የቴብስ ከተማ ነዋሪ መሆኑን የቴብስ የመጀመሪያ ነዋሪዎች ደግሞ ከኑብያ የመጡ ስለመሆናቸው ነው::በሌላ አነጋገር ከሜሮይ ወደቴብስ ሄደው መስፈራቸውን የሚያረጋግጥ ነው:: ሜኔስ ከላይኛው ግብጽ የመጣ የካህናት ዝርያ የነበረ ሰው ነበር፤ እርሱ በግብጽ ከመንገሡ በፊት በርካታ የሥልጣኔ ዘመናት ግብጽ እንዳለፈች በንሰን ገልጿል:: የዘመናት ብዛት ሳያጠፋቸው በአስደናቂ ሁኔታ በሃውልቶቿ ላይ ተጽፈው የተገኙት ጥንታዊ መረጃዎች ለዚህ ማረጋገጫዎች ናቸው:: ሌፒስ(Lepius) እንደሚለውና ከተገኙት የፍርስራሽ ቅርሶች ለማወቅ እንደተቻለው ከ6 ሺህ ዓመታት በፊት ማለትም በ4ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ግብጽ በከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ላይ ትገኝ ነበረች:: በእነዚሁ ዘመናት፤ግብጽ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ስለነበረች ሥነ ጥበቧና ሃሣቦቿ ሁሉ ንጹሕ እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል:: አስገራሚው ነገር ጥንታውያኑ ቤተ መቅደሶች በሙሉ በውስጣቸው በጽሑፍ የተሞሉ ነበሩ:: ይህም የሚያመላክተው በዚያ ጥንት ዘመን ትምህርት ለሁሉ የተዳረሰ ስለመሆኑ ነው:: ከካህናቶቿ ጽሑፎች በተጨማሪ የተራ ሠራተኞቿ ጽሑፎች ጭምር በአለቶች ላይ ተቀርፀው ተገኝተዋል::



በእኛ የታሪክ ዘመን አቆጣጠር መሠረት በጽሑፍና በቅርጻ ቅርጽ ተመዝግቦ የተገኘው መረጃ ታሪክ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ቢሆንም፣ ከዚያ በፊት ስለነበረው ሥልጣኔ ምን ያክል ዓመታን እንዳስቆጠረ በርግጠኝነት ለመናገር አዳጋች ነው:: ሆኖም በጥቅሉ ማለት የሚቻለው፣ ግብጽ እጅግ በርካታ ቅድመ ታሪክ ዘመናትን ማሳለፏንና በነዚሁ ዘመናት እስከአሁን ለተጠቀሰው የሥልጣኔ ደረጃ መብቃቷን ነው:: የቤሮሰስ፣የማንቴኦና የሂንዱ የታሪክ መጽሐፍትን የዘመናት አቆጣጠር ያጠኑ ተመራማሪዎች እንደአሉት ለመረዳት ያልቻልዋቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ:: ከጥፋት ውሃ በፊት በምድር ይኖሩ የነበሩት የመጀመሪያው ዓለም ሰዎች ጥቁሮች ብቻ ነበሩ የሚል እምነት አለ:: ይህም ከዘፍጥረት እስከ ጥፋት ውሃ ድረስ የነበሩትን ዘመናት ያጠቃልላል:: በሳይንሳዊ ጥናት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የታሪክ ጸሐፍት የጸፏቸው የዘመናት ቅደም ተከተልና በቁፋሮ የተገኙትን መረጃዎች ስናነጻጽር በያሻር መጽሐፍ ተጽፎ ከተገኘው የዘመን አቆጣጠር የበለጠ ዘመናትን ዓለማችን እንዳሳለፈች የሚያመላክት ነው:: በርግጥም፣ እንደእኛ ዘመን አቆጣጠር መሠረት በምድር የሰው ልጅ ታሪክ አጭር ቢመስልም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ የምናገኘው መረጃ፤በምድር አንድ ሺህ ዓመታት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አንድ ቀን መሆኑን ነው::

የሴይስ ካህናት፤ሶሎንን እንዲህ አሉት "እናንተ ግሪኮች ጥንት ስለነበረው ዕውቀት አዲሶች ናችሁ:: በእናንተ ዘንድ በጥንት ዘመን ስለነበረው ነገር

አንዳች አታውቁምና መሃይሞች ናችሁ:: በእኛ ቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የ8 ሺህ ዘመናትን ታሪክ መዝግበን አስቀምጠናል:: ከፈለጋችሁም ባለፉት 9ሺህ ዓመታት የአባቶቻችን ታሪክ ምን እንደነበር እንነግራችኋለን:: ይህም ስለ ተቋሞቻቸው፤ስለ ሕጎቻቸው እንዲሁም ስለድንቅ የሥራ ውጤቶቻቸው ነው::" ባልድዊን እንደጠቀመው፣ሰሎንም ሆነ ፕላቶ ይህን አባባል የማይመስል ነው በማለት አላቃለሉትም:: ምክንያቱም ግሪካውያን ራሳቸው የእነርሱ የዘር ምንጭ እነማን እንደነበሩ ለመናገረ ባለመቻላቸው ነበር:: ሄለናዊ ብለው በሚጠሩት ምድራቸው፤ከእነርሱ በፊት ስለነበሩት ፈላስፎያኖች እንኳ የሚያውቁት በጣም ጥቂት ነበር:: ባልድዊን እንደሚለው፣ግብጻውያን፤ሜኒስ ከመንገሡ በፊት ስለነበረው ቅድመ ታሪካቸው ዘግበው ለማቆየታቸው ምንም ጥርጥር የለውም:: ሆኖም ግን የአረማውያን ሥነ ጽሑፎችን ማውደም ወይም ማጥፋት በሚል ሰበብ አክራሪዎች በአሌክሳንድሪያ ቤተ መጻሕፍት ላይ ባደረሱት ታላቅ ቃጠሎ የተነሳ በጽሑፍ ተከማችቶ የነበረው ዕውቀት ወድሟል::

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት አንድ ጥያቄ አለ:: ይኸውም ግሪኮች ስለ ቅድመ አያቶቻቸው ማንነት አንዳች ነገር ሳያውቁ እንዴት ስለግሪኮቹ ሄለናዊ አኗኗር ግብጻውያን ለማወቅ ቻሉ? ምክንያቱ ግልጽ ነው:: ግሪክ፣ የተባሉት ሕዝቦች ጥንት በስደት ወደ ሄለናዊ ምድር ገብተው የሠፈሩና ከግብጻውያን ባህል ጋር ተመሳሳይነት ከነበራቸው ከሌላ ዘር ሰዎች ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል::እንደ አንዳንድ ተመራማሪዎች



አባባል፣ የጥፋት ውሃ በኩሽ ዘር ላይ ባለመድረሱ የተነሳ ኢትዮጵያ የነበራትን ስልጣኔ በኋላ ለተነሱት የሰው ዘሮች ለማበርከት ችላ ይሆናል ይላሉ:: የጥፋት ውሃ በመላው ዓለም የታወቀ ቢሆንም፣በአፍሪቃ ግን አይታወቅም ባይ ናቸው:: ስለዚህም፣ኢትዮጵያ ከጥፋት ውሃ ለተረፈው ዓለም ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሯትን ዕውቀትና ሥነ ጥበባት አበርክታ ሊሆን ይችላል የሚሉ አስተሳሰቦች አሉ:: በግብጽ ምድር የሚታዮት ሥራዎች ሁሉ «ረቱ» በመባል ይጠሩ የነበሩ ሰዎች ሥራዎች አይደሉም በማለት ሬክሉስ ይከራከራል:: ከሕንድ እስከ ኖርዌይ ድረስ የኩሽ ዘር አድርሷል ስለተባለው ተጽዕኖ በያሻር ዘመናት አቆጣጠርም ሆነ በፊንቂያውያን ሃገር የተገኙት መረጃዎች ለመግለጽ በቂ አይደሉም በማለት ይከራከራል::

ስለግብጽ ምድር ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ መለስ ብለን እንመልከት፤ ምድሪቱ ለሁለት የተከፈለች ነች:: የታችኛው ግብጽ የሚባለው የአባይ ወንዝ ወደሜዲተራንያን ባህር ሲቃረብ እስከተፈጠረው ረግራጋማና ደለላማ ባህር ገብ መሬት (ዴልታ) ያለውን ምድር ያጠቃልላል:: የላይኛው ግብጽ የሚባለው ደግሞ ከዴልታው አንስቶ እስከ መጀመሪያው የአባይ ፏፏቴ ድረስ 930 ኪሎ ሜትር ርዝመት የሚደርሰውን ምድር ያካትታል:: የላይኛው ግብጽ በጥንቱ ዘመን ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን የተሞላ ነበር:: እንደ በንሰን አባባል፣በጥንቶቹ ሃውልቶች ላይ ተቀርጸው የተገኙት ምስሎች የሚያሳዩት፣አንገታቸው ያጠረ፣ራስ ሞላላ፣ግምባራቸው ጠባብ፣አፍንጫቸው አጭርና ደፍጣጣ፣

ከናፍራቸው ትልቅና ወፍራም፣አገጫቸው አጠር ያለና ወደ ኋላ የዘመመ ሰዎችን ነው:: የእነዚህ ሕዝብ ገዥዎች ሙሉ በሙሉ ኩሽ ኢትዮጵያውያን ስለመሆናቸው የቀደምት ፈርዖኖቹን ገጽታና የተሳሉባቸውን የሸክላ ሣህኖችንና ጥንታውያን ቅርሶችን መመልከት ይበቃል:: ታላቁ የስፊንክስ ሃውልት፣የአንድ ጥንታዊ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ገጽታን የሚያሳይ ሲሆን፣የዛሬውን ኢትዮጵያዊ መልክና ገጽታ በሃውልቱ ላይ ካለው የኬምፕስ መልክ ጋራ ስናነጻጽር ተመሳሳይነቱ ቁልጭ ብሎ ይታያል:: ይህም ዘመን ያልሻረው የኩሽ ኢትዮጵያዊን ዘር የሚወክል ማስረጃ ነው::

የታችኛው ግብጽ(ዴልታው ክፍል) በለም አፈር የተሞላ፣እርሻ በብዛት የሚታይበት የቴምር ዛፎች የሚበቅሉበት ሲሆን፣ዝናብና ጤዛ ከዴልታው ይልቅ ወደ ባህሩ ጠረፍ ይበዛል:: በአሌክሳንድሪያ ከተማ ጀንበር ስትጠልቅ፤ ከዓየሩ ርጥበት የተነሳ በውጭ የተሰጡ ልብሶች ዝናብ እንዳረሰረሰው ረጥበው ይገኛሉ:: ዝናብ ብርቅ ስለሆነ፣ በዝናብ ጊዜ ሕዝቡ በየጎዳናው ወጥቶ ሲደሰት ይታያል:: ከፀደይ ወራት አጋማሽ በኋላ ግን በዚህ ክልል ከተሰነጣጠቀ መሬትና እንደ ግራጫ ከመሰለ ምድር በስተቀር ሌላ ነገር አይታይም:: በመጸው ወራት፣ውሃው የደፈረሰ ቀይማ መልክ ሲኖረው የቴምር ዛፍ ማደጊያ ወቅት ነው:: በክረምት ደግሞ መላው የታችኛው ግብጽ በቆንጆ ልምላሜ ተውባ የምትታይበት ወቅት ነው:: የላይኛው ግብጽ በተራሮች መካከል የሚገኝ ጠባብና ለም ሸለቆ የሚታይበት ምድር ሲሆን፣ከታችኛው ግብጽ ጋር ሲነጻጸር ደረቃማ የዓየር ንብረት ያለውና ለጤናም ተስማሚ የሆነ ክልል ነው::



ለማዩ በብርሃን ፀዳል የተሞላና ሙቀቱ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ይህን ሙቀት መቋቋም ለሚችል የሰው ዘር ስፍራው እንደ መልካም የመኖሪያ ስፈራ የሚቆጠር ነው የሚሉ አሉ:: ዝናብ በዚህ አካባቢ የተለመደ ስላልሆነ የእርሻ ሥራዎች በመስኖ አማካኝነት የሚካሄዱ ናቸው፤ በክልሉ ትልቁ ትኩረት ውሃን እንዴት ከወንዝ መሳብ ወይም መጥለፍ ይቻላል የሚለው ጉዳይ ነው:: በሁለቱ አካባቢዎች ከሚታየው የዓየር ንብረት ልዩነት የተነሳ በሕዝቦቹ መካከል የአካልና የቆዳ ቀለማት ልዩነቶች እስከመከሰት ደረጃ አድርሷል:: በታችኛው ግብጽ የነዋሪዎቹ ቆዳ ነሐሳማ ሲሆን፣በላይኛው ግብጽ ደግሞ ጥቁር የቆዳ ቀለም መለያ ሆኗል::

በባሕርይ ረገድ ግብጻውያን በአጠቃላይ ደስተኞ፣እንግዳ ተቀባዮችና ግልጾች ናቸው:: ይህ ደግሞ እውነተኛው የአፍሪቃዊ መገለጫ ነው:: አረባዊ ፈላሂን ግን ጭምት፣ ባለው ተደሳችና እሺ ብሎ የሚኖር ነው:: አምሮ (Amrou) እንደተናገረው፣ ለራሱ ሳይሆን ለሌላው በማገልገል የኖረ ነው:: ፈላሂው ለግብጽ ያለው ፍቅር ጥልቅና ሁለንተናዊ በመሆኑ ከግብጽ ቢነጠል ፈጽሞ እንደሚሞት የሚያምን ነው:: ከማመጽ ይልቅ መሞትን የሚመርጥ፣የቤተሰብ ገቢውን በጌጣ ጌጥ ላይ የሚያውል፤ ሌላ ሃብት የማይፈልግ ዓይነት ሰው ነው:: የተፈጠረው ለሰላም እንጂ ለጦርነት አይደለም ብሎ ያምናል:: ለሃገሩ የአርበኝነት ስሜት ቢኖረውም የተዋጊነት መንፈስ ግን የቀዘቀዘ ነው:: የጦርነት ነገር ከተነሳ የሚታሰበው የወታደሮች ሰቆቃ በመሆኑ፣የጦርነት ወሬ ከተሰማ

የጎሣዎቹ ግማሹ ሕዝብ ወደ ተራሮች ሸሽቶ ይደበቃል ይኸውም የሚሆነው ወታደር ስመመልመል የወጡት የመንግስት ወኪሎች ወደ ስፍራቸው እስኪመለሱ ድረስ ነው። ከወታደራዊ አገልግሎት ለማምለጥ ራሱን አካለ ጎደሎ እስከማድረግ ይደርስ ስለነበር ይህን የፈላሂውን ፍርሃት በማወቅ የግብጽ ሥነ ጽሑፍ ሰዎች ሳይቀሩ መሳለቂያ ያደርጉት ነበር። ስለዚህም ነበር የጥንታዊቷ ግብጽ ጦር ሠራዊት በኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች በእጅጉ የተሞላና በእነርሱም አመራር ሥር የነበረው። እነዚህ ታሪኮች የሚገልጹልንና እንድንቀበል የሚያስገድዱን እውነታዎች ቢኖሩ፣ "የጥንቱ ዘር" የተባሉት ኩሾች በወታደራዊ ኃይላቸው ዓለምን የመቆጣጠራቸውን ጉዳይ ነው።

ኒብሁር (Niebur) እንደሚለው ስለግብጽ ስናስብ መደነቅ የሌለብን አንድ ጉዳይ በፋርስ፣በግሪክ፣በሮም፣በአረባውያንና በቱርኮች በተለያዩ ጊዜያት ስለመያዟና ስለመገዛቷ ነው። በተለይ ደግሞ በኒለኛው ዘመናት እንደ ጎርፍ ወደግዛቷ ከገባው አረብ የተነሳ የግብጻውያኑ ቁጥር ዛሬ በእጅጉ አሽቆልቁሏል። (Niebur's Travels, Vol. p. 104)

እንደ ሬክለስ (Reclus) አገላለጽ "ረቱ" በመባል የሚታወቁት ሰዎች የመዳቀል ሁኔታ ቢታይባቸውም አሁንም የጥንት ቅድመ አያቶቻቸውን ይመስላሉ። በዛሬይቱ ግብጽ፣ቅብጦች(Copts) ተብለው የሚጠሩትና የፈርዖን ሰዎች በመባል የሚታወቁት በፕቶሎሚ ዘመን በእጅጉ የተዳቀሉበት ወቅት ነበር፤በብዛት ተከማችተው የሚገኙት በላይኛው ግብጽ ሲሆን፣መላው መንደሮች የእነርሱ ናቸው። በከተማ የሚኖሩት በዕደ ጥበባት ሥራ፣ገንዘብ በማበደርና ተቀጥሮ በመሥራት ያገለግላሉ። እንደሌሎቹ ግብጻውያን ሳይሆን፣ዘግይተው ያገባሉ፤ለቤተሰባዊ ሕይወትና ለልጆቻቸው ይበልጥ ትኩረትን ይሰጣሉ። ለጥንታዊው ሃይሮግሊፊክስ ጽሑፍ ቁልፍ የሆነው የጥንቱ ቅብጦች ቋንቋ ዛሬ በየትም ስፍራ አይነገርም። ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሚነገረው ቋንቋ አረብኛ ሲሆን፣ይህም ግብጽ በቅኝ ገዥዎቹ አረቦች ተገዳ የተቀበለችው መሆኑን ያመለክታል። ቅብጦች አሁንም ቢሆን የቁም ጽሑፍ የሚጽፉ ሰዎች አሏቸው። በጥንት ዘመን የነበረ የውል ስምምነቶችን ያዘሉ መረጃዎች በእጃቸው ይገኛሉ።ቅብጦች አሁን በሃገሪቱ ውስጥ በዝቅተኛ የመንግሥት ሥራ መደብ የሚሠሩ፣ጮክ ብለው በመናገር የሚታወቁ፣የቆዳ ቀለማቸው ከአረቦቹ ይልቅ ጠቆር ያለ፣ፀጉራቸው ዳበር ያለና ዞማ የሆነ፣አፍንጫቸው አጭር፣ ከናፍራቸው ሠፊ የሆነ ሕዝቦች ናቸው። ከፈርዖን የዘር ግንድ በቀጥታ የሚዛመዱና ከግብጽ ሕዝብ አንድ ስድስተኛውን የሚወክሉ ናቸው።እንደ ሬክለስ አባባል፣የዛሬዎቹ ቅብጦች ለጥንታውያኑ ለዓላውያን ገዥዎቻቸው ያላቸው ስሜት አናሳ ነው። (Africa, Vol. I, Reclus)

ሥልጣኔና ባህል ከግብጽ በስተደቡብ ትገኝ ከነበረችው የሜሮይ ከተማ እንደተሰራጨ የሚያሳምኑ መረጃዎች መኖራቸውን የዘመናችን የጥናትና ምርምር ሰዎች ለመቀበል ተገድደዋል። ግብጽ በመጀመሪያ በብዙ ንጉሦች ተከፋፍላ ትገዛ የነበረች ምድር ነበረች፤ገዥዎቿ በየጊዜው

ጦርነት ሲገጥሙ ኖረዋል። ሆኖም ግን፤ነገሥታቱ የአባይን ወንዝ ተቆጣጥሮ በሥራ ላይ ለማዋል ከገጠማቸው ችግር የተነሳ በ3895 ዓመት ቅ.ል.ክ በንጉሥ ሜነስ ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት ስር በመዋሃድና መዲናቸውን በሜምፊስ ከተማ በማድረግ ሥርወ መንግሥቱ ለአንድ ሺህ ዓመታት እንዲቀጥል መሰረት ጥለዋል። ይህ ጥንታዊው ንጉሣዊ መንግሥት የፒራሚድ ገንቢዎቹ ዘመን በመባል ይታወቃል።

ሳይስ(Sayce) ባገኘው መረጃ መሠረት ከ6ኛው ሥርወ መንግሥት በፊትና ከዚያ በኋላ የታዩት የራስ ቅሎች የተለያዩ ናቸው። ይህም የሚያመላክተው ወደ በስተኋላ ከሌሎች የሰው ዘር ጋር በመደባለቃቸው የተነሳ ስለተፈጠረ የለውጥ ሂደት ነው። በርግጥም፣በዚያን ዘመን ምንም ተጨማሪ የስልጣኔ ዕድገት ያለመመዝገቡ ሃውልቶቹ በራሳቸው ምስክር ናቸው። በሌላ አንጻር ኢትዮጵያ በቅኝ ገዥነት ግብጽን ከመያዝ ይልቅ ፊቷን ወደ ምዕራብ አውሮፖና ወደእስያ አህጉራት በማዞር ከስፖኝ እስከ ህንድ የተስፋፋችበት ጊዜ ነበር።

ከ2400 እስከ 2000 ዓመት ቅ.ል.ክ በግብጽ የመካከለኛው ዘመን ንጉሣዊ መንግሥት ተብሎ ይታወቃል፤በዚህ ወቅት የቴብስ ከተማ መዲና የሆነችበትና የታወቀችበት፣ውብና ድንቅ ቤተ መቅደሶች የተገነቡበት፣ ሚስጢራዊ ሥርዓቶች ተግባራዊ የሆኑበት፣ አሜን ራዕ ቅዱስ አምላክ በመባል የታወቀበት ዘመን ነበር። የግብጽ ፒራሚዶች በተገነቡበት በ5ኛ ውና በ6ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን አሜን ራዕ በሕይወት እንደነበር ይታመናል፤ሆኖም ግን እስከ 11ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ድረስ



በግብጽ ይታወቁ ከነበሩት አማልክት መካከል አልነበረም። ፈርዖኖች የነበሩት ሁሉ በቀጥታ ከአሜን ራዕ የዘር ግንድ የመጡ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፤ይህ ደግሞ በተራው ዜጋ ሳይቀር ተአማኒነት ነበረው። አሜን ራዕ ማን ነበር? እርሱ ከቀድሞ የኢትዮጵያ አማልክት ውስጥ ዋነኛው ሲሆን፤የካም ልጅ የሆነው ኩሽ ሌላው የመጠሪያ ስሙ ነው። የኩሻዊ ዘር አባት ነው። እርሱ ከግብጽ አማልክት መካከል ጥንታዊም አይደለም። ምክንያቱም በኖህ ዘመን ሌሎች ስለነበሩ። አሜን ራዕ በድል አድራጊነቱ ይታወቃል። በጥንቱ ሥርዓት መሠረት፣በገድሉ የሚታወቅ ሰው ሲሞት እንደቅዱስ ተቆጥሮ ከአማልክት ወገን የመመደብ ባህል ስለነበር፣ምንም እንኳን አሜን ራዕ እስከ 11ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ድረስ በሕይወት ባይዘልቅም እንደ አማልክት ተቆጥሮ ይዘከር ነበር።

አሜን ራዕ ወይም ኩሽ፣ በግብጽ የተቀደሱ ስፍራዎች በመዘከር የዋነኛ ነቱን ስፍራ ስለመቀዳጀቱ ማስረጃዎች አሉ። ዚየስ፣አፖሎና ኦሲሪሲ በአምላክ ደረጃ ቢታዩም ሰዎች መሆናቸው የታወቀ ነበር። ግሪኮች፤ ዚየስ በሚል ስም አሜን ራዕን ከመጥራታቸው ባሻገር ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚጋበዝ አምላክ ብለውታል። በሮማውያን ዘንድ ጁፒተር ተብሉ ተጠርቷል። ዚየስ የኢትዮጵያ ገዥ ከመሆኑ ሌላ ከሕንድ እስከ ኖርዌይ በነበሩ ግዛቶችና ንጉሦች ላይ ንጉሠ ነገሥት ነበር። ሆረስ፣አፖሎ፣በሉስና ናምሩድ የኩሽ ልጆቹ ሲሆኑ፣የኩሽ ቅኝ ግዛቶች በነበሩባቸው ሃገሮች ሁሉ የታወቁና የሚመለኩ ነበሩ። ስለአሜን ራዕ

ክብር በሚደረጉ ማንኛውም የግብፃ ሥነ ሥርዓቶች ወቅት የኔግሮ መልክ ያላቸው አፍሪቃውያን ያገለግሉት እንደነበር በሃውልቶች ላይ ተቀርጸው ያሉት ምስሎችም በግልጽ ያሳያሉ:: አሜን ራዕ ራሱ የጥቁር ዘር ሲሆን፣ስለግብጽ የአምልኮ ሥርዓት በተጻፈው የኋለኞቹ ምዕራፎቹ ውስጥ ስሙ በጉንት ኔግሮዎች ቋንቋ ተጠቅሶ ይገኛል::



# ምዕራፍ ስድስት
## ግብጽና ወርቃማው ዘመን

የግብጽን ታላቅነት የሚያቃልሉ የሉም ባይባልም ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ነው:: በአውሮፖ የነበሩ ነገዶች ከእንስሳ ባልተናነሰ የአኗኗር ዘይቤ ለመኖራችውና ለስልጣኔም ባይተዋር እንደነበሩ ማስረጃዎች አሉ:: በዚህ ምክንያት አውሮፖውያን በጽሑፍ ዘግበው ያቆዩልን ምንም ታሪክ የለም፣ስለሆነም አውሮፖውያን ስልጣኔን ሳያውቁ ግብጽ ኃያልና የሠለጠነች ታላቅ ሃገር ነበረች:: የግሪክ ሰዎች ገና የዋሻ ነዋሪዎች በነበሩበት ዘመን ግብጻውያን የሥነ ጥበብ ሰዎች ነበሩ:: ከዘመናችን የኢንዱስትሪያዊ ሂደት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ሥራ ይሰሩ ነበር:: ዛሬ በተግባር ላይ ያዋልናቸውን የሳይንስ ዕውቀቶችና የምናስተምራቸውን የሞራል መሠረቶች ግብጻውያን በሃውልቶቻቸውና በፓፒሪ ብራናቸው ላይ መዝግበው ያቆዩልን ናቸው:: ስለሆነም ለዛሬው ሰው የአስተሳሰብ አድማስ መሠረት የሆነውን ሁሉ ያገኘነው ከአባይ ወንዝ ዳርቻ እንደሆነ ማመን ይኖርብናል (The Earth and Its Inhabitants, Africa, Vol. I, P.207):: ጥንታውያኑ የግብጽ የኪነት ሥራዎች የሚያስተላልፉት መልዕክት ደግነትንና በቀላሉ መደለል እንደማይገባ ነበር፤ሆኖም ግን ዘመናቱ እየነጎዱ ሲሄዱና ከሌሎች ዘር ጋር መደባለቅ ሲመጣ የቀድሞ ሃይማኖታዊ መሠረታቸውን እስከ መርሳት ብሎም እንስሳትን እስከ ማምለክ ደርሰው ነበር::

ራክሉስ እንደሚገልጸው፣ የዛሬይቱን ግብጽ ያለችበትን ደረጃ ስንመለከት ታላቅ የነበረችበትን የጥንቱን ዘመን እንድናስብ ያደርገናል። የግብጽ አወዳደቅ ፈጣን እየሆነ የመጣው ከራምሴስ ካልዓይ በኋላ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል። ምስራቃውያን ነገሥታት ዜጎቻቸውን በመዳፋቸው ጨብጠው በመግዛት ሲታወቁ፣የግብጽ ፈርዖኖች ደግሞ በአንጻሩ ሕዝባቸውን በሃይማኖታዊ መመሪያዎች በመሸበብ እንደገዙት መረጃዎች ይጠቁማሉ። እንዲያም ሆኖ መብታቸውና ንብረታቸው በሕግ የተጠበቀ ነበር። ዛሬ ተወዳዳሪ ስሌላቸው የጥበብ ሥራዎች ባለቤት እንደነበሩ ከታሪክ ማህደራት ቢታወቅም፣አንዳንዶቹ ዛሬ ጨርሰው ጠፍተዋል። ለምሳሌ ግብጻውያን፣አስከሬንን እንደ ሕይወታዊ ሰው ጠብቆ የማቆየትን ጥበብ ተክነው ነበር። ሳይስ እንደሚለው በጊዛ ስፍራ የፈርዖን ካፍ ሬ ሃውልትን ለሚጎበኝ ሰው የድንጋይ ሃውልት መሆኑን እስከመጠራጠር ይደርሳል። ድንቅ ሥራ ነው። ሃውልቱ፣ዳዮራይት ተብሎ ከሚጠራ በጣም ጠንካራ አለት ተቀርጾ የተሠራ ሲሆን፣ባለንበት በአሁኑ ዘመን ስንኳ ይህንን አለት ለመጥረብ የሚያስችሉ መሣሪያዎች አልተሠሩም ማለት ይቻላል።

ዶነሊ(Donnelly) እንዳረጋገጠው፣የሥልጣኔ ጮራ በየተራ ከግብጽ ወደ ከለዳውያን ከዚያም ወደ ሕንድ ብሎም ወደ ግሪክ በመጨረሻም ወደ ሮም መፈንጠቁን ብንረዳም እነዚህ ሕዝቦች ሥልጣኔውን ከመቀበል በሻገር ከግብጾቹ ባገኙት ላይ አዲስ ነገር አልጨመሩም። ባለፉት ሦስትና አራት መቶ ዓመታት እነዚህን የጥበብ ሥራዎች ምንም ቁሣዊ ለውጥ



ሳያደርጉባቸው ቆይተዋል። የነበረውን ተቀብሎ ከማስተላለፍ በስተቀር አንዳችም ያሻሻሉት ነገር አልነበረም። በርግጥ፣በግብጻውያን ዘንድ ያልታወቀ በኮሎምበስ ዘመን የታየው አዲስ ነገር የሕትመት ጥበብ ብቻ ነበር። ፈርዖን ሜነስ ከመንገሱ በፊት ይህ የጥንት የኩሽ ዘር የሕንጻ ጠበብቶችን፣ቀራጺያንን፣ሰዓሊያንን፣የሥነ መለኮት ሰዎችን፣የሙዚቃ ተወዛዋዦችን በውስጡ ያካተተ ነበር። በተለይ የህክምናን ጥበብ በማጥናት በህክምና ዕውቀት ረገድ መጻሕፍትን በመጻፍ የሕይወት ዘመኑን ያሳለፈ እንደ ንጉሡ ሜነስ ልጅ ማን አለ? በዚህ ረገድ ለ6 ሺህ ዓመታት ያክል የሰው ዘር ከግብጽ ከተገኘው ጥበብ በስተቀር ብዙም ርምጃ አልተራመደም ማለት ይቻላል።

ጥንታዊዋ ግብጽ ሃይማኖቷ በሚስጢር የተሸፈነ ነበረ ሆኖም ታመልክ የነበረው አንድ አምላክን ብቻ ነበር። በኋለኞቹ ዘመናት በሃውልቶቿ ላይ የተገኙት ማስረጃዎች የሚገልጹት ግን በግብጽ ብዙ አማልክት ይመለኩ እንደነበር ነው። እንደ ደ ሩዥ አስተሳሰብ(De Rouge) ይህ የአማልክት አምልኮት የተመሠረተው በአንድ አምላክ አምልኮት ላይ ሲሆን፣ኘታ ከግብጻውያን አማልክት ዋናውና እንደ አምላክ የሚቆጠር የእውነት ጌታ፣የሰማይ ገዥ፣የምድርና የሰማይ ንጉሥ ተብሎ ይጠራ ነበር። ከእርሱ ቀጥሎ የፀሐይ ንጉሥ ተብሎ የሚጠራው ራዕ መጣ። የእርሱ አምልኮት ሁሉን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ከኦሲረስ ይለያል። በቅኝ ግዛትነት ግብጽን ከእኛ የወሰደው ኦሲረስ ነው በማለት ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ይናገራሉ። በግብጻውያን ትረካ እጅግ ከፍተኛውን ስፍራ ይዞ የሚገኘው

በኦሲሪስና(Osiris) በኢሲስ(Isis) ላይ የተመሰረተው ሲሆን፣የአምልኮት ስፍራቸው በላይኛው አባይ በፊሌ(Philae) እና በአቢዶስ(Abydos) ከተሞች ነበር:: ተመራማሪው ፔትሪ በዚህ ስፍራ ስለ ጥንቱ የሰው ዘር ቅርሶችን አግኝቷል:: እንዲሁም በአቢዶስ ከተማ የኦሲሪስ መካነ መቃብር ተገኝቷል:: በዚያን ዘመን በቂ ሀብትና ክብር የነበረው ግብጻዊ ሁሉ በዚህ የመቃብር ስፍራ መቀበርን ይመኝ እንደነበር የሚጠቅሱ ጽሑፎች አሉ:: ሆረስ(Horus)፤የኦሲሪስና የኢሲስ ልጅ ሲሆን፣እናቱ ኢሲስ ከቀንድ የተሠራና የሩብ ጨረቃ ምስል ያለበትን ቆብ በራሷ ላይ በማድረግ ትታወቃለች፤ጥቁሯ የሶአዳን አምላክ በመባልም ትጠራ ነበር:: ቶት(Thot)፣የኦሲሪስ ወንድም ሲሆን፣አስማተኛው ካህን፣ዋናው የጨረቃ አምላክ፣የዕውቀትና የማስተዋል ጥበብ ሰጭ፣የጽሕፈት ጥበብ አምላክ ተደርጎ ይከበር ነበር:: የመመለኪያውም ስፍራ በሶአዳን ነበር::

በክብር አነስተኞቹ አማልክት ከእርሱ በኋላ የመጡት ናቸው:: አማልክቱ ይታወቁባቸው የነበሩበት የእንስሳት ምልክቶች የነበሯቸው ሲሆን፣ለምሳሌ የኦሲሪስ አርማ ኮርማ በሬ ነበር:: ቀደምት ግብጻውያን በእንስሳት አምልኮት አይታወቁም:: ወደኋላ የመጣው ትውልድ ደግሞ በንጉሦቻቸው አርማ ሆነው በሚታወቁት እንስሳት ላይ የሚደረግን ማናቸውንም መተላለፍ እንደ ታላቅ ስድብና ርኩሰት ይቆጥሩት ነበር:: ምክንያቱ እንስሳዎቹ የአማልክቱ መለያ በመሆናቸው የተነሳ እንደ ክቡር ፍጥረት ያዩአቸው ስለነበር ነው:: በእነዚህ እንስሳት ላይ ጉዳት በሚያደርስ በማንኛውም ሰው ላይ ሕዝቡ እስከሞት የሚደርስ ቅጣት ይፈጽሙበት ነበር::



እነዚሁ ክቡር እንስሳት በላያቸው ላይ በጉልህ በሚታይ መለያ ይታወቃሉ፣ምርጥ ምግብም ይመገባሉ፣ውድ ልብስ ይለብሳሉ፣ በሚሞቱበትም ጊዜ ለቀብራቸው ሥነ ሥርዓት የንጉሦቹና የመኳንንቶቹ ሃብት ይውል ነበር::

በግብጻውያን አፈታሪክ ውስጥ ኦሲሪስ፣የሞተን ሰው ነፍስ የመመለስ ችሎታ ነበረው ተብሎ ይነገራል:: ኦሲሪስ፤ ነፍስ ስላደረገችው በደል በመመርመር ፍርድ ሰጪ ሲሆን፣ቶት ደግሞ በነፍስ ላይ የሚፈረደውን ዘላለማዊ ቅጣት መዝጋቢ ነበር ይባላል:: ስለዚህም የእያንዳንዱ ሰው ነፍስ በኦሲሪስ የፍርድ ወንበር ፊት ማለፏ የግድ ነበር ይባላል:: የግብጽን ሥነ ጽሑፍና ሥነ ጥበብ ለመረመረ ሰው ነገሯ ሁሉ ከሃይማኖት ጋር በእጅጉ እንደ ድርና ማግ የተሳሰረ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል:: በ3500 ዓመት ቅ.ል.ክ ፈጣሪ አምላክ በሰው አምሳል ተገልጦ በምድር ላይ ነበር ብለው ግብጻውያን ያምኑ እንደነበር ከመረጃዎቹ ለማወቅ ይቻላል::

በጥንታዊቷ ግብጽ ግርዛት እንደ ሃይማኖታዊ ግዴታ የሚፈጸምና በመላው ሕዝብ ተግባራዊ ይደረግ የነበረ ሥርዓት ስለመሆኑና ምንጩም ከኢትዮጵያ የገኘ መደብ የተገኘ እንደነበር ይነገራል:: ይህ ሥርዓት በግሪኮችና በሮማውያኖች አገዛዝ ዘመን ተግባራዊነቱ የቀረ ቢሆንም፣ የጥንቱን ሥርዓት ለመከተል በወሰኑ ካህናት ዘንድ ግን ተጠብቆ ቆይቷል:: ሄሮደተስ እንደተናገረው፣ ኢትዮጵያውያን ይገረዙ ነበር:: እንደ ሊኖርማንት(Lenormant) አባባል፣ግርዛት ከኢትዮጵያውያን የተገኘ ነው:: ግርዛትን ዛሬ ተግባራዊ እያደረጉ ያሉት የኮፕቲክ አብያተ ክርስቲያናትና

አቢሲኒያውያን ናቸው። ዕብራውያን ግርዛትን ከመቀበላቸው በፊት የሚታወቅ ነበር።

ይኸው የግርዛት ሥርዓት በምዕራብ አፍሪቃ ተግባራዊ እንደሆነ አልደንድሮፐ(Oldendrope) ጽፏል። ይህ የሚያመለክተው ግርዛት በጥንታዊቱ አፍሪቃ የቆየ ሥርዓት መሆኑን ሲሆን፣ በመሐመድ በተመሰረተው የእስልምና ሃይማኖት ዘንድ እንደ ሃይማኖታዊ ግዴታ የማይታይ ነው። በደቡብ አረቢያ የነበሩ ኩሻዊ አረቦች ግን ይህንን ሥርዓት ከኢትዮጵያ ተቀብለው ግርዛትን ይፈጽሙ ነበር። ፖኮክ በጥናቱ እንዳገኘው ኩሻዊ የሆኑት ሂምራውያን አረቦች በተወለዱ በ8ኛው ቀን ልጆቻቸውን ሲገርዙ ሌሎች ሴማውያን አረቦች ደግሞ ልጆቻቸውን በወለዱ ከ10ኛው እስከ 15ኛው ዓመት መካከል ባለው ጊዜ ይገርዙ ነበር።

ኦሲሪስና የግብጻውያን ትንሣኤ(Osiris and the Egyptian Resurrection) በተባለው መጽሐፉ መግቢያ ላይ በጅ(Budge) እንደሚነግረን፣ከ1200 ዓመት ቅ.ል.ክ ጀምሮ ግብጻውያን ካህናት ስለሃይማኖታቸውና ስለ እምነታቸው መሠረት ምንነትና ትርጉም ለመረዳት እየተሳናቸው ቢመጣም፣ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውን ሥርዓት ላለመተው ሞክረዋል። ሆኖም ግን፣ቀስ በቀስ ወደ አስማተኛነትና የጥንቆላ ሥራ ተሸጋግረዋል፤ እጅግ ጥቂቶች ግን የጥንቱን እምነትና ሥርዓት ጠብቀው ቆይተዋል። ግብጽ፣በ3400 ዓመት ቅ.ል.ክ የእውነትን፣የፍትሕን፣የጽድቅን መንገድ ትከተል እንደነበረች ይነገራል። በጅ፣በገጽ 15 ላይ እንዳሰፈረው፣የግብጽ



ሃይማኖት ሁሉም ባህርያት የአፍሪቃዊነትን እንጂ የእስያዊነት ባህርያትን አያመለክቱም። እውነተኛው የግብጽ ሃይማኖት ያበቃው በ3 ሺህ ዓመት ቅ.ል.ክ ሲሆን፣ ለዚህ ምክንያቱ በግብጽ የሃይማኖት መሪዎች የነበሩት ኢትዮጵያውያን የአሜን ካህናት በትረ መንግሥታችውን ከግብጽ ተነጥቀው ወደ ናፓታ ከተመለሱ በኋላ ነበር። በዚህም የተነሳ፣ግብጽ የሃይማኖቷን ጥልቅ ሚስጢርና አብሯት የነበረውን የአምልኮት ሥርዓት አጥታለች።

በንግዱ ዘርፍ፣ግብጻውያን በሐቀኝነትና በማስተዋል ይሠሩ ነበር፤ ከተሞቻቸው ሥርዓት የሰፈነበት፣ጠብና ግርግር የማይታይበት ብሎም ፍትሕ ያለአድልዎና ያለመዘግየት የሚፈጸምበት ምድር ነበረች። በዕደ ጥበብ ረገድ የብረት የወርቅና የመዳብ ሥራዎች የሚሰራባት፣የሽመና የእንጨት፣የቆዳ፣ የሸክላ፣የመስታወት፣የጫማና የብራና ሥራ እንዲሁም የጦር መሣሪያዎች የሚፈበረክባት ምድር ነበረች።

እንደዌስት አባባል የእጅ ሙያ ችሎታቸው፣ ክህሎታቸውና የምርት ሂደቶቻቸው አሁንም እንኳን ቢሆን የማይታወቁ ናቸው። በተለይ ሽማኔዎቻቸው ያመርቷቸው የነበሩት ለስላሳና ልዩ የሆኑ የሳይነን ጨርቆች ከሐር አይተናነሱም ነበር። የወርቅና የመስታወት ሥራ ውጤቶቻቸው በዚህ ሙያ መስክ የነበራቸውን ጥበብና ክህሎት ይገልጻል። ከመስታወት ንጥረ ነገር የሚሠሯቸው ጌጣ ጌጦች፣ ከከበሩ ማዕድናት እንደተሠሩ አድርገው የማቅረብ ችሎታቸው ከፍተኛ ከመሆኑ

የተነሳ፣የትኞቹ እውነተኞች የትኞቹ ተመሳስለው የተሰሩ መሆናቸውን ለመለየትና ለማወቅ ያዳግት ነበር:: በዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱስ አስርቱ ትዕዛዛት ከመጻፋቸው አስቀድሞ መልካም ሥራ ከሞት በኋላ ሽልማትን፣ክፉ ሥራ ደግሞ ቅጣትን እንደሚያስጥ በግብጻውያን ሃውልቶች ላይ ተጽፎ ነበር:: ስለመድኃኒቶችና ጥቅማቸው የሚገልጹ መጽሐፍት ነበሩአቸው:: ስለመድኃኒት ምርምር በማድረግ ታዋቂ የነበረው ኦሲሪስ አባቱን ከራስ ምታት ህመሙ በምን መድኃኒት እንዳዳነው ተገልጾ ይገኛል:: (World Progress-West):: አባቱ የፀሐይ አምላክ ከተባለ፣ልጁ ይህንን ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አይታይም::

በሥነ ፊደል እድገት አኳያ፣እንደ ክሬቶቹና እንደ ኢትዮጵያውያን፣ ግብጾች ፊደላቶቻቸውን ወደ ተሟላ ደረጃ አላሳደጉትም:: "ጽሑፎቻቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ የምልክቶች ስብስብ ከመሆን ባሻገር አላለፉም::" እንደሳይስ አባባል፣በግብጻውያን ጽሑፎች ውስጥ ከአረቢያው ምሽት ትረካዎች ጋር የሚመሳሰሉ ጥቅሶችን እናያለን፤ለምሣሌ የሲንደሬላ፣የአርባዎቹ ሌቦችና ሲናባድ መርከበኛውን የመሳሰሉ ትረካዎች:: አፍሪቃውያኑ ደግሞ ስለኤዞፕ ብዙ ትረካዎች አሏቸው:: ኤዞፕን እንደራሳቸው ሰው አድርገው ይመለከቱታል፤ምክንያቱም ኩሻዊ ስለሆነና እነርሱም ራሳቸውን ከኩሽ ነገድ እንደሆኑ በመቁጠራቸው ነው:: በአፈ-ታሪኩ መሠረት ኤዞፕ ሰውነቱ ጎባጣ የሆነ ጥቁር ሰው ሲሆን፣በጥንቱ ዘመን በእስክንድርያና በታናሽቱ እስያ ከተሞች የታወቀና የተከበረ ሰው ነበር:: የግብጻውያኑንና የአረቢያን ምሽቶች ትረካ



ተመሳሳይነት ስንመለከት ከኩሽ ኢትዮጵያውያን የተቀዳ መሆኑን እንረዳለን:: ግብጽ በጥንቱ ዘመን በኢትዮጵያ ገዥነት ሥር ትተዳደር ስለ ነበር በጋራ የወረሰችው የባህል ውጤት ነበር ለማለት ይቻላል::

የቤቶችን አሠራር በተመለከተ፣የተራ ዜጋው ቤት ሳይቀር በጡብ ሸክላዎች የተገነቡ፣በአብዛኛው ባለአራት ማዕዘንማና ባለ አንድ ፎቅ የሆኑ፣የቤቶቹ ጣሪያ ጥላ ተደርጎባቸው እንደመዝናኛም ስፍራ ያገለግሉ የነበረ፣ግቢዎች በአትክልትና በአባባ ያሸበረቁ፣የውሃ ሻሻቱም የነበራቸው፤የመንግሥት ሕንጻዎች ከጥርብ አለት የተሠሩና ከሌላው የተለዩ ነበሩ:: ግብጻውያን ወንዶች ሽመና ሲሰሩና ንግድን ሲያካሂዱ፣ ሴቶቹ ደግሞ ግብይይቶችንና የድለላ ሥራን በማከናወን ይሰማሩ ነበር:: ተዋጊ የሆነው ክፍል ከሁሉም በላይ የሆነ ጥቅማ ጥቅሞች ይሰጠው ነበር:: ከታክስ ነፃ የሆነና ከግዛቲቱ የአንድ ሦስተኛ መሬት ባለቤት ነበር:: በእርሻ የሚተዳደረው አባወራ ለመሬቱ ግብር ከፋይ ሲሆን፣ ፈላሂኑ ግን መሬት አልባ ነበር:: ቀብርን በተመለከተ እንደኩሽ ሕንጾች የቀብር ሥርዓት ማለትም ባል ሲሞት ሚስትን ከባሏ ጋር የመቅበር ባህል በግብጽ ውስጥ ይደረግ እንደነበር የታወቀው በቴብስ ከተማ በፈርዖን አሜን ሆቴፕ ካልዓይ መካነ መቃብር ውስጥ ከሚወዳቸው ሚስቶቹ ጋር ተቀብሮ በመገኘቱ ነበር::

የግብጽን የቤተሰባዊ አኗኗር በተመለከተ፣ዳንከር(Duncker-History of Antiquity) በተባለው መጽሐፉ በቅጽ 1 ገጽ 118 ላይ እንደገለጸው፣

በመቃብሮቹ ውስጥ 4ሺህ ዓመታትን ያስቆጠሩ ልዩ ልዩ ስዕላት ይታያሉ።ማረሻዎች፣ኮርማዎች፣ጥጃዎች፣አህዮች፣በጎች፣ፍየሎች፣ላሞች ደሮዎች፣የቅቤና የዓይብ ምግቦች ናቸው። ሌሎች የቅርጻ ቅርጽ ምስሎች፣የሽመና፣የሸክላ፣የብረት፣የግንብ፣የጫማ፣የጠርሙስና፣የመስታወት ሠራተኞችንና ሰዓሊዎችን ያካተተ ምስል ያሳያሉ። ስዕላቱ የሚገልጹት በዘመኑ የነበረውን የማህበረሰብ ክፍል ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣ኢኮኖማዊና ሃይማኖታዊ አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ሲሆን፣ስለገጠሩ ሕይወት ተስለው የተገኙት መረጃዎች ሠልጥነናል ብለን የምንኩራራውን እኛን እንኳን መለስ ብለን ራሳችንን እንድንመረምር ያደርገናል። በጥንቱ ግብጻዊ ቪላ ቤት የነበሩትን ቁሳቁሶች ስናይ ዛሬ እኛ በአውሮፖ አለን ከምንለው ጋር የተመሳሰሉ ናቸው። በዘመናቸው ስለነበሯቸው የናይለን ልብሶቻቸው፣ስለቤት ቁሳቁሶቻቸው፣ስለሙዚቃና፣ስለጦር መሣሪያዎቻቸው ጥራትና ድንቅነት ብዙ ማለት ይቻላል።

በተቃራኒው ሴማውያን በተባሉት ነገዶች ዘንድ የተከበረ ሥራ የተባለው የከብት ርባታ ሥራ ነበር። በግብጽ ሕብረተሰብ ዘንድ በበግና በአሣማ(እሪያ) ርባታ የተሰማራ ሰው ሁሉ በዝቅተኛ ደረጃ መታየቱ የሚያመለክተው ግብጻውያን ከሴማውያን ዘር ያለመሆናቸውን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፀአት ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 ላይ "ሙሴም ለእግዚአብሔር ለአምላካችን የግብጻውያንን ርኩሰት እንሰዋለንና እንዲህ ይደረግ ዘንድ አይገባም፣እነሆ እኛ የግብጻውያንን ርኩሰት በፊታቸው



ብንሰዋ አይወግሩንምን?" ብሎ የተናገረበት ዋና ምክንያት በግብጽ ምድር የፈርዖን መለያ የበግ ምልክት ስለነበር ዕብራውያን ደግሞ በግ አርቢዎች ስለነበሩ ግብጻውያን ያከበሩትን በግ ለመስዋዕትነት ቢያቀርቡ በግብጻውያን ዘንድ እንደ ታላቅ ርኩሰት ተደርጎ ስለሚቆጥር ነበር። በዚህም የተነሣ ዕብራውያን በግብጽ ምድር በነበሩበት ዘመን ሁሉ ግብጻውያን አብረዋቸው አይመገቡም ነበር።

በአባይ አካባቢ ይኖር የነበሩት ሕዝቦች ዋነኛ መሠረታቸው እርሻ ሲሆን፣ ይኸም የካም ዘር መለያ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በሥነ ጥበብና በኢንዱስትሪ ሥራዎች በሚገባ የተካኑ ነበሩ። ተቀርጾ በተገኘ በአንድ ጽሑፍ ላይ እንደታየው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የነበረ የሕንጻ ንድፍ ሙያ ለቀጣይ ሃያ ሦስት ትውልዶች ሲተላለፍ መቆየቱን እንዲሁም ጋብቻ በተለያዩ የሙያ ዘርፍ ባላቸው ሰዎች ዘንድ የተከለከለ እንዳልነበረ የሚገልጽ ነበር።

ግብጻውያን የመዝናኛ ስፍራዎችን ማዘውተር የሚወድዱ፣ በአትሌቲክስ ስፖርቶች በእጅጉ የሚደሰቱ፣የቤት ውስጥ ውድድሮችን የሚከታተሉ፣የሰርከስ ጥበቦችን የሚያደንቁ፣ሕፃናት ልጆቻቸው የሚጫወቱባቸው በርካታ የጫወታ ዓይነቶችና አሻንጉሊቶች የነበሯቸው ሲሆን፣የግብጽ ከፍተኛው መደብ ግን እንደሙዚቃ የሚያስደስተው ነገር አልነበረም።በገና፣ጊታር፣ዋሽንት፣ጡሩምባ፣እምቢልታ፣መለከት፣ትርያንግል፣ከበሮ፣ማሲንቆን የመሳሰሉትን የሙዚቃ መሣሪያዎች ነበሯቸው።

በዘፈን ወቅት የአካል ውዝዋዜአቸው ደግሞ ሞገስን የተሞላና ደስ የሚያሰኝ ነበር::

ከግብጽ ሌላው አስደናቂ ነገር ከ5 ሺህ ዓመታት በፊት የሞቱ ሰዎችን አስከሬን እስከዛሬ ድረስ ያለምንም መበላሸት የማቆየታቸው ሚስጢር ነው:: አሁንም ጥበቡ አይታወቅም:: በአሁኑ ዘመን አስከሬንን ጠብቀን ማቆየት የምንችለው ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ሲሆን፣በዓለም ሙዚየሞች ውስጥ የምናያቸው የፈርዖኖች የፊት ገጽታ ከዛሬ 4ሺህ ዓመታት በፊት በነበሩበት ሁኔታ ላይ ናቸው:: በዘመናችን የፋይናንስ ስሌት አስከሬንን ለብዙ ሺህ አመታት እንደተጠበቀ አድርጎ ለማቆየት በድሮይቱ ግብጽ እስከ 1200 የአሜሪካን ዶላር የሚጠይቅ ሲሆን፣ ከዚህም ባነሰ ወጪ እስከ ተወሰነ ዘመናት ለማቆየት የሚያስችል ጥበብ በተራው ግብጻዊ ቤት ይደረግ ነበር::

ኩሻዊ ግብጻውያን የተዋጣላቸው ኢንጂነሮችም ነበሩ::የአባይን ወንዝ አቅጣጫ በማስለወጥ የሜምፊስን ከተማ ለመገንባት ችለዋል:: ሞኢሪስ፣ተብሎ የሚጠራው ሀይቅ የዙሪያው ርዝመት ወደ 720 ኪሎ ሜትር ሲሆን፣የግንቡ ከፍታ ወደ 110 ሜትር ይደርስ ነበር:: የግንባታው ጥበብ እጅግ የተወሳሰበና የተራቀቀ፤ከምድር በታችና ከምድር በላይ የሆኑ እያንዳንዳቸው አንድ ሺህ አምስት መቶ የሚደርሱ የውሃ ማስተላለፊያ ዋሻዎች ነበሯቸው:: ሄሮዶተስ፤ይህንን ድንቅ ሥራ ተመልክቶ ለማመን ተቸግሮ ነበር:: በካርናክ፤የተሠራው ቤተ መቅደስ አምስት መቶ ሜትር ርዝመት በአራቱም አቅጣጫ ያለው ሲሆን፣ያንን



ስፍራ የጎበኙ ሁሉ ያዩትን ለመግለጽ ቃል አልባ ይሆናሉ ምክንያቱም ለአእምሮ መረዳት የሚያዳግቱ የግንባታ ጥበብ ኩሻዊ ገንቢዎች እንደተጠቀሙ ይታያልና:: በኋለኞቹ ዘመናት ግሪኮች የተጠቀሙበት የህንፃ ንድፍና የጌጥ ሥራ ሙሉ በሙሉ ከግብጾች የተቀዳ ለመሆኑ አያጠራጥርም:: ዛሬ በግብጽ ቆመው የሚታዩት ግዙፍ ሃውልቶችን በምን መሣሪያ እንደ ተጠረቡ ለመግለጽ አልተቻለም:: የዘመናችን የብረት መሣሪያዎች ግራናይት በተባለው ጠጣር አለት ላይ ፊደላትን ለመቅረጽ ይቸገራሉ::

አሜሊያ ቢ ኤድዋርድስ (Amelia B. Edwards)፤ አንድ ሺ ማይልስ ከአባይ ከመነሻው(A Thousand Miles Up the Nile) በተባለው መጽሐፏ እንደጻፈችው፣የግብጽ የሕንጻ ንድፍ ከሌላው የሚለየው በዓይነቱ ብዛትና ወደር በማይገኝለት ውበቱ ነው:: ወደቤተ መቅደሶቹና ቤተ መንግሥቶቹ የሚወስዱት ውብ ጉዳናዎች በግዙፍ ሐውልቶችና ስፊንክሶች የተሞሉ ሰፋፊ አዳራሾች በፀጥታና በግርማ የተሞሉ ናቸው:: በእነዚህ ሐውልቶች ላይ የምናየው ክህሎትና ችሎታ ከጥንቱ ዘመን የቅርጸ ቅርጽና ግንባታ አንጻር ዛሬ ብዙም እንዳልተራመድን ነው:: በግድግዳዎቹና በጣሪያዎቹ ላይ የተሳሉትን ውብና ድንቅ ስዕላትን እየኮረጅን እንገኛለን:: በካርናክ የሚገኘው ታላቁ አዳራሽ የሰው ልጅ ከሠራቸው ክቡር ሥራዎች ሁሉ የላቀ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: «የምሰሶች አዳራሹ» በሚባለው ሥፍራ የሚታዩት ግዙፍ ምሰሶች የዓለማችን ድንቅ ሥራዎች ናቸው ማለት ብቻ ሳይሆን፣እንዴት ሊቆሙ እንደቻሉ ለመግለጽ ያዳግታል:: በዚያ ሥፍራ ቆም ብለን ቁመታቸውን ከእኛ ቁመት ጋር ብናነጻጽር

እንደኢምንት እንሆናለን:: በዚህም የተነሳ እነዚህን ሕንጻዎች ስለገነቡት ሰዎች ከማሰብና ከመደነቅ በቀር ሌላ የምንለው ነገር የለም:: ገንቢዎቹ ራሳቸውን የአማልክት ልጆችን ነን ብለው ቢጠሩ ምን ያስደንቀናል!

ታላቁ ፒራሚድ የተገነባው በ2.5 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ጥርብ ድንጋይ ሲሆን፤የተቀመጠበት አቅጣጫ በ30ኛው ፓራላል(ትይዩ መስመር) ላይ መሆኑንና የፒራሚዱ መሠረቶች በትክክል ይህንን ጂኦሜትራዊ መስመር የጠበቁ ስለመሆናቸው ተረጋግጧል:: በፒራሚዶቹ ውስጥ የፈርዖኖች አስከሬንና ውድ ቁሳቁሶቻቸው የተቀበሩበት መካነ መቃብራት ተገኝተዋል:: ምንም እንኳን ሕንጻዎቹ በሺህዎች የሚቆጠሩ ዘመናትን ያሳለፉ ቢሆኑም፣አለቶቹ ዛሬም ቢሆን የጥንት ቦታቸውን በግሩም ሁኔታ ጠብቀው ይታያሉ::

እንደ ሳይስ አባባል፣በፈርዖን ክሁፉ ዘመን የተገነቡት እነዚህ ፒራሚዶች ለማመን በሚያዳግት መልክ ጥንት በነበሩበት ሁኔታ በሲሚንቶ ተያይዘው ይገኛሉ:: እንደፔትሪ እምነት፣ግብጻውያኑ ከአልማዝ ጥርስ በተሰሩና የቧንቧ ቅርጽ በነበራቸው የመሰርሰሪያ መሣሪያዎች አለቶቹን እንደሰረሰሯቸው ይታያል ብሏል:: በተጨማሪም፣እነዚህን ግዙፍ አለቶች በቀላሉ ወደፈለጉበት አቅጣጫ ለማንቀሳቀስ ስለመቻላቸው ማስረጃዎች በግልጽ ይጠቁማሉ በማለት ገልጾታል:: ስለእነዚህ የግንባታ መሣሪያዎች ምንነት እስከዛሬ ድረስ ለማወቅ አለመቻሉ አስገራሚ ነው::



ፊደላቶቹን እንዴት እንደቀረጿቸውና እንዳተሟቸው በራሱ አስገራሚ ከመሆኑም በላይ፣ ከ4 ሺህ ዓመታት በፊት የተቀረጹት እነዚህ ጽሑፎች አንዳችም የመበላሸት አዝማሚያ ሳያሳዩ ትላንት እንደተሠሩ ውብ ሥራዎች ሆነው መቆየታቸው ደግሞ ሌላው ድንቅ ነገር ነው:: አንዳንዶቹ እንደሚገምቱት፤ይህንን ሥራ ሊሰሩ የቻሉ ሰዎች ስለ ኤሌክትሪክ ኃይል ዕውቀት የነበራቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ አያጠራጥርም ባይ ናቸው:: “ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም” የሚለው የጠቢቡ ሰለሞን አባባል፤በእርግጥም ትክክል መሆኑን ያሳያል:: ዛሬ የግብጽ ሥነ ጥበባት ተብለው በየሙዚየሙ ውስጥ የሚታዩት ቅርሳ ቅርሶችን ለሚመለከት ሁሉ በ5ኛውና በ6ኛው የግብጽ ሥርወ መንግሥት ዘመን የነበሩት ቀራጺያንና ሰዓሊያን ምን ያህል የተዋጣላቸው ባለሙያዎች እንደነበሩ አመላካች ነው:: የቴባን ሰዓሊያን፤ የቀለማትን ሕብረ ሕግጋት ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ የሠሯቸው ስዕላትን ለተመለከተ ሁሉ በዘመናችንም እንኳ ቢሆን ተወዳዳሪ የሌላቸው እንደሆኑ እንገነዘባለን::

ፒራሚዶቹ የተገነቡት በተቆራረጡና በአራት ማዕዘን መልክ ከተጠረቡ አለቶች ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ጥርብ ድንጋይ ክብደት ከ25 እስከ 150 ኩንታል የሚመዝኑ ነበሩ:: እስከዛሬ ተጠብቀው ያሉትን የእነዚህን ድንቅ ሕንጻዎች አቀማመጥና የውሃ ልክ እንዲሁም የማዕዘናቱን ትክክለኛነት ለተመለከተ የዘመናችንን ግንበኞች አንገት የሚያስደፋ ከመሆናቸውም ባሻገር፣ በብዙ ካሬ ሜትሮች ላይ የተገነቡትን የእነዚህን ሕንጻዎችን የግንባታውን ጥራትና ውበት እንዲሁም አሠራር ትክክለኛነት

ስንመለከት፣በተራቀቁ የእይታ መለኪያ መሣሪያዎች(Optical devices) ዕገዛ መታነጻቸውን ያመለክታል:: በሥነ ጥበብ ረገድ ከኑብያ ግዛት ጀበል ባርከል ተወስደው በብሪቲሽ ሙዚየም የሚገኙት የአናብስት ቅርጻ ቅርጾች በቡኒሐሰን የተቀደሰ ሥፍራ የሚታዩት ድንቅና ውብ ስዕላት፣በተለያዩ መካነ መቃብራት ላይ ተስለው የተገኙትን የስዕል ሥራዎች እንዲያው በአጭሩ ድንቅ ናቸው ብሎ ማለፍ ይሻላል:: የግብጽ በርካታ ሐውልቶች በዓረቦች ተሰባብረውና ወድመው ቀርተዋል ጥቂቶቹ ደግሞ በእንግሊዛውያንና በአሜሪካውያን ጥፋት ደርሶባቸዋል:: ይህ ጥፋት ሰለጠንን በሚሉት ወገኖች በመፈጸሙ እንደአሳፋሪ ነገር እንቆጠረዋለን::



# ምዕራፍ ሰባት

## ግብጽና ኃያላን ፈርኦኖቿ

እንደ ኤም ቻባስ(M. Chabas) አገላለጽ፣ግብጽ በ4ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን የደረሰችበትን የዕድገት ደረጃ ለመግለጽ ቢያንስ የ4 ሺህ ዓመታት የታሪክ ዘመናትን መመርመር የግድ ይላል:: ይኸውም ከመጀመሪያው ሥርወ መንግሥት በፊት ያለውን ማለት ነው:: የዚህ አንደምታ፣ጥንታዊና የሁሉ ቀዳማይ ኤምፓየር የመኖርን ሐቅ የመቀበል ጉዳይ ነው:: ከጥንታዊ መረጃዎች እንደተረጋገጠው፣ ኪነቱና የሥነ ጥበብ ሥራዎቹ፤ሃይማኖቱ፤ሁሉ ነገሩ ኦርጅናሌና ንፁህ እንደነበር የኋላ ኋላ ግን እየተበረዘና እየተከለሰ እንደመጣ ይታያል:: የግብጽ ታሪክ ማህደራት እንደሚሉት ከላይኛው ግብጽ የመጣው ንጉሥ ሜነስ በ3895 ዓመት ቅ.ል.ክ ከመንገሡ በፊት አሥር የቲናይት(Thinite) ነገሥታት ነግሰው ነበር:: የሁሉም ምንጫቸውም ከላይኛው ግብጽ እንደነበር ያመለክታል:: ከእነርሱ በፊት ደግሞ ዘመን የማይቆጠርለት ፈጣሪ አምላክ ሰማይንና ምድርን ብቻውን እንደገዛ ተጽፏል:: ይህ አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር የሚቃረን አይደለም::

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ከጥፋት ውሃ በፊት ከአዳም ጀምሮ አሥር አባቶች ተቆጥረዋል:: የሒንዱ፣የከለዳውያን፣የዓረቦች፣የግሪክና የኬልት ዜና መዋዕላት እነዚህን አሥር የነገድ አባቶች፣የጥንት ንጉሦች ብለዋቸዋል:: ከግብጽ መዛግብት ውስጥ ለመረዳት አስቸጋሪ ሆኖ የተገኘው ከጥፋት ውሃ በፊት ስለ ነበረው የዘመን አከፋፈልና አቆጣጠር ነበር::



ከመጀመሪያው የግብጽ ሥርወ መንግስት ኩሻዊው ጥቁር ንጉሥ( በዝሆን ጥርስ ላይ ተቀርጾ የተገኘ(ከW.M.F.Petrie "" አቢዶስ"" ክፍል 2 የተገኘ ምስል)

ሰር ጂ ጋርድነር ዌልከርሰን፣የጥንት ግብጻውያን ባሕልና ፀባይ(The Manner and Customs of Ancient Egyptians) በሚለው መጽሐፋቸው እንደሚገልጹት ሥልጣኔው ከታችኛው ግብጽ ዜባድ(Thebad) ከተማ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተዛምቷል። በሂሮግሊፊክ ተጽፈው ያሉት ጽሑፎች የሚያረጋግጡት ጥንታዊያኑ ከተሞች የነበሩበት ስፍራ በላይኛው አባይ ስላመሆኑ ነው። የሜምፊስ ከተማ በንጉሥ ሜነስ መቆርቆሩ ቢታወቅም፣ሜነስ ከመነሳቱ በፊት ዚስ(This) የተባለችው ከተማ የንጉሦች መዲና ሆና ስመቆየቷ መረጃዎች አሉ። ይህች ከተማ ለአቢዶስ አጐራባች ነበረች።በዚህ ሥፍራ ነበር የጥንቱን የሰው ዘር በተመለከተ ቅርሶች የተገኙት። ሬናን፤መረጃዎቹን ተመርኩዞ እንዳረጋገጠው፣ ግብጽ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስ ረጅም ዘመናት ያልወሰደባት ዋነኛው ምክንያት አቅኚዎቹ ኩሾች ሥልጣኔን ከኢትዮጵያ ይዘው የመጡ በመሆናቸው ነበር። የሜነስ ወራሽ የነበረው አትሆቲስ(Athotis) ይህን



አስመልክቶ የጻፈው መረጃ አለ። በብሪቲሽ ሙዚየም የሚገኘው ከፓፒረስ የተገኘ የሕክምና ነክ መረጃ ደግሞ ለየት ያለ ነገር እንዳለው ይታያል። በ4ኛው የቲናይት ዘመነ መንግሥት ታላቅ ረሃብ በግብጽ ምድር ተከስቶ እንደነበር ማስረጃዎች አሉ። እንደማንቴኦ (Mantheo) የታሪክ ጽሑፍ መሰረት፣በ7ኛው ንጉሥ ዘመን ብዙ አስደናቂ ነገሮች ታይተዋል፤እንዲሁም ታላቅ ቸነፈር በግብጽ ምድር ተከስቶአል። በ2ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ኦፊስ የተባለ የኮርማ አምልኮት በሜምፊስ ከተማ ሲጀመር፣በቲናይት ነገሥታት በአንደኛው ዘመን ደግሞ የሴቶች ሉዓላዊነት ሕግ ታወጀ ነበር።

በ3ኛው ሥርወ መንግሥት ማለት በሜምፋይት (Memphite) ዘመን ሊቢያኖች በግብጽ አገዛዝ ላይ ያመጹበት ሲሆን፣ ይህ የሚያመላክተው ከአባይ ወንዝ ባሻገር ግብጽ ገዢና የበላይ እንደነበረች መሆኗን ነው። ዶክተር ብሩግሽ(Dr.Brugsch) እንደሚሉት፣በዚህ ዘመን የነበሩት ነገሥታት ራዕ(Ra) የሚለው የክብር ስም ተቀጽላ አልነበራቸውም። ሆኖም ግን ቀጣይ ነገሥታቶች፣ራዕ የሚለውን ተቀጥያ መጠሪያ አስፈላጊነትን ተቀብለው ተጠቅመውበታል። 4ኛው ሥርወ መንግስት፤ሄሮዶተስ፤ ኬኦፕስ ብሎ የጠራው የመጀመሪያ ንጉሥ ፈርዖን ኩህፋን ሲሆን፣የፒራሚድ ግንባታ ሥራ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ብሎም የግብጽ አንጸባራቂ ታሪክ የተጀመረበት ዘመን ነበር። ዘመኑ፤የንጉሦቹ ሥልጣን ፍጹማዊ ተደርጐ ይቆጠር የነበረበት፣ ዘመኑ ... የደረሱበት፣የጥንቱ ገዥዎቹ በተወዳጅነታቸው እስከመመለክ ደረጃ የደረሱበት፣

ኢምፓየር ገና ያልተመሰረተበትና ሰላም የሰፈበት ዘመን ስለነበር፣ ፈርዖን ኩህፉ ታላቁን ፒራሚድና የኢሲስን ቤተ መቅደስ በታላቁ ስፊንክስ አጠገብ ለማስገንባት አስችሎታል፡፡ እንደ ብሪታኒካ አባባል፣በፒራሚዶቹ ግንባታ ወቅት የጠፋው የሰው ሕይወት በተራዘመ የጦርነት ወቅት ከሚሞተው ሰው ያላነሰ ነበር ይላል፡፡

የ4ኛው ሥርወ መንግሥት የተመሰረተው ቅ.ል.ክ በ3700 ዓመት ሲሆን፣ስለዚህ ዘመን አስመልክቶ በቅርብ ዘመናት በቁፋሮ የተገኙት ማስረጃዎች የንጉሥ ኩህፉን የፊት ገጽታ ለማየት አስችሎናል፡፡ ይኸውም ግዙፍ የሆነ የኢትዮጵያዊ የፊት ገጽታ! ፔትሪ፤ስለ ንጉሡ ሲጽፍ፣ "ስለዚህ ሰው ከሁሉ የሚደንቀው ነገር ሕዝብን የማንቀሳቀስ ታላቅ ችሎታውና የገዥነት ባህሪው ሲሆን፣በታሪክ ከተመዘገቡትና በጠንካራ ባህርያቸው የሚጠቀሱትንና የሚታወቁትን እንኳ በተዕጽኖው ሥር ለማድረግ የቻለ መሪ ነበር፡፡"ይለዋል እስከ አሁን ከተገኙትና ከሚታወቁት ከግብጽ፣ ከግሪክና ከሮማውያን ነገሥታት ምስል ስብስብ ውስጥ የፈርዖን ኩህፉን ገጽታ የሚመሳሰል አልተገኘም፡፡ የጥንታውያን ኩሾችን የፊት ቅርጽንና ገጽታን ለሚያጠና ሁሉ ያለ ምንም ጥርጥር የኢትዮጵያዊ የፊት ገጽታ ለመሆኑን የዛሬዎቹን ኢትዮጵያውያን የፊት ቅርጽ አቀማመጥና ገጽታ በመመልከት ተመሳሳይነታቸውን ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡





ኩሻዊው ጥቁር ፈርኦን ኩፉ(Khufu) ታላቁ የፒራሚድ አስገንቢ.
(ከW.M.F.Petrie "" አቢዶስ"" ክፍል 2 የተገኘ ምስል)

በአቢዶስ የቁፋሮ ሥፍራ፤ፔትሪ ያገኘው ከዝሆን ጥርስ የተቀረጸ የመጀመሪያው ሥርወ መንግሥት ንጉሥ የፊት ገጽታ ባለ ደፍጣጣ አፍንጫ፣አገጫማና የራስ ቅሉ ሞላላ ነበረ፡፡ በጊዛ ሙዚየም፣በሼክ ኤል በለድ፣ የፒራሚዱ የበላይ ጠባቂ በነበሩት የሚገበኘው ግን የክልስ መልክ ያለው ነው፡፡ የስፊንክስ ሃውልት፤ሆረስ ተብሎ ለሚታወቅ የጥንት አምላክ አምሳል የተሰራ ነው፡፡ ዶክተር ዱቡዋ እንደሚሉት፣ይህ ታላቅ ስፊንክስና ሌሎችም በታኒስ የሚገኙት ስፊንክሶች፤በቡባስቲስ ሥፍራ ግዙፍ ምሰሶዎች ላይ ተቀርጸው ያሉት ምስሎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ የጥቁር አፍሪካውያን ጥንት ነገሥታትን ገጽታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በ5ኛ ውና በ6ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመናት የታነጹት ሕንጻዎችና የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎች እንደቀድሞው የተዋጣላቸው አልነበሩም፡፡ በ5ኛው ሥርወ ተሰለው የተገኙት ምስሎች የሚያሳዩት በሥልጣን ላይ የነበረው የገዥ መደብ በአብዛኛው ኢትዮጵያውያንን ያካተተ ስለመሆኑ ነው፡፡ በወቅቱ የመንግሥት መዲና ወደ መካከለኛዋ ግብጽ የተዛወረበት ወቅት ነበር፡፡ በእነዚህ መንግስታት ዘመን በግብጽ ይኖሩ የነበሩ በአሥር ሺህ

የሚቆጠሩ ኒግሮዎች ወደሶርያና ዓረቢያ ምድር፤ግብጽ ላደረገችው የመስፋፋት ዕቅድ በወታደርነት ስለማገልገላቸው ተጠቅሷል። ከ6ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን በኋላ ግን መዛግብቶቹ መረጃ አልባ ናቸው ማለት ይቻላል። በቀጣዩ ዘመናት ስለተከናወኑት ሥራዎች የሚገልጹ ሐውልቶችም የሉም።

በግብጽ ታሪክ የመካከለኛው ንጉሣዊ መንግሥት የሚባለው ከ2400-2000 ዓመት ቅ.ል.ክ ያለው ዘመን ሲሆን፣ከዚህ በፊት የነበረው ንጉሣዊ ዘመነ መንግሥት የሜምፋይት ዘመን ተብሎ ይጠራ ነበር። የቀጣዮቹ ሶስት ሥርወ መንግሥታት ደግሞ የቴባን (Theban) ዘመን ይባላሉ። ዘመኑ የቴባን ገዥዎች አገዛዝ ዘመን ነበር ተብሎ ይታወቃል። ግብጽ፤ወርቃማው ወደሚባለው ዘመን የተሸጋገረችው በ12ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ሲሆን፣የአሦር ምድር ደግሞ በጦርነት ወደ ባድማነት ተለውጣ ነበር።

የኩሽ ደም የነበረው አሜን ኤምሃት፤ኃያል ንጉሥና የሁለቱ ምድሮች ገዥ በመባልም የሚታወቅ ሲሆን፣ከ6ኛው ሥርወ መንግሥት በኋላ ወድቀው የነበሩትን የሥነ ጥበባት ሥራዎችና የሥነ ሕንጻ ዕውቀቶችን ነፍስ ዘርቶባቸዋል። ለዚህ የሚጠቀሰው ምክንያት ጥንት ግብጽን ለሥልጣኔ ያበቃው የጥንቱ የኩሽ ደም በዙፋኑ ላይ ዳግም በመቀመጡ ሲሆን፣በዚህ ንጉሥ ዘመን በአሥር ሺህ ኤከሮች የሚቆጠሩ ረግረጋማና ውሃ ያቆሩ መሬቶች ተወግደዋል፣የአባይ ወንዝ የተትረፈረፈ ውሃ ወደ



ሰው ሠራሽ ሃይቅነት ተለውጧል። አሜን ኤምሃት ቀዳማዊ በትንሹ 20ሺህ ኤከር ጠፍ መሬቶችን ለማልማት ከደቡብ ሰዎችን አምጥቶ በማስፈር እንደወይን፣አጃ፣ጥጥ፣አፊር፣ባቄላ፣ቀይ ሥር፣ሎሚና ሌሎች የአትክልት ውጤቶች እንዲመረቱ አድርጓል።



ከግራናይት አለት ተጠርቦ በታኒስ ቤተ መቅደስ የተገኘውና በሚስተር ደብሊው ኤም ኤፍ ፔትሪ የተነሳው ፎቶ ግራፍ የተገኘው የአሜን ኢምሃት ቀዳማዊ ምስል (12ኛው ሥርወ መንግሸት)።

ግብጽ፤ በንጉሥ ኡሱርጤሰን (Usurtesen) ካልዓይ(2ኛ) ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ ብልጽግና መቀዳጀቷ ይነገራል። የኡሱርጤሰን ጦር ሠራዊት አንድ መቶ በሮች ከነበሯት የቴብስ ከተማ በድል እየተመመ ሲወጣ የሚያሳይ ምስል በሃውልቶቿ ላይ ይታያል። አሜን ኢምሃት ካልዓይና ሣልሣዊ እንዲሁም ኡሱርጤሰን ቀዳማይ የዘር ግንዳቸው ከኑብያ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ነበሩ።

ግብጽ ወደ ቀደሞው ክብሯ የተመለሰችው ከላይ በተጠቀሱት ፈርዖኖች ዘመን ሲሆን፣በተለይ ኡሱርጤስን ሣልሳዊ በዘመነ መንግሥቱ በድል አድራጊነቱ የታወቀ፣ እንዲሁም በምህንድስና ሥራ ውጤቶቹ የላቀ ደረጃ ደርሶ እንደነበረ ማስረጃዎቹ ይገልጻሉ። ከዚህም ባሻገር ኡሱርጤስን በኑብያ ውስጥ እንደአምላክ የሚታይ ነበረ።

የግብጽን ሥርወ መንግሥት በ12ኛው ዘመን ኃያል የሆነ የኩሻዊ መንግሥት ይወዳደራት እንደነበረ ታሪክ ይገልጻል። ኢትዮጵያና ግብጽ በነዚህ ዘመናት መካከል የመለያየት ሁኔታ የተከሰተበት ቢሆንም፣በግብጽ ሥልጣን ጨብጠው የነበሩት ኢትዮጵያውያን እንደነበሩና በወቅቱም የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እስከ ግብጽ ደቡባዊ ጫፍ ድረስ ይደርስ እንደነበረ በታሪክ ተዘግቦአል።

አሜን ኢምሃት ሣልሣዊ እጅግ ሰፊ የሆነውን የሞኢሪስ ሰው ሠራሽ ሐይቅ በመገንባት የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህን ድንቅ ሥራ የተመለከተው የግሪኩ ታሪክ ፀሐፊ ሄሮዶተስ ስለ አሜን ኢምሃት ገለጻውን በአድናቆትና በሰፊው ነበር ያሰፈረው።

በግብጽ የታላቅ መከራ ዘመን ወረደ የሚባለው ከ2080-1525 ዓመት ቅ.ል.ክ ነበር፤በ1700 ዓመት ቅ.ል.ክ፤ማለት በ13ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን፤ ግብጽ የተወረረችበትና ድል የተነሳችበት ዘመን ሲሆን፣በነዚህ ዘመናት ምንም ዓይነት የተዘገበ የታሪክ መረጃዎች የሉም ማለት



ይቻላል። ለዚህም የሚጠቀሰው ምክንያቱ ሃገሪቱ በተከፋፈለ የንጉሣዊ አገዛዝ ሥር ወድቃ በነበረችበት ወቅት፤ሃይክሶስ(Hyksos) የሚባሉ ጨካኝና ምህረት የለሽ ነገዶች ምድሪቱዋን በመውረራቸው ውድቀትዋ እየተባባሰ ነበር፤ከግብጽ በስተደቡብ የነበሩ ልዑላን ግን ግዛታቸውን ከቶ አላስደፈሩም። ከእስያ የመጡት እነዚህ ነገዶች በአርብቶ አደርነት ኑሮ የሚታወቁ ሲሆኑ፣በእነርሱ ወረራ ወቅት በምድረ ግብጽ የነበሩት ቤተ መቅደሶች ፈረሱ፤ሐውልቶችም ወደሙ። ለዓባይ አካባቢ የሥልጣኔ ምንጩ ከእስያ ነው ለሚሉ ሁሉ ይገነዘቡት ዘንድ የሚገባቸው ጉዳይ ቢኖር፣የጨለማው ዘመን በመባል በግብጽ የሚታወቀው ዘመን በእነዚህ እስያውያን አገዛዝ ዘመናት መሆኑን ነው። ግብጽ፤በሃይክሶስ ወራሪዎች በተያዘችበት ወቅት የታችኛው ግብጽ የንጉሣዊ ቤተሰብ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በስደት ኖሯል።

እኒህን ጨካኝ እስያውያን ከግብጽ ምድር ያባረረው ንጉሥ አህሜስ(Aahmes) የሚባል ክልስ የቴባን ሰው ሲሆን፣ግሪኮች አሞይሲስ እንዲሁም የሰሜንና የደቡቡ ንጉሥ ብለው ጠርተውታል። ይህ ሰው ጥቁርና ውብ የሆነችውን ልዕልት ኔፍሩዋሪን(Nefruari) በማግባቱ የኩሾቹን ጠንካራ ድጋፍ ለማግኘት አስችሎት ነበር። የግብጽ ፈርዖኖች በጋብቻ ከጥቁር ልዕልታት ጋር የመተሳሰራቸው ጉዳይ የተለመደ የነበረበት ዋናው ምክንያት፣የኢትዮጵያ ንጉሥ ከነበረውና እንደ አምላክም ይመለክ ከነበረው ከአሜን ራዕ የዘር ግንድ ውስጥ የመሆናቸውን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ ነበር።

ታላቅ ውበት፣ጠንካራ ገፀ ባህሪና የማስተዳደር ችሎታ የነበራት ንግሥት ኔፍሩዋሪ ወይም ኔፈርታሪ (Nefertari) በግብጽ ታሪክ ውስጥ እጅግ የተከበረች ሴት ነበረች።ግሪኮች፤አሜኖፊስ(Amenophis)ብለው የሚጠሩት አሜን ሆቴፕ(Amenhotep) ልጇ ሲሆን፤ከእናቱ ጋር በጋራ በመሆን ለብዙ ዘመናት ገዝቷል። ማሪየት፤በ1850 ዓ.ም የፈርዖን አህሜስን እናትና የኑብያን ንግስት የነበረችውን የአሆቴፕን(Aahotep) ያልበሰበሰ አስከሬን አግኝቷል። በአስከሬኑ ላይ ያሉት የጌጣ ጌጥ ሥራዎች ጥንት በነበሩበት ሁኔታ እንዳሉ በካይሮ ሙዚየም ውስጥ ይታያሉ። ከሥራዎቹ ድንቅነት የተነሣ የዘመናችን ጌጣ ጌጥ ሠራተኞች እንኳንስ እንደርሱ አድርገው መሥራት ቀርቶ በቅጡ አስመስለው ለመሥራት እንደሚቸገሩ መስክረዋል።

ግብጽን ወደ ቀደምት የበላይነት ክብሯ የመለሳት ፈርዖን አህሜስ ሲሆን፣የፈራረሱትንና የተዘጉትን ቤተ መቅደሶች እንደ ጥንት መልካቸውና ውበታቸው አድርጎ አስገንብቷል፤በአምስት መቶ ዓመታት የሂክሶስ አገዛዝ ግብጽ ያጣችውን ሁሉ በጥቂት ዓመታት መልሳ ለማግኘት እንድትችል አድርጓታል። በእርሱ ዘመን፤ ሀገሪቱ በታላላቅ ሕንጻዎችና የመንገድ ግንባታዎች የተሞላችበት፣የንግድና ዕደ ጥበባት በሮች የተከፈቱበት ወቅት ሲሆን፣አህሜስ የመሰረተው ኢምፓየር ግብጽን ለቀጣዩ 1500 ዓመታት ወደ ዕድገትና ብልጽግና ዘመን መልሷታል።



በግብጽ የ18ኛው ሥርወ መንግሽት ከ1500-1300 ዓመት ቅ.ል.ክ ሲሆን፣ ሥልጣኔዋ ጣራ የነካበት፣የዓለም ዳኛና ፈራጅ እስከ መሆን ደርሳ የነበረችበት ዘመን ነበር። ሳይስ እንደሚለው፣ግብጽ በምስተራቅ አቅጣጫ ያሉትን መንግሥታት በጦርነት ድል በማድረግ ወደ ኤምፓየር ደረጃ የተሸጋገረችበት፣ግዛቶችን ያስፋፋችበት፣ንብረት ያከማቸችበት፣በገጸ በረከት የተንበሸበሸችበት ዘመን ሲሆን፣የፈርዖን አህሜስና የንግሥት ኔፍርታሪ ልጅ የሆነው አሜኖፊስ ቀዳማዊ ይህንን የተራዘመ የኢትዮጵያ ጦርነት ከመሩት መካከል አንዱ ነበር። ልጁ ቶትመስ ቀዳማዊ፤ ሶሪያንና ፊንቂያን በቁጥጥሩ ሥር ስለማድረጉ ታሪክ ይዘግባል። የእርሱ ሴት ልጅ ሀታሱ(Hatasu) ደግሞ የአሜን ልጅና መገለጫው ነኝ በማለት ራሷን ትጠራ ነበር። ቶትመስ ቀዳማዊ፣የሁለቱ ምድሮች የበላይ ጠባቂ ተብሎ ከመጠራቱም ባሻገር የጦር ሠራዊቱን ከሶኡዳን በስተምዕራብ ወዳሉት ምድሮች አዝምቷል። የሚገርመው ጉዳይ የኢትዮጵያውያን ገዥነት በታዩባቸው በ4ኛው፤በ12ኛውና በ18ኛው የግብጽ ሥርወ መንግሥታት ዘመናት የነበሩት የኪነ ጥበባት ውጤቶች ተመሳሳይ ሆነው የመገኘታቸው ነገር ሲሆን፣ኢትዮጵያውያን ገዥዎች ባልነበሩባቸው ዘመናት ደግሞ የግብጽ ባህላዊ እሴቶች ተዳክመው የታዩባቸው ዘመናት እንደነበሩ አዛምዶ ማየት ይቻላል።

ታላቁ ቶትመስ ሣልሳዊ(3ኛ) ከፈርዖኖች ሁሉ ያለ ጥርጥር የላቀ ቦታ ነበረው የሚባልበት ምክንያት እርሱ በነገሠባቸው 54 ዓመታት ሃገሪቱን የንግድ፣ የዕደ ጥበባትና የሥነ ጥበብ ሥራዎች ማዕከል

አድርጓት ስለነበር ሲሆን፤እንደ ሳይስ አባባል፣በዚህ ፈርዖን ዘመን የቴብስ ከተማ የዓለም መዲና በመሆኗ የተነሳ ሀብት ወደ እርሷ ከመጉረፉም ባሻገር በነበረው ታላቅ የባህር ኃይል በሜዲትራንያን ባህር ላይ የበላይነትን ተቀዳጅቶ ነበር። በአልጀሪያ የእርሱ ሐውልት ተገኝቷል፣በካርናክ "የጥንት ቅድመ አያቶች" አዳራሽ ተብሎ በሚጠራው ሥፍራ ቶትመስ ሣልሣዊ ለቀደሙት 61 አያቶቹ ገፀ በረከት ሲያቀርብ ተስሏል። ራሱን የደቡብ ንጉሥ ልጅ ነኝ ብሎ ይጠራ የነበረው ፈርዖን ቶትመስ በኑብያ በርካታ መታሰቢያዎችን አስገንብቷል። በአምልኮት ረገድ በደቡብ የሚመለከውን አምላክ የማምለኩ ጉዳይ የሚሰጠን ግንዛቤ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት በግብጽ በትረ ሥልጣን ጨብጠው እንደነበር ነው። ቶትመስ ሣልሳዊ በግብጽ ታሪክ ውስጥ እንደታላቁ እስክንድር ይቆጠር የነበረበት ሌላው ምክንያት ሰፊ ግዛቶችን ድል አድርጎ በመያዙና በመግዛቱ ሲሆን፣ የተቆጣጠራቸውን የ628 ሕዝቦችና የከተሞች ስም በካርናክ ግድግዳዎች ላይ አስቀርጿል።

ግዛቶቹም ሶሪያ፣ሜሶጶታሚያ፣ዓረቢያ፣አርሜንያ፣አቢሲኒያና ኑብያ ነበሩ። በተጨማሪ ፈርዖን ቶትመስ ሌላው የሚታወቅበት ጉዳይ በውብ የግንባታ ሥራው ሲሆን፣የሥራው ብዛት ሥፍር ቁጥር አልነበረውም፤ለዚህም በካርናክ ተገንብቶው የነበሩት የቤተ መቅደስ ፍርስራሾች ሕያው ምስክሮች ናቸው።



ቶትመስ ሣልሣዊ ድል አድርጎ ከያዛቸው ምድሮች አሰባስቦ ያመጣቸውን የተለያዩ ዕጽዋትና እንስሳት የማቆያና የመንከባከቢያ ሥፍራዎች ነበሩት። በታክስና በግብር መልክ በየዓመቱ ከፍልስጤም፣ከፊንቂያ፣ ከሰሜን ሶሪያ፣ ከፑንት ምድር፣ ከአሦርና ከከለዳውያንም ወደ ግምጃ ቤቱ ይጐርፍ የነበረው ሀብት መጠን የለሽ ነበረ፤የቴብስን ከተማ መዲናው ያደረገው ይህ ንጉሥ የአገዛዙ ሥርዓቱ ያለጥርጥር ከቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ኤምፓየር ገዥዎች ከነበሩትን ከአሜን ራዕና ከኦሲሪስ የተለየ አልነበረም ቢባል ማጋነን አይሆንም። የመጀመሪያዋ የዓለም መዲና በመባል የምትጠራው የሜሩ ከተማ በርሱ ዘመን ነበር የተቆረቆረችው። በኋለኛው ዘመናት ግብጽን ለቀው የወጡት የኢትዮጵያ ካህናትና ወታደሮች ግን መዲናቸውን በናፓታ መሥርተዋል። አንዳንድ የታሪክ ጸሓፍት ይህ የጥንቱ ኤምፓየር በአጠቃላይ ስድስት ሺህ ዓመታትን አሳልፏል ይላሉ።

የፈርዖን ቶትመስ ሣልሣዊ ልጅ አሜን ሆቴፕ ካልዓይ ሲሆን፣ በእርሱ ዘመን ግብጻውያን የነነዌን ከተማ ይዘዋል። ከተማይቱ እንዳትማረክ ተባብረው የተዋጉትን የሰባት ነገሥታት አስከሬን ይዞ የተመለሰው ይህ ንጉሥ፤የሚች ነገሥታቱን ራስ በመቁረጥ በቴብስ ከተማ አደባባዩ ላይ ሰቅሏቸው ነበር። ቀጥሎም በ1400 ዓ.ም ቅ.ል.ክ በትረ ሥልጣኑን የጨበጠውና በደም ኢትዮጵያዊ የነበረው የኑብያይቱ ንግሥት መቱማ (Metuma) ልጅ፤ ግሪኮች አሜኖፊስ ብለው የሚጠሩት አሜን ሆቴፕ

ሣልሣዊ ነበር:: በኤልያድ ታሪክ ሜምኖን ተብሎ ተጠርቷል:: በትሮይ ጦርነት ለዕርዳታ የደረሰው እርሱ ነበር:: ጥቁሩ ልዑል በመባል ተጠርቷል:: ስልብ በተባለ ሥፍራ በሚገኝ ሐውልት ላይ እርሱና ሚስቱ ጠአይ (ፀሐይ) ለአሜን ራዕ መባዕ ሲያቀርቡ የሚያሳይ ስዕል ተገኝቷል:: በሉክሶር፤ያለውን ታላቅ ቤተ መቅደስና በቴብስ ከተማ የተገነቡትን ግዙፍ ሐውልቶችን ያሳነጸ እርሱ ነበር:: ገኘርነቱም ከደቡብ ኢትዮጵያ እንስቶ እስከ ሜሶጶታሚያ ይደርስ ነበር::

ቶትመስ ሣልሣዊ፣አሜኖፊስ ሣልሣዊና ራብዓዊ(4ኛ) ሁሉም ጥቁር መልክ ነበራቸው:: በተለይ የአሜኖፊስ ሣልሣዊ ሐውልት በጉላ መልኩ የኩሽ ኢትዮጵያዊ ገጽታ ማሳየቱን የተመለከተው ተመራማሪው ዳርዊን በእጅጉ ተደንቋል:: በዘመናችን የብዙዎችን ቀልብ የሳበው የአሜኖፊስ ሣልሣዊ ልጅ፤ ቱት አንክ አሜን (Tut-ankh-amen) የተወለደው በ1350 ዓመት ቅ.ል.ክ ሲሆን፣አቴናና ሮማ የሚባሉት ከተሞች ገና ያልታወቁበት ዘመን ነበር:: የዚህ ንጉሥ መካነ መቃብር ከቴብስ ከተማ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የመቃብር ሸለቆ ተብሎ በሚታወቀው ሥፍራ ለ3 ሺህ ዘመናት አንዳችም ጉዳት ሳይደርስበት በላይምስቶን አለት ገደል አፋፍ እንደተዘጋ ተገኝቷል:: በዚህ አካባቢ ከ18ኛው እስከ 20ኛው ሥርወ መንግሥታት የነበሩትን የፈርዖኖች መካነ መቃብራት ለማግኘት ሙከራ ሲደረግ ቆይቶ በ1922 ዓ.ም እ.ኤ.አ ሊገኝ ችሏል:: በቱት አንክ አሜን መቃብር በራፍ ላይ የተገኘው ማህተም ያመለከተው መቃብሩ ያለመደፈሩን ነበር:: ይህንን መቃብር ያገኘው ተመራማሪ ለሎርድ



ካርናርቨን ወዲያው መልዕክት ከመላኩም ባሻገር ስለግብጽ ታሪክ ዕውቀት ያላቸውን ጠበብት ድጋፍ ጠይቆ ነበር::

ወደመቃብሩ በመጀመሪያ የገቡት ተመራማሪ ፕሮፌሰር ብሬስተድ "እንዲህ ያለ ሥፍራ አያለሁ የሚል ሕልም አልበረኝም፣ቁሳቁስ የተሞላበት የፈርዖኑ መካነ መቃብር እጅግ የሚያስደንቅ ነበር፤እንዲህ ዓይነት ሀብት ካለንጉሥ በቀር ማንም አይኖረውም:: ያየሁት የኪነ ጥበብ ሥራ ውበት ለማሰብ ከምችለው በላይ ነበር" ብለዋል:: ወደ መቃብሩ መጀመሪያ ክፍል ሲገባ፤በሐውልት፣በቅርጸ ቅርጾች፣በራስ ጌጦች፣በቁም ሣጥኖች፣በአልጋዎች፣በወንበሮች፣ በሠረገላዎችና በውብ የተጌጡ የሸክላ ዕቃዎች የተሞሉ ናቸው:: በሸክላ ዕቃዎቹ ላይ ተስለው የሚታዩትን ስዕላት በጥንቃቄ ላጤነ፤ዛሬ በዘመናችን ከሚታወቁት የቻይናና የጃፓን የሸክላ ዕቃዎች ስዕል በእጅጉ የላቁ ናቸው:: የንገሡ የክብር ልብሶች በወርቅ የተጌጡ፣የአንገት ሀብሉ በአምባር መልክ የተሠራ፣የቆዳ ነጠላ ጫማው በወርቅ የተለቤጠ ነበሩ፤ እንዲሁም በመቃብሩ ከተገኙት ቅርሶች ሁሉ እጅግ የተዋበ የንጉሡ ዙፋን ነበር:: በወርቅና በብር የተለበጡና በከበሩ የጌጥ ማዕድናት የተሸቆጠቆጡም ነበሩ:: የአበባ ማስቀመጫዎቹ አስደናቂ ናቸው:: ሽቶዎቹ፣ምንም እንኳን 3ሺህ ዓመታትን ያሳለፉ ቢሆኑም መዓዛቸው እንደ አዲስ ያውድ ነበር::

ሀሮልድ ኤም ዊክስ(Harold M.Weeks)፤"የዚህ ንጉሥ ኤምፓየር ዘመን በዓለማችን እጅግ አንፀባራቂ ወቅት ነበር ብሏል:: በፈርዖን ቱት አንክሀ

አሜን መካነ መቃብር የታዩት ቅርሶች በታሪካዊ ቅርስነታቸው ዋጋ ሊተመንላቸው አስቸጋሪ ቢሆኑም ከአሥር ሚሊዮን ዶላር ያላነሰ ዋጋ አልነበራቸውም። ይህ ፈርዖን እንዲህ የተከበረ ቢሆንም፣በ18ኛው ሥርወ መንግሥት ዘመን ከነበሩት ጋር ሲነጻጸር በእርሱ ዘመን የግብጽ መንግሥት እየተዳከመ የሄደበት ወቅት ነበር።" ከሐውልቶቹና ከግድግዳ ስዕላቱ የተገኙት ማስረጃዎች የሚያሳዩት፤ንጉሡ የጥቁር ዘር ስለመሆኑ፣ የስሙ ተቀጽላ አሜንን መያዙ የግብጽና የሶሉዳን አምላክ ተብሎ ከሚጠራው ከአሜን ራዕ ጋር ለማያያዝ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ግብጻውያን በጸሎታቸው መጀመሪያና መጨረሻ ይህን ስም ይጠቀሙ ነበረ፤እኛም የክርስቲያኑ ዓለም ሰዎች ደግሞ ከዕብራውያኑ በወረስነው መሠረት የታላቁን አሜንን መጠሪያ ስም ለልመናችን ማሳረጊያ እየተጠቀምንበት እንገኛለን።

አሜኖ ፊስ ራብዓዊ (4ኛ) ደግሞ አዲስ ሃይማኖት ለመመሥረት ጥረት ያደረገና በዚህም የተነሣ በእርሱና በአሜን ካህናት መካከል የከፋ ጦርነት ተካሂዶ በመሸነፉ የተነሳ፣የቀድሞ መዲናውን ተገዶ እስከ መልቀቅ የደረሰ ሰው ነበር። የዚህ ግጭት መዘዙ ሳያበቃ በእስያ ምድር የነበረ ይዞታውን ሁሉ እስከ ማጣት አድርሶታል። በእርሱ ዘመነ መንግሥት ማብቂያ፣ግብጽ ቀድሞ ተቀዳጅታ የነበረውን ክብር ሁሉ ያጣችበት ዘመን ነበር። በእርሱ ምትክ የነገሠው ንጉሥ ግን ከአሜን ካህናት ጋር ፈጥኖ እርቅ በማውረዱ የተነሳ፣ከዚህ ዓለም በሞት በተለየበት ወቅት በነገሥታቱ መካነ መቃብር የመቀበር ፈቃድ እስከ ማግኘት አብቅቶት



ነበር። ራምሴስ ደግሞ የአሜኖፊስ ሣልሣዊ የልጅ ልጅ የነበረችውን ልዕልት ጣይን (ፀሐይን) በማግባቱ የተነሣ ለዙፋናዊው መንግሥት በትረ ሥልጣን መቀዳጀት በቅቶ ነበር። ከዚህ የጋብቻ ሐረግ የተወለደውና የቀጣዩ ዙፋን ሕጋዊ ወራሽ የሆነው ራምሴስ ካልዓይን፣ግሪኮች፤ሴሶስትሪስ (Sesotries) ብለው ይጠሩት ነበር። የ19ኛው ሥርወ መንግስት ዘመን ከ1300 ዓመት ቅ.ል.ክ ጀምሮ ሲሆን፣በራምሴስ ቀዳማይ እና በሴቲ (Seti) ቀዳማይ ዘመነ መንግሥት፤ግብጽ ወደ ቀድሞው ክብሯና ዝናዋ ለመመለስ የበቃችበት ዘመን ነበር። ራምሴስ ካልዓይ በሥልጣን በቆየበት ስድሣ ሰባት ዓመታት፤በአቢዶስ ቤተ መቅደስ ውስጥ የሃምሣ ዘጠኝ ወንድ ልጆቹና የስድሳ ሴት ልጆቹ ስም በዝርዝር ተጽፎ ተገኝቷል። በኑብያ፣ሁለት ድንቅ ቤተ መቅደሶችን እንዲሁም በካርናክና በሉክሶር ተጨማሪ ቤተመቅደሶች አስገንብቷል። ሶርያን፣ሜሶጶታሚያን፣አሦርን፣ሜድን፣ፋርስን፣ባክትሪንና ሕንድን እስከ ጋንጅስ ወንዝ ድረስ እንዲሁም ስካቲያንስንና የታናሽቱ እስያ ነዋሪዎችን በመዳፉ ሥር አድርጎ ገዝቷል። እነዚህ የተጠቀሱት ሥፍራዎች ሁሉ ጥንት ኩሻውያን ይኖሩባቸው የነበሩ ናቸው። ፈርዖን ራምሴስ ካልዓይ፣ እነዚህን ሁሉ ሃገሮች ድል ነስቶ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ወደ መዲናው ይዞት የተመለሰው ምርኮና የዘረፈው ሀብት መጠን የለሽ እንደነበር ይነገራል።

ዘመኑ፤የሕዝቦች ዓይነትና ብዛት ለውጥ የተከሰተበትና የሕዝብ ፍልሰት ወደ ደቡብ አቅጣጫ የተስፋፋበት፤የዘመናይቱ ፋርስ ብሔር፣የአርመንና

የቱሮ ስካቲክ ሕዝቦች ወደ ግሪክ በብዛት መፍለስ የታየበት ወቅት ነበር። በእነዚህ ሕዝቦች ፍልሰት የተነሳ ግብጽ በሕዝብ ብዛት ተጨናንቃ ስለነበረ፤ከሕንድ እስከ ስፓኝ ተሠራጭቶ የነበረው የኩሽ ሕዝብ ወደ ቀድሞው ምድሩ መመለስ በመጀመሩ ተመላሾቹን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረችም። ወደ ሜሶጶታሚያ፣ሶርያ፣ኤጅያን ባህረ ሰላጤና ወደ ታናሽነቱ እስያ በነበረው ፍልሰት የተነሳ የየሃገራቱ ሕዝቦች አስተሳሰብ ቀስ በቀስ እየተቀየረ በመሄዱ ግብጽን በጥላቻ ዓይን ማየት ጀመሩ፤ ብሎም በግብጽ ላይ ቅኝ ግዛቶቹ አመጹ።የዚህ ውጤት ግብጻውያንን በዓባይ ወንዝ ዳርቻዎች ብቻ እንዲወሰኑ አስገደዳቸው። ፈርኦን ሬሜሴስ ሣልሣዊ በግብጽ ዙፋናዊ መንግሥት የጀግንነት ሥራ የሠራ የመጨረሻው ንጉሥ ሲሆን፣እርሱ ወደ ሥልጣን በወጣበት ዘመን፤ግብጽ በጠላቶቿ ተከባ የነበረችበት ጊዜ ነበር። ይህም ሆኖ፣ከጠላቶቿ የተሰነዘረባትን ጥቃት ተቋቁማ ለማባረር ችላለች። ከሬምሴስ ሣልሣዊ በኋላ የነገሡት ገዥዎች ግን እምብዛም የሚታወቁበት ነገር የለም። በ1100 ዓመት ቅ.ል.ክ፤የአሞን ካህናት ሥልጣን በመንጠቅ ለጥቂት ጊዜያት ዙፋን ላይ ቢቀመጡም ብዙ ጊዜ ለመቆየት አልቻሉም።





ፈርኦን ራምሲስ(Rameses) 2ኛ(ታላቁ)
በቀይ ግራናይት ድንጋይ ሐውልት የተቀረጸ( ፎቶግራፍ በሚስተር W.M.F.Petrie)

በ1090 ዓመት ቅ.ል.ክ ታናይት የተባለው የገዥ መደብ የአሞንን ካህናት በማባረር ሥልጣን በመያዝ ለአንድ መቶ ዓመታት ገዝቷል። ከእነርሱ ቀጥሎ ከታችኛው ግብጽ ወደ ሥልጣን የወጡት ቡባስተስ የተባሉት ናቸው። የቲናይት ሥርወ መንግሥት በግብጽ ሥልጣን ይዞ በቆየባቸው ዘመናት መላው የአሞን ከፍተኛ ካህናትና የንጉሣውያን ቤተሰቦች ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በናፓታ ከተማ ተቀናቃኝ መንግሥት አቋቁመው ነበር። በኢትዮጵያውያንና ሊቢያውያን የተሞላ የጦር ሠራዊት የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ አዘርች አሜን (Azerch-Amen) ኃይሉን በማጠናከር የግብጽን ምድር ሙሉ በሙሉ ከያዘ በኋላ ወደ ፍልስጤም ግዛት ዘልቆ በመግባት በቁጥጥር ስር አድርጓት እንደነበር ማስረጃዎች አሉ።

ንጉሥ ፒያንኪ(Pianki) በ800 ዓመት ቅ.ል.ክ የቴባይ ግዛትን እንደ አንድ የኢትዮጵያ አውራጃ አድርጎ ገዝቷል፤በቴብስ ከተማ ዘውዳዊው መንግሥቱን ሲያቋቁም ግብጻውያን በመልካም አቀባበል ተቀብለውታል። ይህም የሚያመላክተው ከታችኛው ግብጽ ሰው ይልቅ በኢትዮጵያዊ ንጉሥ መግዛትን መምረጣቸውን ነው።ንጉሥ ታርካካ በ693 ዓመት ቅ.ል.ክ፣መሳውን የዓባይ ሸለቆ በቁጥጥሩ ሥር በአደረገበት ወቅት የቴብስና የሜምፊስ ከተሞች በሮቻቸውን በደስታ ከፍተው ተቀብለውታል። እርሱም በዚሁ ዓመት በጀበል ባርከል ታላቅ ቤተ መቅደስን አስገነባ። ፀሐፊው ስትራቦ፣የንጉሥ ታርካካና የንጉሥ ሬሜሴስ ካልዓይ የድል ገድላት ተቀራራቢነት አላቸው ብሏል። ይህ ንጉሥ በምዕራብ በኩል የሄርኩለስ ምሰሶ የተባለውን ምድርና በስተምስራቅ ደግሞ የአሦራውያንን ግዛት ተቆጣጥሮ ነበር።

በፒራሚዶቹ ላይ የሚታዩት በርካታ ምስሎች የሚያሳዩት፣የሁለቱ ምድር ገዥዎች ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ፣የንግሥናቸው የአጠራር ስም የአሜን ራዕ ስም ተቀጽላ ያደረገ መሆኑን፣እንደ አንክ ካ ራዕ፤አሉ አሜንና፣አሜን አርክ ኔብ የመሳሰሉ ስሞችን ስናስብ፣ኢትዮጵያውያን በጥንት ዘመን ኑብያንና ግብጽን እንደ አንደ ሃገር አድርገው ያስተዳድሩአቸው እንደነበረ አመላካች መሆኑን ነው።

ንጉሥ ታርካካ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት ማለትም በ670 ዓመት ቅ.ል.ክ፤አሦራውያን፣ከግብጽ ምድር አስወጡት። በእርሱ ምትክ የነገሠው



ንጉሥ ታኑት አሜን፣ግብጽን ለማስመለስ በሞከረበት ወቅት የቴብስና የሜምፊስ ከተሞች ተባብረውታል፤የታየር ከተማም ድጋፍ አድርጋለት ነበር። ሆኖም ግን፣ አሦራውያን ዳግም ተመልሰው ከፍተኛ በቀልና ታላቅ ጥፋት አደርሰዋል። ከሊቢያ ዘር ግንድ የነበረውና የኢትዮጵያዊውን ንጉሡ ሳባካ (Sabaka) ሴት ልጅን ያገባው ፈርዖን ሣምቲክ (Psamtik) በ663 ዓመት ቅ.ል.ክ ገደማ የግብጽን በትረ መንግስት ለመጨበጥ በመብቃቱ የአሦራውያንን ቀንበር ሰብሯል። በትረ መንግሥቱን ለመጨበጥ ላደረገው ውጊያ የግሪክ ቅጥረኛ ተዋጊ ወታደሮች ታላቅ ሚና ተጫውተው ስለነበር፤ላደረጉለት ውለታ ምላሽ በእርሱ ዘመነ መንግሥት የግብጽ በሮች ለግሪክ ሰዎች የተከፈቱ ነበሩ። በተጨማሪም የመንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃዎች ሳይቀር በውጭ ዜጎች እንዲያዙ አስደርጎ ነበር። በዚህ ድርጊት የተቆጣው ቁጥሩ ከ200 ሺህ የሚበልጥ የጦር ሠራዊት የግብጽን መንግሥት በመክዳት ወደ ኢትዮጵያ በመቀላቀሉ የተነሳ፣እባኮችሁ ተመለሱ! በማለት ንጉሡ ያቀረበውን ልመናና ጥሪ ቸል በማለት በኢትዮጵያ ስለመቅረታቸው ታሪክ ዘግቧል። የግብጽ ዙፋናዊ ሥርወ መንግሥት ማክተሚያ የተቃረበበት ከ343 ዓመት ቅ.ል.ክ ጀምሮ ሲሆን፣በንጉሥ ኔክታኔበስ ዘመነ መንግሥት፣የፋርስ ኃይሎች ድል እያደረጉ ወደ ግብጽ በተቃረቡበት ወቅት ንጉሥ ኔክታኔበስ የግብጽን ሀብት ሰብስቦ ወደ ኢትዮጵያ ኮብልሎአል። የፋርስ ኃይሎች ግን ለብዙ ጊዜ በድል አድራጊነት በግብጽ ለመቆየት አልቻሉም፣ምክንያቱም የድል አድራጊነቱ ዕድል ፈንታ ብዙም ሳይቆይ ወደታላቁ እስክንድር ስለተሸጋገረ።

መሳው የግብጽ ግዛት በ332 ዓመት ቅ.ል.ክ በታላቁ እስክንድር አገዛዝ ሥር በወደቀችበት ወቅት ግብጻውያን እስክንድርን እንደ አርነት አውጪያቸው በማድረግ ተቀብለውታል፡፡ በ331 ዓመት ቅ.ል.ክ.፤ታላቁ እስክንድር በሊቢያ በረሃ የነበረውን የአሞንን ለምለም የአትክልት ሥፍራ በጎበኘበት ወቅት በዚያ የነበሩ ካህናት የአሞን ልጅ በማለት ተቀብለውታል፡፡ በዚያው ዓመት የከረምት ወራት የእስክንድርያ ከተማ ተቆርቁራለች፡፡ በ306 ዓመት ቅ.ል.ክ ቀዳማዊ ፕቶሎሚ ግብጽን ወደ ጥንቱ የክብር ደረጃ የመለሰበት፤የእስክንድርያ ከተማ የዓለም የንግድና የባህል ማዕከል የሆነችበት ዘመን ነበር፡፡ እስክንድርያ በውስጧ በነበሯት ሙዚየሞችና ቤተ መጻሕፍት ክምችት የተነሳ የግብጽ ታሪክ ከመጀመሪያው ተቀነባብሮ ይጻፍ ዘንድ የተወሰነበትና ማንኤቶ(Manetho) የተባለው የታሪክ ጸሐፊ ዜና መዋዕሉን ለማዘጋጀት የበቃበት ዘመን ነበር፡፡ ይህ ከፕቶሎሚ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየው ንጉሣዊ ዘር እስከ ክሊኦፓትራ ዘመን ቢደርስም፣ በእርሷ ዘመን የሮማው ቄሣራዊ አገዛዝ ገናና ስለነበር፣የአገሯን የይስሙላ ነጻነት ለማስጠበቅ የበቃችው በቄሣሩ ላይ በነበራት ተወዳጅነት ብቻ ነበር፡፡ ከእርሷ ሞት በኋላ ግን፣የፈርዖኖች ምድር የነበረችው ግብጽ፤በሮማ ቄሣራዊ መንግሥት እንደ አንድ ክፍለ ሀገር ሆነች፡፡

በቄሣር ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ የክርስትና ሃይማኖት በታላቅ መከራ ላይ የነበረበት ጊዜ ነበር ሆኖም ግን፤በ391 ዓ.ም የመንግሥት



ሃይማኖት ለመሆንና ለመስፋፋት በቃ፡፡ ሆኖም ግን ከ639-641 ዓ.ም. መሐመዳዊያን ዓረቦች ግብጽን በመውረር ድል አድርገው በመያዛቸው የተነሳ የክርስትናው ሃይማኖት ተዳከመ፡፡ካይሮ፤ለአዲሱ የእስልምና ሃይማኖት ትምህርት ማስፋፊያ ማዕከል ትሆን ዘንድ በመዲናነት ተመረጠች፡፡ ለማጠቃለል በታናሹ እስያ፣በደቡብ ካስፒያንና በሜዲትራኒያን አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ቀደምት ነዋሪዎች ከግብጽ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ታሪክ አላቸው፡፡ የራስ ቅላቸው ሳይቀር የላይኛውን ግብጽ ሰዎች ይመስላል፡፡ ጥንታዊያኑ ስካቲያን(Scythian) ጠጉራቸው ቀይ፣ዓይናቸው ሰማያዊ፣ እግራቸውም ላይ ንቅሳት የነበራቸው፣የዘር ግንዳቸው ምናልባትም ከሰሜናዊ ክፍል ቅርንጫፍ ከሆኑ የኩሽ ሕዝቦች ሊዛመድ ይችላሉ የሚል ግምት አለ፡፡ ከታሪክ ማህደራት እንደምንረዳው፤ንጉሥ አሜኖፊስ (ሜምኖን) በአንድ ወቅት መላውን ዓረቢያ፣ሊቢያና ኢትዮጵያን በቁጥጥሩ ስር ስለማድረጉ፤ግዛቱንም እስከ ባክትሪን ድረስ ስለማስፋፋቱ በኢራናውያኑ የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

አሜኖፊስ በካውካስ ይኖሩ የነበሩትን የስካይቲክ ብሔሮች በቁጥጥር ሥር ከማድረጉም በላይ የኢትዮጵያ ግዛት እስከ ነበረችው እስከ ካልቺስና እስከ ዶን (Her.II.104) ድረስ ዘልቆ ነበር፡፡ እነዚህ ከጥንታዊው የኩሽ ግዛቶች ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፡፡ በሔርኩለስ ጽሑፍ ውስጥ እንደተጻፈው የኩሽ ግዛት እስከ ምዕራብ አውሮፓ ድረስ ስለመዝለቁ፣ሌሎች ጥንታውያን መዛግብት ደግሞ በኢትዮጵያዊው ሲማንደስ (Cymandes) የተመራ

ግዙፍ የጦር ሠራዊት ባክትሪናን ለማስገበር ስለመዝመቱ፣የድል አድራጊው የአሲሪስ የጦር ሠራዊት ደግሞ ከሕንዱ ጋንጀስ ወንዝ እስከ ዳኒውብ ወንዝ ያለውን ግዛት ስለመቆጣጠሩ፣የባኩስና የዳዩኒሰስ የጦር ሠራዊትም በምድራቸው ስለመትመሙ በምዕራብ አውሮፓ አፈታሪክ ውስጥ ይነገራል። እንዲህ እያልን የታሪክ ሂደትን እስከአለንበት ዘመን ድረስ መግለጽ እንችላለን። የዚህ አጭር ትርጉም ዋና ዓላማ በግብጽ ምድር የነበረውን የጥንታዊውን ኩሽ ኢትዮጵያ ኤምፓየር ምንነት ለኢትዮጵያ አንባብያን ለማሳወቅ ነው።

**ተፈጸመ!**

## ደራሲዋ የጠቀሰቻቸው ዋቢ መጽሐፍት


1. Roscnmuller, Biblical Geography, BK III P. 154.
2. H.G.Wells, Outline of History, Vol. 1.P. 158
3. Rawlinson, Ancient Monarchies, Vol.I.
4. Bunsen, Philosophy of Ancient History.
5. Baldwin, Prehistoric Nations.
6. Diodorus Siculus, Bk. IIII, ch . 3
7. Crowfoot, Meroe. PP. 6,30
8. Herodotus, Bk. II ,P.29
9. Cyclopedia of Biblical Literature
10. Heeren, Historical Research - Ethiopian Nations, ch. 1, P. 46
11. Maurice, Ancient History Hindustan.
12. Crowfoot, Ancient Meroe.
13. Heeren, Ancient Nations of Africa.
14. Reclus, The Earth and Its Inhabitant, Vol. I, P. 306, P.207.
15. A. H. Sayce, Ancient Empires of the East.
16. Frobenius,Voice of Africa, Vol. II, P.621.
17. Budge, Egyptian Soudan.
18. Duncker, History of Antiquity
19. Budge, Osiris and the Egyptian Resurrection.
20. Niebur, Travels, Vol. P. 104.
21. Amelia B. Edwards, A Thousand Miles Up the Nile.
22. Sir G. Gardner Welcurson, The Manner and Customs of Ar Egyptians.
23. Herdotus, Bk II, P.104